የብ/ዓ/በብ/ዓ/ጴ/ወጳ/ቤ/ክ/ፍ/ሃ/ሰ/ት/ቤት
ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት መስከረም 2006.

# የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ

# የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ

አዘጋጅ፡-

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት

መስከረም 2006 ዓ.ም

## Contents


የማቴዎስ ወንጌል ........ I

አንድምታ ........ I

አዘጋጅ፡- ........ I

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት ........ I

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ........ I

መስከረም 2006 ዓ.ም ........ I

መታሰቢነቱ ........ III

ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932-1982ዓ.ም) ........ III

መቅድም፡- ........ IV

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ........ V

የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ ........ V

መግቢያ፡- ........ V

የማቴዎስ ወንጌል ........ 1

ምዕራፍ አንድ ........ 1

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው። ........ 1

የማቴዎስ ወንጌል ........ 23

ምዕራፍ ሁለት ........ 23

የማቴዎስ ወንጌል ........ 36

ምዕራፍ ሦስት ........ 36

የማቴዎስ ወንጌል ........ 50

ምዕራፍ አራት ........ 50

የማቴዎስ ወንጌል ........ 57

ምዕራፍ አምስት ........ 57

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ........ 65

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት ........ 65

ትምህርት ክፍልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የተዘጋጀ ........ 65

መስከረም 2006 ዓ.ም ........ 65

# መታሰቢነቱ



ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932-1982ዓ.ም)

# መቅድም፡-

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደምናገኘው ስለወጣቶች ኅብረት(ማኅበር) የመጀመርያ ጽንሰ ሐሳብ የተነሳው ከግብጽ ከመጡ አባቶች በብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመነ ፐርትክና ነው፡፡ የኢትዮጰያ ኦርቶዶስክ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናንን በሃይማኖት በምግባር ለማድናት ካላት ጽኑ ዓላማ የተነሳ የሰንበት ት/ቤቶችን በየአጥቢያው አቢያተ ክርስቲያናት በማደራጀት የፍሬው ተቋዳሾች እንድንሆን ግንባር ቀደም አስተዋጽዎን አበርክታለች፡፡ ጉዞዋ የማይቋረጥ የሕይወት ስንቅን ያነገበ ነውና ዛሬም ወደፊትም ይህ ተግባርዋ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደ ሰንሰለት በተጣመረ የሰንበት ት/ቤቶች የእለት ክትትል ታግዞ ይራመዳል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤታችን በ1959 ዓ.ም ተመስርቶ እስካለንበት ዘመን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በቅድምያ የመንፈሳዊ ወጣቶች ኅብረት የነበረ ቢሆንም 1986 ዓ.ም ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ይህ ሰንበት ትምህርት ቤትም ወጣቶችን በመሰብሰብ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ ኖት አዘጋጅቶ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዶግማ ቀኖና ትውፊት በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ይህንን መማርያ ኖት በተለያየ ወቅት በማዘጋጀት አዲስ ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ አስታየት በመስጠት ትምህርት ክፍሉን በመምራት የተባበሩንን መምህራን ሙሉዓለም ሽፈራው ሙሉቀን ተሾመ ዮሐንስ ኃይሉ ዮሐንስ ገ/መስቀል ሚሊዮን ዳንኤል ጋዙ ሚኪያስ ይልማ ኢየሩሳሌም ጌቱ ዲ/ን ያሬድ መለሰ አብርሐም በቀለ እግዚአብሔር ጸጋውን ያድልልን እንላለን፡፡

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል

መስከረም 2006 ዓ.ም

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ

## መግቢያ፡-

ጥንት በቀደመው ዘመን አባቶቻችን በቃል የተማሩትን በቃል ሲያስተምሩ እኩሌታዎቹ በቃል የተማሩትን ብዕር ቀርጸው ብራና ዳምጠው ቀለም በጥብጠው በጽሑፍ ሲያሰፍሩ በብዙ ድካም ነበር አያሌ ነገሮችን ያቆዩልን፡፡ ከእነርሱም ሲወርድ ሲወራረድ ከእኛ የደረሰው አንዱ የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት ነው፡፡ አንድምታ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማብራራት፣ የተቋጠረን ለመፍታት የሚያገለግል የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ እንዲሁም ምዕመናን እምነታቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲገነዘቡት ያደርጋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትርጓሜ የሰውን ልብ እንዲያበራና አስተዋይ እንደሚያደርግ ተጠቅሷል /መዝ 118፡130/ ስለዚህም የትርጓሜ ትምህርት ለአንድ ክርስቲያን እንደሚያስፈልገው ምንም ጥርጥር የሌለው ነገር ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ትርጓሜን ማወቅና መማር የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያኖች በቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ወንጌልን እንዲረዱ ስለሚደረግ እና የአባቶችን ትምህርት በሚገባ እንዲያውቁ አንድምታን መነሻ በማድረግ እንመለከታለን፡፡ የምሥጢር መጻሕፍትን ክቡር ማዕድ የመፈተትና የማደል ሙያ የተቀዳጁ (የታደሉ) ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ‹‹አንባቢ የሆነ አስቀድሞ የመጽሐፍን አርዕስቱን' መቅደመ ነገሩን' ምክንያተ ጽሕፈቱን ሳይዝ ወይም ሳያውቅ ምልዐተ ንባቡን የሚመለከት አይኑር›› ብለዋል፡፡ ሊቃውንቱ እንዲህ የሚያደርግ ቢኖር እርካብ ሳይረግጥ ወደ ኮርቻ'ድንክ (ደረጃ) ሳይረግጥ ወደ ዙፋን የሚወጣ የዋህ ሰውን ይመስላል እንዳሉት እንዳይሆንብን የማቴዎስን ወንጌል አንድምታ ትምህርት ከመጻፋችንና ከመናገራችን በፊት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስቀድሞ መማር ይገባል፡፡እነርሱም፡-

- የትርጓሜ አስፈላጊነት
- የትርጓሜ ዓይነት
- የአንድምታ ትርጓሜ (ትምህርት) መቼ ተጀመረ?
- ስለ አራቱ ወንጌላዊያንና ምሳሌዎቻቸው
- የቅዱስ ማቴዎስ የሕይወት ታሪክ፣ ሥራና ገድል
- የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ዓላማና አከፋፈሉ የሚሉትን ዋና ዋና አርዕስቶች አስቀድሞ መመልከት ይገባል፡፡

### ሀ. የትርጓሜ አስፈላጊነት

ሰው እንደመላእክት አዋቂ ብሩህ አእምሮ ያለው ሆኖ ተፈጥሮ ሳለ በኃጢአት ምክንያት ብሩህ አእምሮው ጨለመ'ፀጋ እግዚአብሔር ተለየው'ተሰጥቶት የነበረውን ክብር በማጣቱም የፈጣሪውን ቃል ትቶ የፍጡር ቃል በመስማቱ አዋቂ ሆኖ ሳለ አላዋቂ ሆነ፣ የእግዚአብሔርን መልእክት በቀጥታ ከማስተዋል ተገታ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ‹‹መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ›› ማቴ 22፡29 እንዲህ ሲል የሰው ልቡና ነገረ እግዚአብሔር እንደተሰወረበት የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መልዕክታት የያዙ

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሆናቸው ሰው የእግዚአብሔርን ምስጢር እንዲያውቅና እንዲረዳ ትርጓሜ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገረ እግዚአብሔር ተሰውሮበታልና፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንደ ድንች እና እንደ ካሮት ተቆፍሮ ወጥቶ የሚበላ እንጂ በዓይን ታይቶ በእጅ የሚቀነጠስ አይደለም፡፡ ሥጋዊ ምግብ እንኳን በእሳት በስሎ ሲበሉት ለሰውነት ተስማሚ እንደሚሆን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን በትርጓሜ ተብራርቶ ሲማሩት ሲመገቡት ለህይወት ተስማሚ ይሆናል ብሎም ለሰማዕትነት ያበቃል፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያምር የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ከዚህ በታች ያሉትን ነገሮች ለመረዳት ለመገንዘብ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ነው፡፡

ሰዎች አንዱ ከሌላው በብዙ መንገድ ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

በሀገር፡- የአንዱ ሀገር ትምህርት'ባህል ወግና ልማድ ቋንቋ ወዘተ ከሌላው ሀገር ይለያል፡፡

በትምህርት፡- አንዱ ምሁር ሌላው ኢምሁር ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም በማስተዋል በሞራል በማገናዘብ አንዱ ሰው ከሌላው ሰው በትምህርቱ ብቃት በእውቀት የመቀበል የመረዳት ችሎታው ይለያያል፡፡ ስለዚህ እነዚህን የመሳሰሉት እውነታዎች ከግንዛቤ ያስገባ ግሩም የሆነ ገለጻና ማብራሪያ ለመስጠት ትርጓሜ አስፈላጊ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የተነገረበትና የተጻፈበት ዘመን እጅግ ሩቅ ነው፡፡ ቦታው ባህሉ ሥርዓቱ ኑሮው ልማዱ ቋንቋው ዛሬ ካንበት ዘመን የተለየ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተነገረላቸው ህብረተሰቦች በአስተሳሰብና በዕውቀት ከእግዚአብሔርም ጋር ከነበራቸው ቅርብነት አኳያ ከዛሬው ህብረተሰብ የተለዩ ነበሩ፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለዛሬው ኅብረተሰብ መተርጎም አስፈላጊ ነው፡፡

ሌላው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ የንግግር ዓይነቶች እንደ ሕልም፣ እንቆቅልሽ፣ ምሳሌያዊና ቅኔያዊ፣ ራዕይና ትንቢት ጥበብም ስላሉት ሌላም በእንስሳት ጠባይ በርካታ መልእክቶች አሉ፡፡ እነዚህን ለመረዳት ትርጓሜ አስፈላጊ ነው፡፡ የቀድው ንባብ በኋለኛው ተተርጉሞ ይገኛል፡፡ ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን፣መጽሐፈ ሳሙኤልና መጽሐፈ ነገሥት በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ተብራርተዋል፡፡ እንዲሁም ቀደም ያሉ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት በኋለኞቹ ተተርጉመዋል፡፡ ዘፍ 40፣1-23፣ መሳ 14፣12፣ ዳኤል 5፣12፣ ሉቃ 13፣32፣ ዮሐ 10፣11፣ ኤር 31፣29-30 ሕዝ 18፣1፣ ማቴ 10፣10 በ1ኛጢሞ 5፡18 ዮሐ 2፣21፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያ እርስ በርሱ የተያያዘ እንደመሆኑ በአንድ ቦታ ትንቢት የተነገረለት በሌላ ቦታ ተፈጽሞ በአንድ ቦታ ያልተተረጎመው በሌላኛው ተተርጉሞ ይገኛል፡፡ ሌላው መጽሐፍት እርስ በእሳቸው የሚጋጩ መስለው የሚታዩት ትርጉማቸውን ካለማወቅ የተነሣ ነው፡፡ ትርጓሜ ግን ይህን ሁሉ ያስታርቀዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው የመጻሕፍትን ከላይ አርእስታቸውን ከታች ህዳጋቸውን ተመልክቶ አንዱን በአንዱ መርምሮ አመዛዝኖ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ እነ ቅዱስ ቄርሎስ በአጠቃላይ በሃይማኖተ አበው ያሉ ሊቃውንት ከተረጎሙት ትርጓሜ ከሰጡት አስተያየት ሳይወጡ መተርጎም ይገባል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው በቃል ከመምህራን በመማር የተቀበለውንም እንዳለ በትውፊትም በትርጓሜ መጻሕፍትም ማግኘት ይችላል(ፊሊ 4፣9)፡፡ አባቶቻችን ገጽ በገጽ ከሐዋርያት የተማሩትን ያዩትንና የሰሙትን በትውፊትም በትርጓሜ መጻሕፍትም ማግኘት ይቻላል በጽሑፍም በቀጥታ ለእኛ አድርሰዋል፡፡ በተለይም በቤተ ክርስቲያን የተለመደው የትምህርት አሰጣጥ የቃል ትምህርት ይህንን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እንግዲህ ከአባቶቻችን የአስተምህሮ ሥርዓት እንዳንወጣ ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ሥልጣንን በተመለከተም ማንም ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በራሱ ሐሳብ

እንደራሱ ፈቃድ ሊተረጉም እንደማይገባው ተጽፎአል፡፡ 2ኛ ጴጥሮ 1፣20 ከዚህ የምንረዳው አንድምታ  ትርጉም ማንም እንደፈለገው ርዕስ መዞ የሚጽፈው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ያልተቃኘ' ሐዋርያትን፣ የሐዋርያን አበውን ከእነርሱም ቀጥለው የተነሡ የኦርቶዶክሳውያን አበው ሊቃውንትን ትውፊት ያልተከተሉ መጽሐፍ ቅዱስን በነጻነት ለመተርጎም ቢሞክሩም እንኳን በሥጋዊ ጥበብ በፍልስፍና ብቻ ስለሚመሩ ከስህተት ላይ ይወድቃል፡፡ 2ኛ ጴጥ 3፣18

ለ. የትርጓሜ አይነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ የትርጓሜ ስልት አላት፡፡ የራቀውን አቅርባ የቀረበውን አጉልታ የምታቀርብባቸው ልዩ ልዩ የትርጓሜ ዓይነቶች ሲኖሯት ከእነዚህ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ ነጠላ ትርጓሜ'ምሳሌ'ምስጢራዊ ትርጉም እና አንድምታ ትርጓሜ ናቸው፡፡

- ነጠላ ትርጓሜ፡-

ነጠላ ትርጓሜ የሚባለው ዘይቤውን ብቻ በቀጥታ የሚተረጉም ምንም ዓይነት ሐተታ የማያደርግ የትርጓሜ ስልት ሲሆን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የሚተረጉም ነጠላ ትርጓሜ ይባላል፡፡ በዚህ ዓይነት ትርጉም ጥንታውያን የሆኑት መጻሕፍት ከውጪ ቋንቋ ወደ ግእዝ ከግእዝም ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በዓለም ላይ አንድ ሆነው የተገኙት እንዲሁ በቀጥተኛው ዘይቤ ብቻ በመተርጎማቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በግእዝ ልሳን ‹‹በልዋ ለዛቲ ቁንጽል›› ይላል ወደ አማርኛ ሲተረጎም ‹‹ለዚያች ቀበሮ እንዲህ በሏት›› ይላል፡፡ ነጠላ ትርጓሜ ማለት ይህ ነው፡፡

ምሳሌያዊ፡-

ምሳሌ ማለት አንድን ነገር ግልጽ ለማድረግ የሚረዳ ስለሆነ በምሳሌ ሲነገር ነገርን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ‹‹ነገር በምሳሌ. . . . .›› እንዲሉ፡፡ ይህንን የአስተምህሮ መንገድ ጌታ ከምስጢራዊ ትርጓሜ ጋር በማጣመር በወንጌልም ላይ ብዙ ቦታ ካስተማረባቸው መንገዶች አንደኛው ነው፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ›› መዝ 77፣2 ማር 4፣34 እንዳለው እንግዲህ ምሳሌ ሁልጊዜ ከሚመስለው ነገር ያንሳል፡፡ ስለዚህም ምሳሌ ‹‹ዘይሐጽጽ›› ይባላል ‹‹የሚያንስ›› ‹‹ጎዶሎ››  ለማለት ፡፡ ምሳሌ በዕብራይስጥ ‹‹ማሻል›› ይባላል፡፡

ምስጢራዊ፡-

ምስጢር ማለት የተሰወረ ግን በውስጥ ያለ ላይ በላይ የማይታይ እንደ ማለት ነው፡፡ ሌላው የምስጢር ትርጓሜ የሚባለው ደግሞ ምንባቡን ሳይሻ አገባቡን ሳይጠበቅ ምስጢሩን ብቻ በመጠበቅ የሚተረጉም ነው፡፡ በዕብራይስጥ ‹‹ሳተር›› በዐረብኛ ‹‹ሰተር›› በሱርስት ደግሞ ‹‹ስታር›› በእንግሊዝኛም ‹‹ Mystery ›› ይሉታል፡፡ በምሳሌ የተነገረውን ኃይለ ቃል በውስጡ ምስጢር ይዟል ስለዚሁ ሲያስረዱን ትርጓሜ ይሆናል፡፡ ምስጢር የሚባለው ነገር እኛ ልንረዳው የምንችለው ነገር ግን ነጠላ ትርጓሜውን ይዟል ስለዚሁ ሲያስረዱን ትርጓሜ ይሆናል፡፡ ምስጢር የሚለው ነገር እኛ ልንረዳው የምንችለው ነገር ግን ነጠላ ትርጓሜውን ነው፡፡ በሥጋዊ ጥበብ መርምረን ልንደርስበት የማንችለውን ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በምሥጢራዊ ትርጉም ‹‹አንተ ኮክህ›› የሚለው ፍቺ ‹‹አንተ መሠረት ነህ›› ማለት ነው፡፡ በኮክህ(ዓለት መሠረት) የተመሰለው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው፡፡ ‹‹በልዋ ለዛቲ ቁንጽል›› ‹‹ለዚያች ቀበሮ እንዲህ በሏት›› ሲል በቀበሮ የተመሰለው ሄሮድስ ነው፡፡ ማቴ 16፣18 ሉቃስ 13፣22

ሐ. የአንድምታ ትርጓሜ

የአንድምታ ትርጓሜ የሚባለው አንድ ጊዜ ከተተረጎመ በኋላ መሠረታዊ የሐሳብ አንድነቱን ሳይለቅ እንደገና አንድም እያለ እስከ አሥርና አስራ አምስት ጊዜ የሚያወርዱበት አወራረድ የሚሰጡት ሐተታ ነው፡፡ አንድምታ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ አንድም በማለት ፈንታ ‹‹ቦ›› ይላል፡፡ የዚህም ፍቺ ሌላ ይህንን የመሰለ ትርጉም አለው እንደማለት ነው፡፡ በአማርኛ ግን ሁለተኛ ሦስተኛ አይልም እንጂ አንድ እያለ እስከ አስራ አምስትና ከዚያ በላይ ጊዜ ይወርዳል፡፡ ሆኖም ግን ሁለተኛ ሦስተኛ እንደማለት ሦስተኛ አይልም እንጂ አንድም እያለ እስከ አሥራ አምስትና ከዚያ በላይ ጊዜ ይወርዳል፡፡ ሆኖም ግን ሁለተኛ ሦስተኛ እንደማለት የሚያስቆጥር ነው፡፡

◈ የአንድምታ ትርጓሜ (ትምህርት) መቼ ተጀመረ?

የአንድምታ ትምህርት በግልጽ ሊታወቅ የቻለው በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ሊቃውንተ አይሁድ አምስቱን የሙሴ መጻሕፍትንና መጻሕፍተ ነብያትን በአንድምታ ለውጠዋል፡፡ ይህ እንዲህ ሲሆን የጌታችን ተከታዮች ቅዱሳን ሐዋርያት ትክክለኛውን የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት በር ከፍተዋል፡፡

ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ (ሐዋርያት) ወንጌልን ባስተማራቸው ጊዜ መጽሐፍ ስላልነበራቸው ትርጓሜውንም የነገራቸው በጥቂት ሥፍራ ላይ ብቻ ስለነበር ለጊዜው ትምህርቱን ፈጽመው አልተረዱትም ነበር፡፡ ከዕርገቱ በኋላ ግን መንፈስ ቅዱስን በጽርሐ ጽዮን ተቀብለው በአእምሮ ጎለመሱ፣ ምሥጢር ተረጎሙ፣ ብዙ ቋንቋም ተገለጸላቸው፡፡ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸላቸው ወንጌልን ጽፈው ለሕዝብ ለአሕዛብም እየተረጎሙ ማስተማር ጀመሩ፡፡

ሐዋርያት 3 ዓመት ከ3 ወር ያጠኑትን ትምህርት ለዓለም ለማስተላለፍ የረዳቸው ት/ቤቶችን ማቋቋማቸው ነበር፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው የመጀመሪው የክርስቲያኖች ት/ቤት በ60 ዓ.ም በቅ/ማርቆስ ወንጌላዊ የተመሠረተው የእስክንድሪያ የትርጓሜ ት/ቤት ነው፡፡ ሌላው መንፈሳዊ ት/ቤት ደግሞ በሦተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተመሰረተው የሦሪያ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ በተለይ ከ2ኛው እስከ 3ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ከነዚህ ት/ቤቶች በሚወጡ መምህራን አማካኝነት የትርጓሜ ትምህርት ሊያድግና ሊስፋፋ ችሏል፡፡ ከዚህም ሌላ ሠለስቱ ምእት /318ቱ ሊቃውንት/ በ325 ዓ.ም አርዮስን ለማውገዝ በኒቂያ ጉባኤ በተሰበሱ ጊዜ የመጽሐፍተ ብሉያትና መጽሐፍተ ሐዲሳትን እየተረጎሙ ጽፈዋል፡፡

ከ150ው ሊቃውንት በኋላም 200ው ሊቃውንት ንስጥሮን ለማውገዝ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ ባደረጉ ጊዜ እንደዚሁ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ተርጉመዋል፡፡ዮሐንስ ዘቡርልስና አባ ሚካኤል ዘሀገረ አትሪብ በሦስቱ ጉባኤያት የተሰበሰቡ አባቶች የጻፏቸውን ለሰው ልብ እንዲረዳ አድርገው ባጭሩ ጽፈውታል፡፡ ይህም መጽሐፈ ሃይማኖተ አበው በመባል ይታወቃል፡፡ ከዚህም በቀር በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ እንደ ቅ/አትናቴዎስ፣ ቅ/ዮሐንስ አፈወርቅ ወዘተ ያሉ ቅዱሳን አባቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተረጎሙ ጽፈዋል፡፡

◈ የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት በኢትዮጵያ

የመጽሐፍት አንድምታ ትርጓሜ ስልት በሀገራችን መቼ እንደተጀመረ የትና በማን እንደተጀመረ ግልጽ ሆኖ ስለማይታወቅ ያለው አስተያየት ግምታዊ ነው፡፡ይህም፡-

መጻሕፍተ ኦሪት ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ ተተርጉመው ወደ ሀገራችን ሲገቡ የመጻሕፍቱ ጥንታዊ የአንድምታ ትርጉም አብሮ እንደገባ ይታመናል፡፡ ከዚህም ሌላ ከሕገ ኦሪት ጋር

ሊቃውንተ ኦሪት በንግሥተ ሳባ ጊዜ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብረው ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ እነርሱ ሲተረጉሙት ሲያስተምሩት ኑረዋል በማለት አስተያየት ይሰጣል፡፡ በእርግጥም ኦሪት በጥንት ዘመን ተተርጉሞ በሀገራችን ቋንቋ ይሰራበት ነበር የሚለው ታሪክ እውነተኛ እስከሆነ ድረስ ሊቃውንተ ኦሪትም ወደ ሀገራችን መግባታቸውን አምነን ከተቀበለን መጻሕፍትም ሲተረጎሙ መኖራቸው ከቶ ሊያጠራጥረን አይችልም፡፡

በኋላም በዘመነ ክርስትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ከጽርእ ወደ ግእዝ በቀጥታ በተተረጎሙ ጊዜ የአንድምታ ትርጓሜ ስልት የሆኑ መጻሕፍት ሁሉ ሳይተረጎሙ አልቀሩም የሚል አስተያየት ይሰጣል፡፡

ከዚያም አያይዞ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ብዙ መጻሕፍተ ሊቃውንት ሲተረጎሙ የትርጓሜ ስልት የሆኑ መጻሕፍት ሁሉ ሳይተረጎሙ አልቀሩም የሚል አስተያየት ይሰጣል፡፡ ነሐሴ 20 ቀን የሚነበበው ስንክሳር የአንድምታ ትርጓሜ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአባ ሰላማ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነና አባ ሰላማ እንደጀመረው ይተረካል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ጥበባት ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተገለጹለት የመጻሕፍትን ትርጓሜ ሁሉ ያወቀው ወይም የጀመረው እሱ ራሱ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው ሲል ገድሉ ይናገራል፡፡

ይህ አይነት አስተያየት የወል በመሆኑ እንደ እውነት ይቆጠራል እንጂ የትርጓሜውንም መጻሕፍት ቃል በቃል አጥንቶ ወይም ከሰው አግኝቶ ወይም ራሱ ተጣጥሮ እገሌ ደረሰው ጀመረው ስለማይባልና ታሪኩም ከታሪክ ጋር ተያይዞ ስላልመጣ ልብ አኩርቶ አፍን ሞልቶ እንዲናገሩ አያደርግም፡፡

የአንድምታ ትርጓሜ አካል ገዝቶ መልክ አግኝቶ ለመታወቅ የቻለው በጎንደር ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ሊስፋፋ የቻለውም በየጊዜው የተነሡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የተለያዩ መጻሕፍትን በአንድምታ እየተረጎሙ በማቅረባቸው ነው፡፡

ወንጌልን በአንድምታ ተርጉመው ያቀረቡ መምህር ወልደ ሩፋኤልና አለቃ ገብረ መድኅን የተባሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ናቸው፡፡

- አራቱ ወንጌላውያን ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ደግሞ ከአርድዕት መሆናቸው ለምንድነው?
- ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፉ ያላደረገው ሁለቱን ከአርድዕት ያጻፈ ስለምንድን ነው? ቢሉ፡-

ስለክብረ አርድእት፡- ጨርሰው ሐዋርያት ጸፈዋት ቢሆን አርድእት ለማስተማር በወጡ ጊዜ ‹‹እኒህማ የአፍአ ሰዎች ናቸው፡፡ የውስጥማ ሰዎች ቢሆኑ ደጊቱን ሕገ ወንጌል ይጽፉ ነበር፡፡›› ብለው ትምህርታቸውን ከመቀበል በተከለከሉ ነበር፡፡

- አርድእት ብቻ ጨርሰው ያልጻፉት ለምንድን ነው? ቢሉ

ስለ ወንጌል ክብር፡ ጨርሰው ለአርድእት ጽፈውት ቢሆን ይህቺማ ተርታ ሕግ ናት፡፡ ‹‹ድርጊቱን’ምሥጢረ ተአምራቱን በቤተ ኢያኢሮስ’ ምሥጢረ መንግሥቱን በደብረ ታቦር’ምሥጢረ ምጽአትን በደብረ ዘይት’ ምስጢረ ጸሎትን በጌቴሴማኒ ባዩ አዕማደ ምድር በተባሉ በልበ ሐዋርያት ቀርታለች እንጂ፡፡›› እያሉ አይሁድ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከላከሉ ነበር፡፡

ወንጌላውያን አራት የመሆናቸው ምስጢር ምንድን ነው?

ጌታ ከአራት ባሕርያት ወገን የሰራው ብዙ ሥራ አለና በዚያ መስሎ ለመናገር፡፡ በዚያውስ ላይ ‹‹ሥርዓተ ሰማይ ተሰርዓ በዲበ ምድር›› ይላልና፡፡ በሰማይ አራት ጸወርተ መንበር ኪሩቤል አሉ፡፡ እዚህም በአራቱ ወንጌላውያን ይመሰላሉ፡፡ ‹‹ሰማይ ዙፋኑ ምድር የእግሬ መረገጫ›› ይላታል ‹‹እንደም ይሸከሙታል?›› ቢሉ ይሸከማቸዋል እንጂ አይሸከሙትም በዘፈቀደ የሚገለጽባቸው መንበሩን ተሸክው የሚታዩ፣ የሚቀድሱ፣ በጸጋ የሚያድርባቸው ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ የሚሸከማቸውስ እሱ ነው፡፡ ለዚህም ነው እመቤታችንን ‹‹ከኪሩቤል ከሱራፌል ትበልጫለሽ›› ያላት የእሷ መሸከም በረድኤት በጸጋ አይደለም በኩነት እንጂ፡፡

ኪሩቤል ሱራፌልስ ምን ግዘፍ አላቸውና ነው ሰብእ፣ አንበሳ፣ ላህም፣ ንስር ይላቸዋል ቢሉ፣ በዘፈቀደ ያሳየውን ይናገራል ያለ ቢሆን ብዙ አራዊት ብዙ እንስሳ ብዙ አእዋፋት የሉምን? ስለምን በነዚህ ብቻ ያሳያል ቢሉ፡- ግብራቸውን በመልካቸው ለመግለጽ፡፡ አራቱ ሁሉ መገብተ ሰብእ ወአራዊት መገብተ እንስሳ ወአእዋፍ እንደሆኑ ለማጠየቅ፣ ገጸ ሰብእ አእምሮአቸውን፣ ገጸ አንበሳ ግርማቸውን፣ገጸ ሶር(ላህም) ተቀንዮዋቸውን፣ ገጸ ንስር ተመስጧቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

- ማቴዎስ በገጸ ብእሲ ይመሰላል፡- ወልደ ዳዊት፡ ወልደ አብርሃም ብሎ ምድራዊ ልደቱን ስለገለጸ
- ማርቆስ በገጸ አንበሳ ይመሰላል፡- አንበሳ ኑሮው ከሰው እርቆ በምድረ በዳ ነው፡፡ ከዚያ ሆኖ ድምጹን ባሰማ ጊዜ እንስሳት ይገሠጻሉ፣ አራዊት ይደነግጣሉ ማርቆስም ከትምህርት ምድረ በዳ በምትሆን በግብጽ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በመጀመሪያ ባስተማሪ ጊዜ ምእመናን ተገስጸዋል፡፡ አጋንንት መናፍቃን ደንግጠዋል፡፡ አንበሳም ለላህም ጌታዋ ነው ይሰብራታል እሱም ከግብጽ አምልኮተ ላህምን(ጣኦትን) አጥፍቷልና፡፡
- ሉቃስ በላህም ይመሰላል፡- ‹‹የሰባውን ፍሪዳም አምጡና እረዱ እንብላ ደስም ይበለን›› እያለ ምሳሌውን ይጽፋልና፡፡
- ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመሰላል፡- ንስር በእግሩ ይሽከረከራል፣ በክንፉ መጥቆ ይበራል፡፡ በእግሩ እዲሽከረከር፡- እርሱም እንደ ወንድሞቹ የሰው ልጅ ከሰማይ ወረደ ብሎ ይጽፋል፡፡ በክንፉ መጥቆ እንዲበር እርሱም አካል ከህልውና ተገልጸለት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሯልና፡፡ የንስር ዓይኑ ጽሩይ ነው፡ሽቅብ ወጥቶ ረቦ ቁልቁል በተመለከተ ጊዜ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ሥጋም ብትሆን አትሰወረውም፡፡ ያቺን አንሥቶ ይመገባታል፡፡እሱም አካል ከህልውና ተገልጸለት ንጽሐ ሥጋ፡ ንጽሐ ነፍስ፡ ንጽሐ ልቦና ተሰጥቶት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሯልና፡፡

መ. ስለ አራቱ ወንጌላዊያንና ምሳሌዎቻቸው፡-

ወንጌላዊያን በአራቱ አፍላጋት ይመሰላሉ፡፡ ይህንንም በዝርዝር ከዚህ በታች እንመለከተዋለን

ኤፌሶን ፈለገ ሀሊብ/ወተት/ነው፡፡ ማቴዎስ በዚህ ይመሰላል፡፡ በዘር የሚወለዱ የአበውን ልደት ጽፏልና፡፡ ዳግመኛም ሄሮድስ ያስፈጃቸውን የሕጻናትን ነገር ይናገራልና ርስትነቱ ለሕጻናት ነው፡፡

ግዮን ፈለገ ወይን ነው፡- ማርቆስ በዚህ ይመሰላል፡፡ ቅዱስ ዳዊት‹‹ወይን የሰውን ልቡና ደስ ያሰኛል›› ይላል፡፡ ቅብዓ ትሥፍሕት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጥበት በጥምቀት ይጀምራልና፡፡ ርስትነቱም ቢጾሙ ቢጸልዩም ሥራቸውን ደስ ቧቸው የሚሰሩ ሰዎች ርስት ነው፡፡

ጤግሮስ ፈለገ መዓር ነው፡- ሉቃስ በዚህ ይመሰላል፡፡ መዓር ክቡድ ነው፡፡ ሉቃስም ‹‹አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያወቁምና ይቅር በላቸው›› እያለ ክቡድ ነገር ይጽፋልና፡፡ ርስትነቱ ጸዊረ ነገር የሚቻላቸው ሰዎች ነው፡፡

ኤፍራጥስ ፈለገ ዘይት ነው፡- ዮሐንስም በዚህ ይመሰላል፡፡ ዘይት ጽኑዕ ነው፡፡ ‹‹በዓለም ብዙ መከራን ትቀበላላችሁ ነገር ግን ጽኑ እኔ ዓለምን ድል ነሥቼዋሁና›› እያለ ይጽፋልና፣ ዳግመኛም ዘይት ብሩህ ነው የሰውን ልቡና በትምህርቱ ብሩህ ያደርጋልና፣ ዳግመኛም ዘይት አራቱን ሽቶ አዋሕዶ በመዓዛ አንድ ያደርጋቸዋል እሱም ወንድሞቹን በምሥጢር ይበዘብዛቸዋል፡፡ ርስትነቱም የሰማዕታት ነው፡፡

አራቱ ወንጌላውያን በሌሎችም ነገሮች ይመሰላሉ በአራቱ ነፋሳተ ምሕረት፣ በአራቱ መዓዘነ ዓለም፣ በአራቱ ከዋክብት፣ በአራቱ ክፍለ ዘመን፣ በአራቱ የያዕቆብ ሚስቶች እንዲሁም በሌሎች. . .

ሠ. ቅዱስ ማቴዎስ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ማቴዎስ ነው፡፡ እርሱም ቀራጭ ነበር፡፡ ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት የመጠሪያ ስሙ ማቴዎስ ሳይሆን ‹‹ሌዊ›› ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ይኸውም ወንጌላዊ ማርቆስ ስለማቴዎስ ጥንታዊ ስም ሲገልጽ ‹‹በባሕር አጠገብ ሲያልፍ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስ ልጅ ሌዊን አየና ተከተለኝ አለው›› በማለት ‹‹ሌዊ›› በሚል ስም መጠራቱንና የአባቱም ስም እልፍዮስ መሆኑን ጨምሮ ጽፎ ይገኛል፡፡ ማር 2፡14፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ወንጌላዊው ሉቃስም በበኩሉ ስለ ማቴዎስ የመጀመሪያ ስም ሲጽፍ ‹‹ሌዊ የሚባል ቀራጭ በመቀመጫው ተቀምጦ ተመለከተና ተከተለኝ አለው፡፡ ተነሥቶም ተከተለው ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት›› ሲል ስሙንና ስራውን አስፋፍቶ ገልጾአል፡፡ ሉቃስ 5፡2 እንግዲህ ያዕቆብ ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጆች፤ ጴጥሮስና እንድርያስም የዮና ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ማርቆስ ሌዊ፣ ወልደ እልፍዮስ ያለውን ይዘው ማቴዎስ የያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ወንድም መሆኑን የሚገምቱ አሉ፡፡ ማቴዎስ ለሐዋርያነት የተጠራው በዚህ ዓይነት ሲሆን፣ ኋላ ቅዱሳን ሐዋርያት ይህንን ዓለም ወንጌል ለማስተማር በዕጣ ተከፋፍለው በሚሄዱበት ጊዜ ምድረ ፍልስጥኤም ለቅዱስ ማቴዎስ በዕጣ ደርሳዋለች፡፡

ቅዱስ ማቴዎስ ከዚያ ገብቶ ጌታችን ኢየሱስ ከተጸነሰበት ቀን ጀምሮ ወደ ሰማይ እስካረገበት ድረስ ያስተማረውን ትምህርት ያደረገውን ተአምራት ቢያስተምራቸው የፍልስጥኤም ሕዝብ ሁሉ በሕገ ኦሪት የነበሩ ወደ ሕገ ወንጌል፡ በአምልኮ ጣዖት የነበሩ ደግሞ ጣዖቶቻቸውን እየሰበሩ አብያተ ጣዖቶችንም እየመዘበሩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው ተጠመቁ፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ በዚህ ሳይወሰን የወንጌል ትምህርት ወደ አልደረሰባቸው አገሮች ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

ለምሳሌ፤ ፋርስ ባቢሎን፡ ኢትዮጵያንም እንዳስተማረ በታሪክ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ ሀገረ ይሁዳንና ፍልስጥኤምን እንዳስተማረ አውሳብዮስ የተባለ ሊቅ ጽፏል፡፡ ወንጌላዊው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን ማስተማሩን የሚገልጹት እነ አውሳብዮስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ታሪኮች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በዓረብኛ ቋንቋ ተጽፎ የታተመና ስንክሳር የተሰኘው መጽሐፍ የሚከተለውን ቃል አስፍሮ ይገኛል፡፡ ‹‹ወንጌላዊው ማቴዎስ ለማስተማር በታዘዘው መሠረት የወንጌልን ትምህርት በፍልስጥኤም ለሚኖሩ ሕዝብ ካስተማራቸውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳምኖ በስሙ ካጠመቃቸው በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ይልና ከኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት በትግራይ ክፍለ ሃገር ያስተማረ መሆኑን ይገልጻል፡፡››(ገጽ 76)

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 71 ከቁጥር 9-11 ላይ ‹‹የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፡ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ›› ሲል በትንቢቱ እንደተናገረ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የተባሉት ከፋርስና ከባቢሎን የመጡ መሆናቸው ይነገራል፡፡ እንዲህ ሲል የኢትዮጵያን ስም ጠርቶ መናገሩ ራሱ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩልም ሰብአ ሰገልን ከማቴዎስ በቀር ሌሎች ወንጌላውያን አያነሷቸውም፡፡ ይህም ማቴዎስ የሰብአ ሰገልን ታሪክ፡ ከየት እንደመጡ፡ ወደየት እንደሚሄዱ፡ ምን አይነት ሥራ ሰርተውም ወደ ሃገራቸው እንደተመለሱ በሰፊው መግለጹ እርሱ በነዚህ ሃገራት ማስተማሩን ይገልጻል፡፡

ማቴዎስ የጻፈውን ወንጌል አተኩረን ስንመለከተው ለአይሁድ በአይሁድ እምነት ለነበሩ ሕዝብ የጻፈው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ጠቅሷቸው የሚገኙት ቃላት ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ናቸው፡፡ ወንጌሉንም የጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን አጻጻፍም በአይሁድ ሕግና ሥርዓት ወይም ወግ መሠረት ነው፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት አይሁድ ምክንያት ፈላጊዎች መሆናቸውን ስለሚያውቅ ሕጋቸውን ወይም ወጋቸውን ቢያፈርስ /ባይከተል/ ሕጋችንን አፈረሰ ወጋችንን አበላሸ በማለት ወንጌልን አንቀበልም እንዳይሉ ነው፡፡

ማጠቃለያ

ወንጌላዊው ማቴዎስ ሂዳችሁ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝና መንፈሳዊ ተልእኮውን ለመፈጸም እየተዘዋወረ ወንጌልን ሲያስተምር ከቆየ በኋላ፣ ጥቅምት 12 ቀን በመጀመሪያው ምእተ ዓመት በሰማዕትነት እንዳለፈ የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡ በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ ጥቅምት 12 ቀን በዓለ ዕረፍቱን ታከብራለች

# የማቴዎስ ወንጌል

## *ምዕራፍ አንድ*

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው፡፡

ይህ በማቴዎስ ወንጌል መጀመሪያ ላይ የተጻፈው ጽሁፍም ሆነ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚገኙ ተመሳሳይ ጽሁፎች የተጻፉት በሠልስቱ ምዕት ነው፡፡ እነዚህ አባቶች አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ በ325 ዓ.ም በተሰበሰቡበት ጊዜ ከሰሯቸው አያሌ ስራዎች ውስጥ አንዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ላይ ተጠርዞው ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት በእነማን እነደተጻፉ መለየት ነበር በመሆኑም ‹‹የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ መቴዎስ እንደጻፈው›› ብለው የማቴዎስ ወንጌል ጸሐፊ ማን እንደሆነ ገለጹልን፡፡

ማቴ1፡1፡- ‹‹የዳዊት ልጅ የአብህርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ››

ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው ከ42 አዕማድ (ሐረግ) ትውልድ እንደሆነ በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 2 እስከ ቁጥር 16 ተጠቅሶ እናገኘለን፡፡ እንዲያውም ከቁጥር 17 ላይ ‹‹እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አስራ አራት ትውልድ፤ ከዳዊቲም እስከ ባቢሎን ምርኮ አስራ አራት ትውልድ፤ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አስራ አራት ትውልድ ነው›› በማለት እነዚህን 42 አዕማድ ትውልድ ይገልጽልናል፡፡ ከነዚህም አዕማድ ትውልድ ውስጥ አብርሃምና ዳዊት ይገኙበታል፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ሁሉ አባቶች (ትውልድ) ተለይተው (በተናጠል) አብርሃምና ዳዊት ብቻ ለምን ተጠቀሱ;

ከ42 አዕማድ ትውልድ ለይቶ አብርሃምን እና ዳዊትን ለምን ጠቀሳቸው ቢሉ፡-

አብርሃም ሥርወ ሃይማኖት ዳዊት ሥርወ መንግሥት ናቸውና አይሁድ እግዚአብሔር ፈጣሪቸውንአብርሃም አባታቸውን ዳዊት ንጉሣቸውን ሲያነሱላቸው ይደሰታሉና (ዮሐ 7÷39)

አንድም፡- ዳዊት እና አብርሃም በአይሁድ ዘንድ እጅግ ተፈቃሪዎችና ተከባሪዎች በመሆናቸው ቅዱስ ማቴዎስም ወንጌሉን በአብርሃምና በዳዊት ጀምሮላቸው (ጽፎላቸው) አይሁድ በቶሎ እዲቀበሉትና እንዲያነቡለት ነው፡፡

አንድም፡- ተስፋን ከተስፋ ለማነጻጸር

ለአብርሃም፡- ‹‹በዘርእከ ይትባረኩ ኩሎሙ አሕዛበ ምድር››ይህም ማለት ‹‹በዘርህ የምድር ነገዶች (ሕዝቦች) ሁሉ ይባርካሉ›› ተብሎ ተነግሮለት ነበርና፡፡ (ዘፍ12÷3)

ለዳዊት፡- ‹‹እስመ አምፍሬ ከርስከ አነብር ዲበ መንበርከ›› ማለትም ‹‹ከአብራክህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ፡፡›› ተብሎ ተስፋ ተሰጥቷቸው ነበርና፡፡

አንድም፡- ትንቢት የተነገረ ለኒህ ነውና

ትንቢትማ፡- ከነገስታት ለሰሎሞን ‹‹እነ እከውኖ አባሁ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ›› ተብሎ ከአበውም ለሴም ‹‹ለይኀድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም›› ተብሎ ተነግሮ የለምን ቢሉ አብዝቶ የተነገረ ለሁለቱ ብቻ ነውና፡፡

አንድም፡- (በሌላ በኩል) ያላመኑ አይሁድ ያመኑትን አይሁድ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ነው ስለማለታችሁ ትውልዱን ቆጥራችሁ አሳዩን ብለዋቸው ነበርና ቅዱስ ማቴዎስ ትውልዱን ዘርዝሮ ጽፎላቸዋል፡፡

በዚሁ ቁጥር ላይ ‹‹የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ …..›› ይላል

አብርሃምን አያስቀድምምን? ዳዊትን አያስከትልምን? ዳዊትን ለምን አስቀደመ? ቢሉ

‹‹አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቀ›› ይሉኛል ብሎ ለክርስቶስ ቅርብ የሆነውን ዳዊትን አስቀደመ

አንድም፡- በቁጥር 2 ላይ ‹‹አብርሃም ይስሐቅን ወለደ ……›› ስለሚል አብርሃምን ይዞ ለመሄድ

እንዲያመቸው አብርሃምን አስከትሎ (ዳዊት) ጠቀሰው

አንድም፡- ከአባትነት ንጉሥነት ይበልጣልና

‹‹የዳዊት ልጅ›› የሚለው ለጌታ ጥቅል ስሙ ነው፡፡ በእለተ ሆሳዕና ሕጻናት ዘንባባ ይዘው ‹‹ሆሳህና በአርያም ለዳዊት ልጅ …..›› እያሉ ማመስገናቸው ይህን እና የዳዊትን በአይሁድ ዘንድ ያለውን ተፈቃሪነት ይገልጻል፡፡ (ማቴ 21÷9)

‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ››

**የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደቱን ታሪክ የሚናገር መጽሐፍ**

አንድም፡- ስለ ክርስቶስ የዘር ሐረግ፣ ስለነገረ ልደቱ የሚያወራ መጽሐፍ ማለቱ ነው እንዲህ ማለቱም የጌታችንን ልደት ከሌሎች ልደታት ለመለየት ነው፡፡ሌሎች ልደታት የሚባሉት እነማን ናቸው ቢሉ

ሀ. ልደተ አዳም እምድር /የአዳም ከምድር መወለድ (መገኘት)

ለ. ልደት ሔዋን እሞገቦ /የሔዋ ከአዳም ጎን መወለድ (መገኘት)

ሐ. ልደተ አቤል እሞከርስ /የአቤል ከሔዋን ማህጸን መወለድ/

መ. ልደት በግዕ እምዕፅ /የበግ ከዕፀ ሳቤቅ መገኘት ዜና

ሠ. ልደተ ሙታን እመቃብር /የሙታን ከመቃብር መነሣት

የጌታ ትንሣኤ ግን ይለያል ሰዎች አሥነሽ ይሻሉ እርሱ ግን በስልጣኑ ተነሥቷል፡፡ከእነዚህ ልደታት ሲለይ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ ብሎ ጻፈ እነዚህ አውጪ (አስገኚ) ይፈልጋሉ እርሱ ግን በገዛ ስልጣኑ ተወልዷልና እንዲህ አለ፡፡

**የሰው ልጆች፡-** በጥምቀት ስንወለድ ውሉደ እግዚአብሔር፣ውሉደ ጥምቀት፣ውሉደ ቤተ ክርስቲያን እንባላለን፡፡ከሥጋ አባቶቻችን ስንወለድ ውሉደ አዳም፣ውሉደ አብርሃም፣ ውሉደ እገሌ እንባላለን፡፡

**መነኮሳት መናኒያን፡-** በቆብ አባታቸው በጥምቀት ውሉደ እንጦንስ ወመቃርስ፣ውሉደ ተክለ ሃይማኖት ወገብረ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ

**የጥፋት (የክፋት) ልጆች ደግሞ፡-** ውሉደ ሰይጣን፣ውሉደ ዲያቢሎስ፣ውሉደ ሞት ይባላሉ፡፡

‹‹ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ››

ዋናው መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ነገር የያዘ ሆኖ ሳለ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ›› አለ ቢሉ፡- በመጽሐፍ በአንድ መጀመር ኋላ ብዙ ማምጣት ልማድ ነውና፡-

ምሳሌ፡- ኦሪት ዘልደት የሥነ-ፍጥረትን ነገር ብቻ ተናግሮ ይቀራልን እንዲሉ

**ማቴ 1፡2 ‹‹ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ ››**

ታሪክ፡-የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ብቻ አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን የአብርሃም ታሪክ ስናነብ አብርሃም አጋር ከምትባው ሠራተኛው እስማኤልን (ዘፍ 16÷1-15) ሕጋዊት ከሆነችው ሚስቱ ከሳራ ደግሞ ይስሐቅን (ዘፍ 21÷1) እንዲሁም ሳራ ከሞተች በኋላ ከኬጡራ ዘፍራን፣ ዮቅሳን፣ሜዳን፣ሞድያም፣የሰቦቅ እና ሰዌሕን የተባሉ 6 ልጆችን ወልዷል፡፡(ዘፍ 25 ÷1-) በአጠቃላይም አብርሃም ስምንት ልጆች ነበሩት፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የተነሣው ይስሐቅ ብቻ የሆነበት ምክንያቱ (ምስጢሩ) ምንድን ነው ቢሉ፡-

የጌታ ልደቱ ከይስሐቅ ነው እንጂ ከሌሎቹ አይደለምና

አንድም ፡- ትቢቱን ምሳሌውን ለመፈጸም፡፡

ትንቢቱ እንደምን ነው ቢሉ፡

ዘፍ 26÷4 **‹‹ዘርህንም እንደ ሰማይ ክዋክብት አበዛዋለሁ እነዚህንም ምድሮች ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ የምድር አህዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ››** ዘፍ 21÷12 **‹‹በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል››**

ምሳሌውስ እንደምን ነው ቢሉ፡-

ይስሐቅ ለመሰዋት (መስዋዕት ሆኖ) መቅረቡ ለክርስቶስ መስዋዕትነት ምሳሌ ነው፡፡

ሐተታ፡- እግዚአብሔር አምላክ አብርሃምን ‹‹በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል›› ብሎታል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጁን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ ከሞት እንኳ እንደሚያስነሣለት በማመን ባለማንገራገር ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ለማረብ እንከመጨረሻው ታዛዥ ሆነ፡፡ በዚህም ታማኝነቱን አሳየ በልጁም ፈንታ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ የነበረው በግዕ ተሰዋ፡፡ (ዘፍ 22፣ዕብ11÷17-19)

ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው፡-

ይስሐቅ የክርስቶስ ምሳሌ፣ ሕሊና አብሃም የመቃብር ምሳሌ ክርስቶስ በከርሰ መቃብር ሦስት መዓልትና ሶስት ሌሊት አድሮ እንደተነሣ ይስሐቅም በሕሊና አብርሃም ሞቶ ተነሥቷልና፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፡-ይስሐቅ የዓለም(የአዳም ልጆች)፣በግዕ የክርስቶስ፣ዕፀ ሳቤቅ የእመቤታችን ምሳሌ ነው፡፡

በግዕ በይስሐቅ ፈንታ እንደተሠዋ ክርስቶስ ስለ ዓለሙ ሁሉ ቤዛ ሆኖ የመሠዋቱ ምሳሌ፣ መሥዋዕት የሆነው በግዕ ከዕፀ ሳቤቅ እንደተገኘ እንዲሁ አማናዊቷ ዕፀ ሳቤቅ እመቤታችንም ‹‹የዓለሙን ሁሉ ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ እንሆ›› (ዮሐ 1÷29) ተብሎ በቅዱስ ዮሐንስ የተነገረለትን አማናዊውን በግዕ ክርስቶስን በማሕፀኗ ጽንስ ተሸክማ ተገኝታለችና በጉ ከአብርሃም መንጋ የተገኘ ነው ቢባል ጌታ ከቤተ አብርሃም መወለዱን ይጠይቃል (ያሳያል)፡፡ ከየት እንደሆነ አልታወቀም ቢባል የጌታ ቀዳማዊ ልደቱ እንደማይታወቅ እንደማይመረመር ያሳያል፡፡

**‹‹ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ ››**

ታሪክ፡-ይስሐቅ ከሚስቱ ከርብቃ የወለዳቸው መንትዮቹ ያዕቆብና ኤሳው እንደሆኑ ከታሪኩ እንረዳለን፡፡ ስምንቱ የአብርሃም ልጆች በእናት እና በልደት ቀን ይለያያሉ እኚህ ግን በአንድ ቀን ተጸንሰው በአንድ ቀን ተወልደው ሳለ፤እንዲሁም ሆኖ ታላቅየው ኤሳው እያለ ያዕቆብን ብቻ ለምን ጠቀሰው?

ትንቢቱን ምሳሌውን ለመፈጸም

ትንቢቱ እንደምን ነው ቢሉ፡-

‹‹ **ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፡፡ ከእስራኤልም ኃጢትን ያስወግዳል**›› (ዘኁልቁ 24÷17)

ምሳሌውስ

ታሪክ፡-ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ተጣልቶ ወደ እናቱ ወንድም (አጎቱ) ወደ ላባ ዘንድ ሲሄድ ከአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ይደርሳል፡፡ ጉድጓዱም ጠላት መርዝ እንዳይጨምርበት በግዙፍ ድንጋይ ተከድኖ በጎችና እረኞች ተሰብስበው ያገኟቸዋል፡፡ ያዕቆብም በጎቹን ለምን አታጠጧቸውም ብሎ እረኞቹን ጠየቀ፡፡ እረኞቹም መላው ኖሎት (እረኛ) እስኪሰበሰብ እንጠብቃለን ከዚያ በኋላ ድንጋዩን አንሥተን እናጠጣቸዋለን አሉት፡፡ ኋላም የአጎቱ የላባ ልጅ ራሔል በመጣች ጊዜ ያን ግዙፍ ድንጋይ ብቻውን አንሥቶ ከውሃው እንዲጠቀሙ አድርጓል፡፡

ይህም ምሳሌ ነው፡-

ያዕቆብ የጌታ፣ድንጋዩ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፣በጎቹ የምእመናን ፣እረኞቹ (ኖሎት) የነቢያት የካህናት፣ውኃው የጥምቀት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ያዕቆብ ያን ግዙፍ ድንጋይ አንሥቶ እረኞች በጎቻቸውን እንዲያጠጡ እንዳደረገ ጌታም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍሳችን የሚወገድበትን ጥምቀት በካህናት አባቶቻችን አማካኝነት እንድናገኝ የመሠረተልን መሆኑን ያስረዳል፡፡

አንድም፡- የጌታ ልደት ከያዕቆብ እንጂ ከዔሳው አይደለምና፡፡

**‹‹ያዕቆብም ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ››**

ታሪክ፡- ያዕቆብ የአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት መሆኑ ይታወቃል፡፡የይስሐቅን ልደት ሲናገር ሌሎቹን ሰባት  የአብርሃም ልጆች አልጠቀሰም የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜም ዔሳውን አላነሳም ከዚህ ደርሶ ስለምን ይሁዳን ከወንድሞቹ ጋር አነሣ አስራ አንዱ የያዕቆብ ልጆች ‹‹ወንድሞቹ›› በሚለው ቃል መጠቃለላቸው ስለምን ነው? ይሁዳን ብቻ ስለምን በስም ተጠቀሰ ቢሉ፡-

ይሁዳና ወንድሞቹ የሚለው የሚገልጸው አስራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ነው ብለናል ይኸውም ክርስቶስ የቤተ እስራኤል ከሆኑት ከአስራ ሁለቱ ነገድ መወለዱን ለማመልከት ነው፡፡

አንድም፡- ከአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተወለዱ ምድረ ርስተ ከነዓንን እንደወረሱ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያትን ትምህርት ያመነ እና የተቀበለ ርስተ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚወርስ ለማሳየት፡፡ አስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች የአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ምሳሌ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

አንድም ነቢይ ቢሆን አባቶቻችን ከቁጥር አይለያቸውም ነበር፡፡ ወንጌላዊው ስለምን ተዋቸው ብለው አይሁድ ደገኛይቱን ወንጌል ከመቀበል እንዳይከለከሉ

ይሁዳን በስም መጥቀሱ

ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ

ትንቢቱ ምንድን ነው ቢሉ ‹‹**በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም**›› (ዘፍ 49÷10)

ምሳሌውስ ቢሉ፡- በቀጣዩ ቁጥር (ቁጥር 3) ተጠቅሷል

**ማቴ 1፡3 ‹‹ይሁዳም ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ››**

የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ ሳራን፣የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ርብቃን፣ የይሁዳና የወንድሞቹን ልደት በተናገረ ጊዜን ልያንና ራሄልን ሳላነሳም፡፡አሁን ግን ትዕማርን ለምን አነሣት ቢሉ ወንጌላዊው ትዕማርን የጠቀሰበትን ምክንያት ለመረዳት በኦሪት ዘፍ 38 ላይ ያለውን ታሪክ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የትዕማር መነሣት እዚያ ላይ በተጠቀሰው ታሪክ ምክንያትነት ነውና፡-

ታሪክ፡- ይሁዳ ሴዋ የምትባል ሚስት አግብቶ ዔር፣አውናንና ሴሎም የተባሉ ሦስት ወንዶች ልጆች ወለደ፡፡ ለበኩሩ ለዔር ትዕማር የምትባል አስተዋይ የሆነች ነገር ግን ከአህዛብ ወገን የምትሆን ሴት አጋባው፡፡ ‹‹አባቴ የኔን ማግባት ባይፈቅድ እንጂ ቢፈቅድማ ከምርጦቹ ከነያላኑ ከእስራኤል ወገን ያጋባኝ አልነበረምን?›› ይህን ብሎ አህዛብነቷን ተጸይፏት የማይደርስባት ሆነ ይህ ትዕቢቱም በእግዚአብሔር አልተወደደለትምና ተቀሰፈ፡፡ እግዚአብሔር ትዕቢትን አይወድምና ቀሰፈው ሞተ፡ይሁዳም ኋላ በሕገ ኦሪት የሚሆነው በሕገ ልቡና ተገልጾለት ለታናሹ ለአውናን ‹‹ለወንድምህ ዘር ተካለት›› ብሎ ትዕማርን አጋባው አውናንም ‹‹ልጅ ቢወልድ ለእርሱ ለስሙ መጠሪያ ይሆነዋል እንጂ ለእኔ ምን ይጠቅመኛል ብሎ እንደወንድሙም ክፉ አደረገ እግዚአብሔርም ምቀኝነትን አይወድምና ቀሰፈው ሞተ፡፡በዚህ ጊዜ ይሁዳ ትንሹ ልጁ ሴሎምም ይሞትብኛል ብሎ ትዕማርን ‹‹ወደ አባትሽ ቤት ሂደሽ ተቀመጪ›› ልጅ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ብሎ በብልጠት (በፈሊጥ) ወደ ዘመዶቿ ላካት፡፡ ትዕማር እዘነች ሂደች ማዘኗ ዝሙት ቀረብኝ ብላ አይደለም እመቤታችንና ጌታችን በቤተ ይሁዳ ይወለዳል ሲባል ትሰማ ነበርና እንዴት ከባለ ተስፋ ቤት ወጥቼ ሄዱኩ ብላ ነው እንጂ፡፡

በዚያ ወራት ይሁዳ ሚስቱ ሴይ ሞተችበት መዋዕለ ኀዘኑ ሲፈጸም ቴምናታ ወደምትባል ሀገር በጎቹን ሊያሸልት ሄደ፡፡ ቴምናታ የትዕማር ቤተሰቦች የሚኖሩበት ሃገር ነበረች፡፡‹‹አማትሽ ይሁዳ በጎቹን ሊያሸልት ወደ ቴሞናታ መጥቷል›› ብለው ለትዕማር ነገሯት እሷም ይሁዳ የገባላትን ቃል እንዳልፈጸመላት፣እንዳታለላት ባየች ጊዜ እንዳታለለኝ እኔም ላታለው ብላ ልብስ ዘማ ለብሳ፣ጀንጥላ አስጥላ(ድንኳን አስተክላ ቢሉም ያስኬዳል)፣ከተመሳቀለ (ከመስቀለኛ) መንገድ ቆየችው ይሁዳም በጎቹን አሸልቶ (ሸልቶ) ሲመለስ ከዚያ ከተመሳቀለ መንገድ ደረሰ እስራኤላውያን ሴት ሲያዩ አልፎ መሄድ አይሆንላቸውምና በዚያም ላይ ሚስቱ ሞታበት ነበርና የልጆቹ ሚስት (ምራቱ) መሆኗን አላወቀም ነበርና፡፡ ‹‹በጄ በይኝ›› አላት›› ‹‹ምን ትሰጠኛለህ?›› አለችው ‹‹የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ›› አላት ‹‹መያዣ ስጠኝ›› አለችው ‹‹ከዚህ ምን አለኝና ምን ልስጥሽ (ላስይዝ)›› አላት ‹‹ቀለበትህን፣ኩፌትህን፣ዘንግህን›› ስጠኝ አለችው ይሁዳም መያዣውን ሰጥቶ የሚፈልገውን ፈጽሞ ሄደ፡፡ እሷም (ትዕማርም) ዘማ አይደለችምና እንደጥንቷ ተቀመጠች፡፡

ይሁዳም ሀገሩ ከገባ በኋላ በውሉ መሰረት የፍየል ጠቦቱን አስይዞ መልዕክተኛውን (ሹሙን) ኤራስ ኤዶሎማዊን፡-ይህን ጠቦት ወስደህ ለዚያዝ ዘማ ሰጥተህ ገንዘባችንን ይዘህ ና›› ብሎ ላከው ኤራስ ኦዶሎማዊም የተባለው መንገድ ሲደርስ ያችን ዘማ አጣት፡፡‹‹የዘማይቱ ቤት ወደየት ነው?›› እያለ ሲዞር ‹‹እኛስ በሀገራችን ዘማም የለብንም›› ብለው ተሳለቁበት ኤራስ አዶሎማዊም ወደ ይሁዳ ተመልሶ ‹‹አጣኋት›› አለው፡፡ከ 3 ወራት በኋላ ‹‹ትዕማር መርዓትከ ጸንሰት በዝሙት›› ብለው ነገሩት በምን አወቁና ቢሉ ከ3 ወር በኋላ ጽንስ እየገፋ ጡት እየጠቆረ፣ይሄዳልና በዚህ አወቁ ይሁዳም በአሕዛብ ላይ ሰልጥኖባቸው ነበርና፡፡‹‹በድንጋይ ወግራችሁ፣ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት›› አላቸው (አዘዛቸው) ትዕማርም ‹‹ከይሁዳ ዘንድ አድርሱኝ›› አለቻቸው፡፡አይሆንም አናደርስም አሏት ‹‹እንግዲያውስ ይህ ቀለበት የማን ነው? ይህ ኩፌት የማን ነው? ይህ ዘንግ የማን ነው? ብላችሁ ስጡት አለቻቸው፡፡ ወስደው ለይሁዳ ሰጡት ደነገጠ ከእርሱ እንደጸነሰች ተረዳ፡፡‹‹ትዕማር ረታችኝ ከእኔ ይልቅ ተሻለች ከእኔ የተነሣ ከበረች›› አለ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ መንታ እንደጸነሰች አውቃ ነበርና ለአዋላጅቷ ‹‹ቀድሞ የሚወለደውን (በኩሩን) እንድናውቀው ቀይ ሐር እሰሪበት›› አለቻት በልደታቸውም ጊዜ ዛራ አስቀድሞ እጁን አወጣ አዋላጅቱም ቀይ ሐር አሰረችበት፡፡ ነገር ግን ፋሬስ ወንድሙን ዛራን ወደኋላ ስቦ ጥሶ አስቀድሞ ወጣ (ተወለደ)፡፡ፋሬስ ማለት ‹‹ጣሽ፣ ደምሳሽ፣ ፍልጠት፣ ኃያል›› ማለት ነው እንዳንተ ድንቅ ዕፁብ›› ማን ነው? ያየነው ቀርቶ ያላየነው ወጣ ማለት ነው፡፡ዛራ ማለት ደግሞ ድኩም ማለት ነው፤ ደክሞ (ተጎትቶ ተሸንፎ) ተወልዷልና ቀድሞ አይቶነው ወደ ኋላ ቀርቶ የተወለደ ማለት ነው፡፡

ታሪኩ እንደተገለጸው ነው ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው፡-

ይሁዳ የእግዚአብሔር አብ፣መልእክተኛው የቅዱስ ገብርኤል፣ ጠቦቱ እግዚአብሔር ወልድ፣ ቀለበቱ የሃይማኖት፣ኩፌት(አንባር) የአክሊል ሦክ፤ ዘንግ (በትር) የመስቀል፣ትዕማር የቤተ አይሁድ፣ ፋሬስ የኦሪት፣ዛራ የወንጌል ምሳሌ ናቸው፡፡

ትዕማር ማስያዣውን ይዛ ቀረች እነጂ ዋጋን ጠቦቱን እንዳላገኘች ቤተ አይሁድም ትንቢት ቢነገርላቸውም ሱባኤ ቢቆጠርላቸውም ተስፋ ቢሰጣቸውም ትንቢቱን ተስፋውን ሰምተው ቀሩ እንጂ በክርስቶስ አላመኑም፡፡

አንድም፡- ትዕማር የምኩራብ (የቤተ ክርስቲያን) ምሳሌ

ትዕማር ልጆችን ከአባታቸው ከይሁዳ እንጂ ከልጆቹ እንዳላገኘች ቤተ ክርስቲያንም ምዕመናንን ከእግዚአ ነቢያት፣ ከእግዚአ ካህናት ከክርስቶስ አገኘች እንጂ ከነቢያት ከካህናት አላገኘችምና

ትዕማር ዘርን ከልጆችም ከአባትም ፈለገች እንጂ እንዳልተጠየፈች ቤተ ክርስቲያንም ከሕዝቡ፣ከአሕዛብ፣ ከግዙር ከቆላፋ ያመኑትን ሁሉ ተቀብላለች (ትቀበላለች)

ጌታም በመዋዕለ ስጋዌው፡-‹‹ወደ እኔ የመጣውን (ያመነብኝን) ከቶ ወደ ውጪ አላወጣውም›› (ዮሐ 6÷37) ያለው ይህን ያመለክታል፡፡

አንድም፡- የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ዔሳውን አልጠቀሰም ነበር፡፡ አሁን ግን ፋሬስ እና ዛራ በአንድነት መጠቀሳቸው ስለምንድን ነው? ቢሉ፡- ፋሬስና ዛራ ምሳሌነት ስላላቸው ነው፡፡

ፋሬስ የኦሪት ዛራ ደግሞ የወንጌል ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ዛራ እጁን አውጥቶ መመለሱ ወንጌል በመልከ ጼዲቅ ታይታ የመጥፋትዋ ምሳሌ ነው፡፡ (ዘፍ 14÷17) ፋሬስ ጥሶ እንደወጣ በመሃል ኦሪት ተሠርታለች፤ ዛራ ሁለተኛ እንደመወለዱ ወንጌልም ቆይታ ተሠርታለችና

አንድም፡- እደ ዛራ የቀሳውስት (የካህናት)፣ቀይ ሀር የሥጋ ወደሙ ምሳሌ፡፡

በዛራ እጅ ቀይ ሐር እንደታሠረ ሥጋ

ወደሙ በካህናት እጅ ይፈተታል፡፡

አንድም፡- የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ ሳራን፣ የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ርብቃን፣ የይሁዳንና

የወንድቹን ልደት በተናገረ ጊዜ እነ ልያንና ራሄልን ሳይጠቅስ አሁን ትዕማርን የመጥቀሱ ምስጢር ምንድን ነው? ቢሉ

ለትዕማር መጠቀስ ምክንያቶች ሆነው የሚቀርቡት፡-

አይሁድ ሥርዓት የዘር ሐረግ ሲቆጠር ሴቶች አይቆጠሩም ነበር በመሆኑም ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ለዕብራውያን ነበርና በእነርሱ ሥርዓት (ሥርዓታቸውን ሳያጠፋ) ዕብራውያን የሆኑ ሴቶችን አልቆጠረም (አልጠቀሰም) ትዕማር ግን ዕብራዊ ሳትሆን ከአሕዛብ ወገን ስለሆነች ተቆጥራለች (ተጠቅሳለች)፡፡

አንድም፡- ክርስቶስ ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም እንደመጣ ለማመልከት

አንድም፡- በእስራኤል ዘለፋ ለአሕዛብ ተስፋ ለመሆን፡፡ እስራኤል በልደተ ሥጋ (በዘር) ይመካሉና (የአብርሃም የይስሐቅ ዘር እኛ ነን እያሉ) አሕዛብ ክርስቶስ ከእኛ ዘር ከትዕማርስ አልተወለደምን ብለው ተስፋ እንዲያገኙ ትዕማር በዘር ሐረግ ተቆጥራለች፡፡

ማቴ 1÷4፡- እዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት አባቶች በመጽሐፍ ቅዱስ በቂና የተብራራ ታሪክ ስለሌላቸው ነጠላ ትርጉሙ ይነበብ ፡፡

ማቴ 1÷5 ‹‹ሰልሞንም ከራኬብ ቦዔዝን ወለደ››

ታሪክ፡-የሰልሞን የራኬብንና የቦዔዝን ማንነት ማወቅ ኃይለ ቃሉን ለመተርጎም ይጠቅማልና ከዚህ ላይ ታሪካቸውን እናነሳለን፡፡ በመጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተጠቀሰው እስራኤል በኢያሱ መሪነት ወደ ምድረ ርስት ሲጓዙ ስጢን የተባለ ቦታ አርፈው ሳለ ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን ኢያሪኮን እንዲሰልሉ በስውር ላከ፡፡ እነዚህ ሰላዮች ሰልሞንና ካሌብ ነበሩ፡፡ እነርሱም ደጋ ደጋውን ሲሰልሉ አድረው ከኢያሪኮ ቆላ ሲደርሱ ነጋባቸው፡፡ አሕዛብም አይተው አወቋቸው፡፡

እንደምን አወቋቸው ቢሉ፡-

የሰላይ (የጉበኛ) ዓይኑ ባካና ነውና ዓይናቸው ወዲህና ወዲያ ፈራ ተባ እያለ ሲባክን ተመልክተው

አንድም፡- በልባቸው በአካላቸው፡፡እስራኤል ልባሳቸው ነጭ አካላቸውም ቅርጸ ቀላል ነውና አሕዛብ ግን ቁመተ ገፋፋ ልብስ አዳፋ ናቸውና፡፡

ስለሆነም አሳደዷቸው ወደ አንዲት ጋለሞታ ወደ ሆነች ረዓብ (ራኬብ) የምትባል ሴት ይገባሉ፡፡ ገብተው ሰውሪን አሏት፡፡ ራኬብም ሸሽገቻቸውና ከኢያሪኮ ንጉሥ እጅ እንዲያመልጡ አደረገች፡፡ ‹‹እስራኤል ጉበኞች (ሰላዮች) ከአንቺ ዘንድ ገብተዋል ስጪን አሏት እሷም ‹‹መግባትንስ ገብተው ነበር እህል ቀምሰው ውሃ ጠጥተው ሄዱ›› ብላ በዘዴ የጣለችውን ፍርፋሪ የደፋችውን ውሃ አሳየቻቸው መግባታቸውን ብታምንላቸው መውጣታቸውን አምነውላት ‹‹ገብተን እንይ (እንፈትሽ)›› ሳይሉ ተመልሰው ሄዱ፡፡ራኬብም ወደ ካሌብና ሰልሞን ተመልሳ‹‹ሀገራችን ትወርሳላችሁ ነገሥታቶቻችንንም ትገድሉ የለምን?›› አለቻቸው‹‹በምን አወቅሽ?›› አሏት ‹‹ኃያላኑ ሲፈሩ ሲሸበሩ ያድራሉ በ50 በ60 የሚከፈተው የብረት ሳንቃ ‹‹እንዲዚህ እንከፈታለን እያለ በገዛ ራሱ ይከፈታል፡፡ አሕዛብ ተድላ ደስታ ሲያደርጉ እኔ አላደረኩምና ኢያሪኮን ለመያዝ ስትመጡ ጨምራችሁችሁ እንዳታጠፉኝ ማሉልኝ›› አለቻቸው፡፡እነርሱም ኢያሪኮን በያዙ ጊዜ ከነቤተሰቧ ሊያድኗት ተስፋ ሰጡዋት መላያ ይሆን ዘንድም በመስኮቷ ላይ ቀይ ሐር እንድታስር አስጠነቀቋት፡፡ የሆነውን ሁሉ ለኢያሱ ነገሩት፡፡ ሰንደቅ ዓላማ እንድትሰቅል እስራኤል አሕዛብን አጥፍተው ኢያሪኮን በያዘ ጊዜ ሰልሞን ከራኬብ ደጅ ጦሩን አቆመ ለኢያሱም ‹‹ያልኩህ ሴት ይህች ናት›› አለው ኢያሱም ‹‹ባርኬልሃለው አግባት ልጅም ትውለድልህ›› አለው ሰልሞንም ራኬብን (ረዓብን) አግብቶ በዔዝን ወለዱ፡፡

ራኬብን በኦሪት ረዓብ ዘማ ይላታል ይህ እንደምን ነው ቢሉ ለአንድ ሰው ሁለት ስም እንዳለው እንዲሁ በሁለቱም ትጠራ ነበርና፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ ሁሉ ምሳሌ ነው

ኢያሱ  የጌታ፣ኢያሪኮ የምዕመናን፣አህዛብ የአጋንንት

ኢያሱ አህዛብን አጥፍቶ ኢያሪኮን እንደያዘ ጌታም አጋንትን አጥፍቶ ምዕመናንን እጅ አድርጓልና መስኮት  የከናፍረ ምእመናን፣ሐር  የሥጋ ወደሙ፣ሰንደቅ አላማ  የመስቀል፣ራኬብ የአሕዛብ ራኬብ በመስኮቷ በሰቀለችው ሐርና በደጇ በተከለችው ሰንደቅ ዓላማ ምልክትነት ከጥፋት እንደዳነች አሕዛብም በመስቀል በተሰቀለላቸው የአምላክ ሥጋ እና ደም ከክፋት ይድናሉና ራኬብ ብዙ ወንድ ስታስገባ ስታስወጣ ኖራ ኋላ በአንድ በሰልሞን እንደተወሰነች አሕዛብም ብዙ ኃጢአት ሲሰሩ ብዙ ጣዖት ሲያመልኩ ኖረው በአንድ ጌታ አምነው የመኖራቸውን ምሳሌ ነው፡፡

ሰልሞን የኦሪት፣ ካሌብ የወንጌል ምሳሌ ነው

እነዚህ ሰላይነታቸው በዚህ ዓለም እንደሆነ ኦሪትና ወንጌልም የተሠሩት በዚህ ዓለም ነውና

ራኬብን ለምን አነሣት ቢሉ እንደ ትዕማር በል

ማቴ 1÷5 ‹‹**ቦዔዝም ኢዮቤድን ከሩት ወለደ**››

ከላይ እንዳየነው ቦዔዝ ከራኬብና ከሰልሞን የተወለደ ግማሽ ጎኑ ከአሕዛብ ግማሽ ጎኑ ከአሕዛብ የሆነ ነበር፡፡ በኋላም ከሞዓብ አገር የምትሆነውን ሩትን በውርስ አግብቶ የንጉሥ ዳዊት አያት የሚሆነውን አዮቤድን ወለደ፡፡ ሙሉ ታሪኩ በመጽሐፈ ሩት ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

የሩትም በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ከትዕማርና ራኬብ መጠቀስ ጋር አንድነት አለው፡፡

**‹‹ኢዮቤድም እሴይን ወለደ››** ነጠላ ትርጉም

**ማቴ1÷6፡-‹‹እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ››**

ከዚህ ቁጥር በታች ባሉት ቁጥሮች ሰሎሞንን፣ሮብዓምን፣አብያን ሲያነሣ ንጉሥ አይልም ከዚህ ላይ ዳዊትን ንጉሥ አለ ቢሉ፡-

*ዳዊት ሥርወ መንግሥት ነውና*

*ሥርወ መንግሥትማ ሳኦል አይደለምን ቢሉ፡- ብዙ ትንቢት የተነገረው ምሳሌም የተመሰለው ለዳዊት እንጂ ለሳኦል አይደለም፡፡ በዚያውም ላይ የክርስቶስ የዘር ሐረግ ከዳዊት እንጂ ከሳኦል አይደለምና፡፡*

*ንጉሥ ዳዊት ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ የሆነ ንጉሥ ነበር በእስራኤል ስሙ የገነነ ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩ ረጂም ስለሆነ ከ1ኛ ሳሙ 16 ጀምሮ እስከ መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ ምዕራፍ 2 ድረስ ተጽፏል፡፡ በተጨማሪም በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ተመሳሳይ ታሪክ ይገኛል፡፡ በ1ኛ ዜና 11-29 ተጽፎ ይገኛል፡፡*

**‹‹ንጉሥ ዳዊትም ከኦርዮን ሚስት ሰሎሞንን ወለደ››**

ከአረማውያኑ ወገን እነ ትዕማርን፣ ራኬብን፣ ሩትን  አንሥቶ ሲያበቃ ዕብራዊት የሆነችውን ቤርሳህን ስለምን አልጠቀሳትም፡፡ ስለምን ከኦሪዮን ሚስት አለ ቢሉ?

የቤርሳቤህን ስም ያለማንሣቱ ዕብራዊ በመሆኗ ነው ወንጌሉ የተጻፈውም በዕብራውያን በመሆኑ ዕብራውያን ደግሞ የዘር ሐረግ ቆጠራ ላይ ወንዶችን እንጂ ሴቶችን አይቆጥሩም ነበርና፡፡

አንድም ፡-ከቤርሳቤህ ቢልማ ‹‹ዳዊት ጎልማሳ አስገድሎ የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ ሳለ ንግሥናውን(ግርማውን) ፈርቶ ኃጢአቱን ሳይገልጥበት ቀረ ብለው ወንጌሉን ከመቀበል ይከለከሉ ነበር፡፡ ሐዋርያ ግን ለሰው  ፊት የሚያደላ መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡

አንድም፡- የዳዊትን ኃጢአት ገልጸ የንስሐን ጥቅም ሊያስተምረን ነው፡፡  አዳምን ያህል ሰው በድሎ ንስሐ ቢገባ ተማረ፣ዳዊትን ያህል ሰው  በድሎ ንስሐ ቢገባ ተማረ ፣ ጴጥሮስን ያህል ሰው በድሎ ንስሐ  ቢገባ ተማረ፣ እናንተም ንስሐ ብትገቡ ትድናላችሁ ለማለት

አንድም፡- አይሁድ በዐቂበ ሕግ (በሕግ መጠበቅ) ይመካሉና ‹‹እናንተማ የሕግ አፍራሽ ልጆች አይደላችሁምን;›› ለማለት

አንድም፡- ክርስቶስ የከበረው በዳዊት ነው ይሉ ነበርና ‹‹ዳዊት በክርስቶስ ከበረ  እንጂ ዳዊትማ ጎልማሳ አስገድሎ የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ  አልነበረምን? ለማለት

ማቴ 1÷7 ‹‹ **ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ››**

ከዚህ ላይ የሰሎሞን ታሪክ ቢጠቀስ መልካም ነው፡፡

ማቴ 1÷7 **‹‹ሮብዓምም አቢያን ወለደ አቢያም አሳፍን ወለደ፣ አሳፍም ኢዮሳፍጥን ወለደ፣ ኢዮሳፍጥም ኢዮራምን ወለደ፣ ኢዮራምም አካዝያስን ወለደ፣አካዝያስም ኢዮአስን ወለደ፣ ኢዮአስም አሜስያስን ወለደ ››**

ማቴ 1÷8 **‹‹አሜስያስም አዛርያስ የተባለ ያዝያንን ወለደ››**

ታሪክ፡- በዘመኑ የነበሩት ሊቀ ካህኑ አዛርያስ ነቢዩ ደግሞ ኢሳይያስ ንጉሡ ደግሞ ያዝያን ይባሉ ነበር፡፡ እናም ሊቀ ካህናቱ አዛርያስ ከንጉሡ ከያዝያን በቀኝ ይቀመጣል፡፡ ‹‹ምነው?›› ይለዋል ‹‹ካህን ይነብር በየማነ ንጉሥ ይልብሃል›› ይለዋል ፍርዱን ይገሥበታል፡፡ ‹‹ምነው ፍርዴን ትገስብኛለህ?›› ይለዋል ‹‹እምነ መንግሥት የዓቢ ክህነት›› ይለዋል ከያዝያን የሚበልጥና ልብስ (ልብሰ ተክህኖ) ይለብሳል፡፡ ‹‹ምነው?›› ይለዋል ‹‹ካህናቲከ ይልብሱ ጽድቀ›› ይልብሃል ይለዋል፡፡ ያዝያንም በዚህ ተናዶ ‹‹እኔስ በአባቴ ከቤተ መንግሥት ብወለድ በእናቴ ከቤተ ክህነት እወለድ የለምን? ብሎ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ ሊያጥን ሲገባ ሕዝቡ ተው ይቅርብህ አሉት ንጉሥ ነውና ተጋፍቶ ገባ፡፡

ሲያጥን ጢሰ ቅታሬው ቢነካው ከግባሩ ለምጽ ወጣበት፡፡ በሻሽ ቢሸፍነው ከሻሹ ላይ ወጣበት፡፡ እስራኤል ለምጽ የያዘውን እንኳን ሊያነግሡት ሊገናኙት አይወዱምና ከከተማ ውጪ አስወጡት ልጅንም ኢዮአታምን አነገሡት፡፡

ያዝያን አዛርያስ የተባለበት ምክንያት

አዛርያስ በሉኝ ያለውን ያዝያንን ወለደ ሲል ነው

አንድም ፡- የአዛርያስ ስራ ልስራ ማለት ነው

አንድም፡- በፍና ተሳልቆ ‹‹ሕዝቡን አዛርያስ በሉኝ› ብሎ ተሳልቀውበታልና

እናም ወንጌላዊው ያዝያንን ለምን አነሳው ቢሉ

‹‹ያዚያን›› ካስተማሩት ትምህርት ከሰሩለት ሥርዓት ቢወጣ እንዲህ ያለ መከራ አገኘው እናንተም ካስተማርናችሁ ትምህርት ከሰራንላችሁ ሥርዓት ብትወጡ እንዲህ ያለ መከራ ያገኛችኋል ለማለት ነው

ማቴ 1÷9፡- **‹‹ያዝያንም ኢዮአታምን ወለደ ኢዮአታምም አካዝን ወለደ››**

ማቴ 1÷10፡- **‹‹አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ፤ ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ፤ ምናሴም አሞጽን ወለደ››**

ማቴ 1÷11 **‹‹አሞጽም ኢዮስያስን ወለደ፤ ኢዮስያስም በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኢኮንያን እና ወንድሞቹን ወለደ››**

ኢዮስያስ፡-
- ኢዮአክስ (ሴሎም)
- ኤልያቄም (ዮአኪን) - ኢኮንያን

ማታንያን (ናታን) (ሴዴቅያስ)

ወንጌላዊው የኢዮስያስን የልጅ ልጅ ኢኮንያንን ልጅ ብሎ አኀቶቹን ወንድሞቹ ብሎ እንደነገሠ ጊዜ የተደረገውን ለልደቱ ሰጥቶ ለማን ተናገረ ቢሉ፡- ሰቶም ዘንግቶም አይደለ ልማድ ይዞት ነው እንጂ የልጅን ልጅ ልጅ ማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ልማድ (ወግ) ይዞት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ያዕቆብ ከላባ ኮብልሎ ሚስቶቹን፣ ልጆቹን ይዞ በመጣ ጊዜ ላባ ያዕቆብ 3 ቀን የተጓዘውን 1 ቀን ገሥግሶ ደርሶ ‹‹ወንዶቹንና ሴቶቹን ልጆቼን እንድስም ስለምን አልፈቀድክልኝም››ብሎታልና (ዘፍ 31÷28)

‹‹ አብርሃምም ሎጥን አለው፡፡ እኛ ወንድማማች ነንና፡፡ በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለው›› (ዘፍ 13÷8)

ዘፍ 14÷12-14፡- አብርሃም ስለ ወንድሙ ልጅ ሎጥ ሲናገር‹‹አብርሃምም ወንድሙ እንደተማረከ በሰማ ጊዜ….›› ይላልና

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምናነበው ኢኮንያን የኢዮስያስ የልጅ ልጅ እንደሆነ ነው፡፡ የኢኮንያን ወንድሞች የተባሉት ኢዮአክስና ሴዴቅያስ ናቸው፡፡ እነርሱም አኀቶቹ ናቸው ወንጌላዊው አኀቶቹን ወንድሞቹ የማለቱ ምስጢር (ምክንያት) ከላይ እንደተጠቀሰው ነው፡፡ ይህን ማድረጉ ልማድ ይዞት ነው፡፡

የባቢሎን ምርኮ መጠቀሱ ፡-

ለትምህርት ለተግሳጽ ነው

አንድም፡- ለምሳሌ እንዲያመች ነው

እስራኤል ከክፉ ሥራቸው እንዲመለሱ የእግዚአብሔር ነቢያት ቢመክሯቸውም ባለመመለሳቸው ወደ ባቢሎን ተማርከው 70 ዘመን በባቢሎን በምርኮ እንዲኖሩ እስራኤል ዘነፍስ ክርስቲያኖችም የመምህራንን ትምህርትና ተግሳጽ ሰምተው ከበደል ከኃጢአት ካልተመለሱ ወደ ሲኦል እንደሚወርዱ ለመጠየቅ፣ ለማስተማር፡፡

ምሳሌውም፡-

የእስራኤል ወደ ባቢሎን መማረክ ፡- አዳምና ሔዋን ከገነት ወደ ሲኦል የመውረዳቸው ምሳሌ ነው ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መመለሰቸው የአዳምና ሔዋን እንዲሁም ነፍሳት ከሲኦል ወደ ገነት የመመለሳቸው ምሳሌ ነው፡፡

ማቴ 1÷12-16 **‹‹ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፣ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ ዘሩባቤልም አብዩድን ወለደ ፣አብዩድም ኤልያቄምን ወለደ፣ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፣ አዛርም ሳዶቅን ወለደ ፣ሳዶቅም አኪምን ወለደ፣አኪምም ኤልዩድን ወለደ፣ ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ፣ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፣ ማታንም ያዕቆብን ወለደ››**

ማቴ 1÷16፡- ‹‹…**ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያም እጮኛ ዮሴፍን ወለደ››**

ከዚህ ላይ የክርስቶስ ልደት በቅጽል ተጠቅሶ የዮሴፍ ልደት በዋነኝነት የመጠቀሱ ምስጢር ምንድን ነው ቢሉ ወንጌላዊወው ክርስቶስ እናት እንጂ ምድራዊ አባት ስለሌለው

ዮሴፍ ደግሞ ከዳዊት ዘር ነውና ክርስቶስ በእናቱ እጮኛና ዘመድ በሆነው በዮሴፍ የዳዊት ልጅ ተብሎ እንዲቆጠር ነው፡፡

ምነው በእናቱ የዳዊት ልጅ አይባልምን ቢሉ በልማዳቸው ሴትን ከትውልድ ቁጥር አስገብተው አይቆጥሩምና ነው፡፡ ነገር ግን ወንጌላዊው እመቤታችንም እንዳትቀር በቅጽል አስገብቷታል፡፡ አልዓዛር ማታንና ቅሳራን ይወልዳል ማታን የዮሴፍ አባት ያዕቆብን ቅሳራ ደግሞ የእመቤታችንን አባት ኢያቄምን ይወልዳሉ፡፡

| | አልዓዛር |
|---|---|
| ማታን | ቅስራ |
| ያዕቆብ | ኢያቄም |
| ዮሴፍ | እመቤታችን |

እመቤታችን ለዘመዷ ለዮሴፍ (በ3 ቤት የሚዛመዳት) እንድትታጭ መሆኑ ለምንድን ነው? ቢሉ በልማደ አዋልደ ሰለጳድ ነው፡፡ (ዘኁ 36፡13)

እመቤታችን ለዮሴፍ የታጨችበት ምክንያት፡-

አይሁድ እመቤታችን ክርስቶስን ያለ ወንድ ዘር መውለዷን በማየት ይህችስ ሀይል አርያማዊት ናት ባሉ (ከሰማይ የመጣች ሀይል ናት) እንጂ የአዳም ዘር አይደለችም፡፡ እንዳይሉ ‹‹ከሰማይ የመጣች ሀይል ብትሆንማ ለዮሴፍ ባልታጨች ነበር›› ብሎ ነገራቸው ለማፍረስ አትናትዮስ ሐዋርያዊም መታጨቷ ለዚህ (ከላይ ለጠቀስነው) እንደሆነ ሲያስረዳ ገብርኤል መልአክም ወደ ድንግል ብቻ ተላከ አላለም፡፡ ይልቁንም ‹‹ስሙ ዮሴፍ ለሚባል ሰው (ወንድ) ወደ ታጨች ድንግል ተላከ›› አለ እንጂ የወንድ እጮኛ በማለቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእውነት ሴት እንደሆነች ያስረዳል ብሏል፡፡

አንድም፡- ጽንስን ከአጋንንት ለመሰወር

መጽነሷን ቢያውቁ ኖሮ ብዙ ጽንሶችን ባበላሹ ነበርና

አንድም፡- ከአይሁድ ውግረት (ከመወገር) እንዲያድናት

በሥርዓታቸው በዘኁ 5÷19 ላይ በተጠቀሰው መሰረት አንዲት ሴት ከባልዋ ውጭ ጸንሳ ብትገኝ ማየ ዘለፋ ያጠጧት ነበር፡፡ እንዲሁም አንዲት ሴት ባል ሳታገባ ብትጸንስ በሙሴ ሕግ መሰረት ደብድበው ይገድሏት ነበር፡፡ ስለዚህ እመቤታችን ለዮሴፍ ሳትታጭ ጸንሳ ቢሆን አይሁድ ለድብደባ ባበቋት ነበር፡፡

አንድም፡- አገልጋይዋ ተላላኪዋ እንዲሆን ነው፡፡

ሄሮድስ ልጇን ሊገድለው ባስፈለገው ጊዜ ወደ ግብጽ ስትሰደድ ዮሴፍ አብሯት ተሰዶ እንዲረዳት እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንድትታጭ አደረገ

ስለዚህ ድንግል ማርያም ለዮሴፍ መታጨቷ እኒህና ይህን ለመሳሰሉ ምክንያቶች ነው እንጂ ለሚስትነት አይደለም፡፡ ለዚህስ ቢሆን ኖሮ ለዮሴፍ ትታጭ ሲል ተአምራትን ባሳየ ነበር በትር እስከማለምለም ባላስፈለገም ነበር፡፡

‹‹ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን›› ሲል ምን ያመለክታል?

ክርስቶስ የጽርዕ ቋንቋ ነው በዕብራይስጥ ማስያስ፣ በዓረብኛ መሲህ፣ በግዕዝ ቅቡዕ ይባላል፡፡ክርስቶስ የሥጋዌ (የትስብንት) ስም ብቻ ወይም የመለኮት ብቻ ስም አይደለም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ሲሆን የመጣለት ስም ነው፡፡

ወንጌላዊው ማቴዎስ ‹‹ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን›› ብሎ ማቴዎስ ሲጽፍ ሐዋርያት ሲያደርጉ እንደነበር ሁሉ ከእመቤታችን የተወለደው ኢየሱስ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት እስራኤል ዘሥጋ በተስፋ ሲጠባበቁት የነበረው ክርስቶስ መሆኑን መመስከሩ ነው፡፡(ሌዋ 18÷28፣ሐዋ 2÷36)

ማቴ 1÷17 ‹‹እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አስራ አራት ትውልድ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮ አስራ አራት ትውልድ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶ አስራ አራት ትውልድ ነው፡፡››

ሦስቱ ክፍለ ዘመናት የተጠቀሱበት ምክንያት በሦስቱ ዘመናት የተናገረው፣ የተሰጠው ተስፋ በክርስቶስ መወለድ መፈጸሙን ለማጠየቅ ነው፡፡

ከአብርሃም - ዳዊት ፡-

ይህ ዘመን ዘመነ አበው ይባላል፡፡ በዚህ ዘመን ‹‹በዘርእከ ይትባረኩ ኩሎሙ አሕዛብ ምድር›› ‹‹በዘርህ የምድረ ነገዶች ሁሉ ይባረካሉ›› የሚል ተስፋ ለአብርሃም ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይህ ተስፋ የተፈጸመው በክርስቶ ነው፡፡ (ዘፍ 12÷3)

**ከዳዊት - ባቢሎን ምርኮ ፡-**

ይህ ዘመን ዘመነ ነገሥት ይባላል፡፡ በዚህ ዘመን ‹‹እስመ እምፍሬ ከርስከ ከነብር ዲበ መንበርከ›› ‹‹ከወገብህ (ከሆድህ) ፍሬ በዙፋንህ እኖራለሁ›› የሚል ቃል ኪዳን ለዳዊት ሰጥቶት ነበር፡፡ ይህ ቃል ኪዳን የተፈጸመው በክርስቶስ ነው፡፡ (መዝ 131(132)÷11)

**ከባቢሎን ምርኮ - ክርስቶስ ልደት፡-**

ይህ ዘመን ዘመነ ካናት (ነቢያት) እየተባለ ይጠራል፡፡ በዚህ ዘመን የነበሩ ካህናት ሊመጣ ላለው ክርስቶስ ጥላዎች ነበሩ፡፡ መሥዋዕት ይሰዉ ነበር፡፡ መሥዋዕታቸው ግን ፍጹም ደኅንነትን የሚያመጣ አልነበረም እራሳቸውም በሞት የሚሸነፉ ደካሞች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ፍጹም መሥዋዕት ለመሆንና ፍጹም ደኅንነት ሊያመጣ ሞትንም ድል ለማድግ ታላቁና እውነተኛው ካህን ክርስቶስ መጣ፡፡

ከአብርሃም - ክርስቶስ ልደት (ሶስቱ ዘመናት) በአጠቃላይ አርባ ሁለት ትውልዶች ይሆናሉ፡፡ እነዚህ 42 መሆናቸው ምሳሌነት አለው፡፡ ይኸውም፡- ለሰሎሞን ስድስት እርከኖች ያሏት አንድ አትሮንስ ነበረችው፡፡ እርሱ በ6ኛይቱ ሆኖ ነገር ሲሰማ ሲፈርድ ይውል ነበር፡፡ 6 እርከን በሱባዔ ሲቆጥሩት 42 ይሆናል፡፡ (6x7=42) የ42 አበው ትውልድ ሲፈጸም ጌታ ሰው የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡ ሰሎሞን የጌታ ፣ አትሮንስ የእመቤታችን ፡፡

ተርትሮ የቆጠረውን ደምሮ፣ ደምሮ የቆጠረውን ተርትሮ መቁጠሩ ስለምንድን ነው? ቢሉ አይሁድ ወንጌላዊው ተርትሮ እንጂ ደምሮ ወይም ደምሮ እንጂ ተርትሮ መቁጠር አይሆንለትም ብለው ደገኛይቱን ወንጌል ከመቀበል በተከለከሉ ነበር፡፡

አንድም፡- ተርትሮ መቁጠር የሦስትነት ደምሮ መቁጠር የአንድት ምሳሌ

አንድም፡- በሦስቱ ክፍለ ዘመን የተነገረው በአንድ ጌታ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ

ማቴ 1÷18 ‹‹**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር**››

የነትዕማርን፣ የነራኬብን፣ የነሩትን ሲናገር መጥቶ ነበርና የጌታ ልደት እንዲህ ነው አለ፡፡

የጌታ ልደት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ አይደለም ከጥንት ሲያያዝ የመጣ ነው ለማለት ‹‹እንዲህ ነበር›› አለ

ማቴ 1÷18 ‹‹ **እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች**››

እዚህ ላይ ስለ እመቤታችን ትውልድ (ነገረ ማርያም እስከ ለዮሴፍ መታጨት ድረስ) ቢተረክ ተገቢ ነው፡፡

‹‹**ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች**››

ሳይገናኙ አለ፡- እርሱ ሴት እንደሆነች ሳያውቃት እርሷም ወንድ እንደሆነ ሳታውቀው

አንድም፡- ዮሴፍ ጠባቂ ስላላት አጋዥ ሳትሻ ድንጋሌ ሥጋ ድንጋሌ ነፍስ ስላላት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ጸንሳ ተገኘች

‹‹**ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች**››

እንዲህ ሲል በመንፈስ ቅዱስ ተከፍሎ ኑሮበት አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሥጋና አጥንት የለውም ስለዚህ እንዲህ ማለቱ ‹‹አነጻት›› ሲል ነው

አነጻት ሲል ‹‹የእመቤታች የውርስ ኀጢያት ኖሮባት አይደለም›› ‹‹ከለላት›› ሲል ነው፡፡ ከሩካቤ፣ በዘር ከመቀበልና ድንግልን ከማጣት ጠበቃት ሲል

እመቤታችን በሰው ልጆች (በሔዋን ዘር) ከተሰሩ 3 ግብራት ንጹህ ናት 3ቱ ግብራትም የተባሉት ሩካቤ፣ ዘር፣ ሰስሎተ ድንግልና ናቸው፡፡

ከለላት ሲል፡- ብታደረገው ዕዳ በደል የሚሆንባት አይደለም አላደረገችውም ሲል ነው እንጂ፡፡ ይህንም ለማሳየት በኦሪት ዘፍጥረት 25÷27 ላይ፡- ‹‹ዔሳውም አደን የማያውቅ የበርሃ ሰው ሆነ ያዕቆብ ግን ጭምት ሰው ነበር›› አሁን ዔሳው አደን ማወቁ ዕዳ ሆኖበት ነው? ያዕቆብን አላደረገውም ድልድል፣ ቅምጥል ከቤት ዋይ ነው ሲል ነው፡፡

ጌታ ልደቱን እንበላ ዘርን ያደረገው (በዘር ያላደረገው) ሰለሞን ነው ቢሉ

ቀዳማዊ ልደቱን ለመግለጽ ነው፡፡‹‹5ሺ 5 መቶ ዘመን ሲፈጸም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱን ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደተወለደ ያስረዳልና››

በዘር በሩካቤ ተወልዶስ ቢሆን፡-

ዕሩቅ ብእሲ ባሉት ነበርና

ያውስ ቢሆን ልደቱን ተፈትሆ ካላት (ድንግል ካልሆነች) ያላደረገው ተፈትሆ ከሌላት (ከድንግል) ያደረገው ስለምን ነው ቢሉ

ትንቢቱን ምሳሌውን ለመፈጸም

ትንቢቱ ‹‹እንሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች››. ይላልና (ኢሳ7÷14)

ምሳሌው፡-

አዳም ከኅቱም ምድር ተገኝቷል ጌታም ከኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ነው

ሔዋን ከኅቱም ገቦ (ጎን) ተገኝታለች ጌታም ከኅቱም ማህጸን ለመገኘቱ ምሳሌ

ቤዛ ይስሐቅ በግዕ ከኅቱም ጕንድ እንደተገኘ ቤዛ ዓለም ክርስቶም ከኅቱም ማኅጸን ለመገኘቱ ምሳሌ

ጽምዓ እስራኤልን ያራቀ ውሃ ከኅቱም አለት ተገኝቷል ጽምዓ ነፍሳትን ያበረደ ውሃ ማየ ሕይወት ክርስቶስም ከኅቱም ማኅጸን ለመገኘቱ ምሳሌ ነው

ጽምዓ ሶምሶንን ያበረደ ውሃ ከኅቱም መንሽከ አድግ ተገኝቷል ጽምዓ ነፍሳትን ያራቀ ማየ ሕይወት ክርስቶም ከኅቱም ማኅጸን ለመገኘቱ ምሳሌ

ምሳሌውን አውቆ አስመስሏል ትንቢቱንም አውቆ አናግሯል ድምዳሜው ለምን ነው ቢሉ

እመቤችን ታላቅ የሃይማኖት መምህርት (መመሪያ) እንድትሆን ነው፡፡ ይኸውም፡- ‹‹ድንግል ወእም›› ‹‹ድንግልም እናትም›› እየተባለች መኖርዋ ጌታ አምላክም ሰውም ሲባል ለመኖሩ ምሳሌ ፤ ስትወልደው ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡ ጌታ ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ ምሳሌ

ከመወለዱ በፊት ድንግል - ድንጋሌ ሥጋ፤ በወለደች ጊዜ - ድንጋሌ ነፍስ ከወለደች በኋላ ድንግል - ድንጋሌ ኅሊና ያስተባበረች ከአዳም እና ከሔዋን ዘር እመቤታችን ብቻ የተሰጠ ፀጋ (ሀብት) ነው፡፡

ማቴ1÷19-20 ‹‹እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ›› እርሱ ግን ይህን ሲያስብ እግዚአብሔር መልአክ በህልም ታየው፡፡ እንዲህም አለ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከእርሷ የተፀነሰው በመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ››

ታሪክ፡- እመቤታችን የብፅዓት ልጅ ናት፡፡ ሦስት ዓመት ሲሆናት እናትና አባቷ ወስደው ለካህናት ሰጧት፤ካህናትም ተቀብለው አክብረው ከቤተ መቅደስ ያኖሯታል፡፡ አስራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ ትኖራለች፡፡ ከወላጆቿ ዘንድ ሦስት ዓመት በቤተ መቅደስ አስራ ሁለት ዓመት በጠቅላላ አስራ አምስት ዓመት በሞላት ጊዜ አይሁድ ካህኑ ዘካሪስን ‹‹ይህቺ ብላቴና መጠነ እንስት ደርሳለችና ቤተ መቅደሳችንን ታሳድፍብናለችና ትውጣልን›› አሉት ካህኑ ዘካርያስም እመቤታችንን ‹‹እንደምን ሁነሽ ልትኖሪ ትወጃለሽ›› አላት፡፡ ‹‹ወደ እግዚአብሔር

አመልክትልኝ›› አለችው፡፡ ቢያመለክትም ‹‹ከነገደ ይሁዳ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸው አረጋውያን ብትር ሰበስበህ ከቤተ መቅደስ አግብተው አውጣው ምልክት አሳይሀለሁ›› አለው፡፡ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት (1985) ብትር ሰብስቦ ከቤተ መቅደስ አግብቶ ቢያወጣው ከዮሴፍ በትር ላይ ‹፣ዮሴፍ ማርያምን ጠብቃት›› የሚል ጽሁፍ ተገኘ፡፡ ዕጣ ቢያወጣም ለርሱ ደረሰ፡፡ ርግብ መጥታም አርፋበታለች፡፡ ሦስት ምስክር ሆነ ካህናቱም ‹‹ከእግዚአብሔር አግኝተን የሰጠንህን ከእግዚአብሔር አግኝተን እስክናሰናብትህ ወስደህ ጠብቃት›› ብለው ሰጡት ይዟት ሄደ፡፡

ዮሴፍ ንግድ ሄዶ 3 ወር ቆይቶ ሲመለስ ዮሐንስ የሚባል ፈላስፋ ወዳጅ ነበረውና ሊጠይቀው መጣ ጥቂት ተጨዋውተው ሲሄድ ሊሸኘው ይወጣል፡፡ ዮሐንስም ‹‹ይህች ብላቴና የጸነሰች ካንተ ነው ከሌላ›› አለው፡፡ በምን አወቀ ቢሉ ፈላስፋ ነውና የጌታ ጽንስስ በፍልስፍና አይታወቅም ቢሉ በመልኳ፤ ሴቶች ሲጸንሱ መልካቸው ያምራል ጡታቸው ይጠቁራልና በዚያ አውቆ፡፡ ዮሴፍም ‹‹እኔስ እንኳን ነቢብ ገቢር ኀልዮም አላውቅባትም›› አለው፡፡ ዮሐንስም ‹‹እንግዲያስ ጸንሳለችና ገብተህ ጠይቃት›› ይለዋል፡፡ ዮሴፍም ‹‹የእስራኤል ልጅ ሆይ ድንግልናሽን የገሠሰ ማነው? ከማንስ ነው የጸነስሺ?›› ብሎ ቢጠይቃት ‹‹በመንፈስ ቅዱስ ግብር›› አለችው፡፡ ዮሴፍ ደነገጠ፤ ተጠራጠረ፡፡ እመቤታችንም ‹‹እኔስ መልአኩ አክብሮ ከነገረኝ በቀር ሌላ ምንም ምን እንዳላውቅ እግዚአብሔር ያውቃል›› አለችው፤ ነገሩ ረቀቀበት፡፡

ዮሴፍ ነገሩ ቢረቅበት በደጃፋቸው ወድቆ ደርቆ የሚኖር ግንድ ነበር ተክላ፣ አለምልማ፣ ፍሬ አስፈርታ አሳየችው፡፡ አንህብትን ከባሕርያቸው እንዲራቡ እፅዋትም ከባሕርያቸው እንዲያብቡ የሚያደርግ እርሱ አይደለምን በማለት አስረድታዋለች፤ እርሱም ነገሩን ተረዳው፡፡ ከዚህ በኋላ አንድ አይሁድ ሥርዓተ ለበዓል የሚወጡበት ጊዜ ደረሰ፡፡

ዮሴፍ ‹‹ይዟት ቢወጣ ሴሰነች ብለው ወግረው ይገድሉብኛል ትቻትም ብወጣ (ብሄድ) ‹‹ያደረገችውን ታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ›› እንዲሉ ያደረገውን አውቆ ትቷት መጣ ይሉኛል ብሎ በጽኑ የሀሳብ ውጣ ውረድ ወደቀ፡፡ ‹‹ ወወድቀ ዮሴፍ ውስተ ጽኑዕ መዋግደ ሕሊና›› እንዲል፡፡ ይህን ሀሳብ ሲያወጣ ሲያወርድ ስለነበር ደግ ነውና ሊገልጥባት አልወደደም በስውር ሊተዋት አሰበ እንጂ

በኦሪቱ ‹‹ማየ ዘለፋ›› የሚባል የማጠጣት ሥርዓት ነበር፡፡ ‹‹የስድብ (የመርገም) ውሃ›› እንደማለት ነው፡፡ ባል ሚስቱን የጠረጠራት እንደሆነ አጋልጦ ይሰጣታል፡፡ ውሃ በንቀል ሀረፀ ሰገም(የገብስ እርሾ) አሲዞ ሚስቱን አከናንቦ ይዟት ወደ ሊቀ ካህናቱ ይሄዳል፡፡ ከመድረኩ ስትደርስ ሊቀ ካህናቱ ‹‹ክንብንብሽን ግለጭ›› ይላታል ይኸውም ‹‹ይግለጥብኝ በይ›› ሲላት ነው ከዚያም በኦሪቱ የሚደግሙት አለ ያንን ይደግሙና ያረረ ዕጣን ጨምሮ በጥብጦ ‹‹ባልሽ የጠረጠረሽን አድርገሽው እንደሆነ በወንድ ልጅ ተከበሪ›› ብሎ ይሰጣታል፡፡ እርሷም ‹‹መርገሙ ይደረግብኝ፤ በረከቱ ይሁንልኝ›› ብላ ትጠጣዋለች

ካደረገችው ትሞታለች ካላደረገችው ወንድ ትወልዳለች

ዮሴፍ እመቤታችንን ‹‹ማየ ዘለፋ ትጠጣልኝ›› አላለም ትቷት ሊሄድ አሰበ እነጂ ይህንን ቢያደርግ ደግነቱን ያስቀርበታልን? በኦሪቱ ታዞ የለምን ቢሉ ዮሴፍ ጻድቅ ወንጌል እንጂ ጻድቀ ኦሪት አይደለምና ነው፡

ማየ ዘለፋ ትጠጣልን አሉ ማየ ዘለፋን ቢያጠጧት ከብርሃኗ የተነሳ እርሷን ማየት አቅቷቸዋል፡፡

ማቴ 1÷20፡- ‹‹**እርሱ ግን ይህን ሲያስብ የጌታ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ታየው**››

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በህልም ታየው (ተናገረው)

ሕልም ከሦስት ወገን ነው (ከሦስቱ ወገን ይታያል)

1 ከባሕርይ (ከሐሞት) 2 ከሰይጣን 3 ከመልአክ

ከባሕሪይ፡- (ከሐሞት)

ባሕሪያት (ሐሞታት) 4 ዓይነት ናቸው

በልቀም - እሳታዊ ባህሪይ

ደም - ማያዊ (ውሃዊ)

ሳፍራ - ነፋሳዊ

ሳውዳ - መሬታዊ

እነዚህ ባሕርያት በሰው በሰለጠኑ ጊዜ እንደሰለጠኑበት ባሕርይ የሰው ልጅ በተለያየ ኅብር ሲያልም ያድራል፡፡

ከሰይጣን የሚገኝ (የሚመጣ) ሕልም

እንደ ሄሮድስ፡- በስደቷ ጊዜ "ከዚህ ዋለች ከዚህ አደረች" እያለ ይነግረው ነበር፡፡ ዛሬም ለጠንቋይ ለመተተኛ ቅርባቸው ስለሆነ ይነግራቸዋል፡፡ ሕልም ያሳያቸዋል፡፡

ከመልአክ የሚገኝ ሕልም

እንደ ፈርዖን፣ እንደ ናቡከደነጾር፣ እንደ ዮሴፍ . . .

ዘፍ 41÷11፡- ፈርዖን ሰባት የወፈሩ ላሞች ሰባት የከሱ ላሞችን ሲውጧቸው ሕልምን አየ፡፡ የሚተረጉምለት ቢያጣ ታስሮ የነበረው የያዕቆብን ልጅ ዮሴፍ ሕልም የመተርጎም ጸጋ እንዳለው ሲነገረው ከእስር አስፈትቶ አስመጣው፡፡ ዮሴፍ ሕልም ከእግዚአብሔር እንደተገኘና እግዚአብሔር በግብጽ ምድር ስለሚያመጣው 7 የጥጋብ አመታት እነዚህ ዓመታት በኋላም ስለሚኖሩት 7 የርሃብ ዘመናት ነበር፡፡ እናም በዮሴፍ መካሪነት ንጉሡ በሃገሪቱ አንድ ብልህ አዋቂ ሰው ተፈልጎ በግብጽ ምድር ላይ እንዲሾምና ለረሀብ ዘመን የሚሆነውን እህል በጥጋቡ ዘመን እንዲያከማቹ የሚደረግበትን ዘዴ እንዲያመቻች ይደረግ ዘንድ ለንጉሱ ሲነገረው ይህንን ከአንተ በቀር ሌላ የሚያደርገው የለምና ብሎ ለግብጽ ከንቲባ አድርጎ ሹሞታል፡፡ በዚህም ሁኔታ ግብጽ ከረሃብ ዳነች፤ እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ አደረገው፡፡

ትንቢተ ዳንኤል 4÷1፡- ንጉሡ ናቡከደነጾር እጅግ በጣም የተከበረ ግዛቱም የሰፋና ንጉሥ በመሆኑ ራሱን በጣም ከፍ ከፍ ያደርግ ነበር፡፡ የሚሰጥ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እስኪዘነጋ ድረስ እግዚአብሔር ስልጣንን ከባለስልጣን እጅ ሊወስድ መቻሉን እስኪረሳ ድረስ ራሱን አስታበየ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ሕልም እንዲያይ አደረገው፡፡ በነቢዩ ዳንኤል እንደተተረጎመው ንጉሡ ናቡከደነጾር ስልጣን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንደሆነ እስኪያምን እስኪገነዘብ ድረስ ከሰዎች ተለይቶ ጠጉሩ እንደ ንስር፤ ጥፍሩም እንደ ወፎች እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተለይቶ እንደሚሰደድ እንደ በሬም ሳር እየበላ እንደሚኖር አካሉም በሰማይ ላይ እንደሚረሰረስ በተነገረው መሰረት ንጉሡ ስልጣን የሚሰጥ ከእግዚአብሔር መሆኑን እስኪቀበልና ቅጣቱን እስኪፈጸም ድረስ በተነገረለት (በሕልሙ) መሠረት እንደ አውሬ ከሰው ተለይቶ በዱር ኖርዋል፡ በኋላም ሕሊናው ተመለሰለት እግዚአብሔርን እንዳመሰገነም ተጽ÷ል፡፡

የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታየውና ‹‹የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከእርሷ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፡፡›› አለው፡፡

ዳዊትና ለምን አነሣ ቢሉ፡-

የርጉረሩኀ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ እህትህ ናትና ራራላት ለማለት

አንድም፡- መዝ 131(132)÷11 ‹‹ከወገብህ ፍሬ በዙፋንህ አኖራለሁ›› ብሎ

ለዳዊት የተናገረለት ትንቢት እንደተፈጸመ ለማጠየቅ ዳዊትን አነሣው

አንድም፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከካህናት እጅ እንደተቀበልክ ከእደ

መንፈስ ቅዱስ መቀበልን አትፍራ ለማለት

ከርሷ የሚወለደው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነውና ወደ በዓሉ ይዘሃት ለመሄድ አትፍራ አለው፡፡

ማቴ 1÷21-23 ‹‹ልጅም ትወልዳለች እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ፡፡ በነቢይ ከጌታ ዘንድ እንሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከኛ ጋር የሚል ነው፡፡››

‹‹ወገኖቹን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል››

‹‹ወገኖቹን ኃጢአታቸው ምክንያት ከመጣባቸው ፍዳ ያድናቸዋል›› ብሎ የስሙን ትርጓሜውን የተናገረው መልአኩ ነው

ታሪክ ስለ ጌታችን ልደት

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ‹‹ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ›› ከማለት በቀር ስለ ልደቱ ምንም አልገለጸምና

ከዚህ ሲደርሱ ስለ ክርስቶስ ልደት መናገር ተገቢ ነው ሉቃ 2÷1

ጌታችን በተወለደበት ወራት እስራኤላውያን በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር ነበሩ፡፡ በዚያን ጊዜም ከአውጉስጦስ ቄሳር ሰው ሁሉ ይቆጠር (እንዲጻፍ) ትዕዛዝ ወጣ፡፡ ዮሴፍም ጸንሳ ከነበረች ከእጮኛዋ ከእመቤታችን ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ፡፡ በዚያም የበኩር ልጅዋን ወለደች፤ በመጠቅለያም ጠቀላላቸው፡፡ ጣቱንም አሰረችው፡፡

በመጠቅለያ መጠቅለሏ፡- (በጨርቅ ጠቀለለችው) ለምን ቢሉ

ልብስ የላትም ነበርና ብታጣ በጨርቅ ጠቀለለችው

አንድም፡- ምትሐት እንዳልሆነ ለመጠየቅ

አንድም፡- ዮሴፍ ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ እንዲህ ይገንዙሃል ስትል

አንድም፡- ካህናት በቤተ መቅደስ ሥጋህን ዕለት ዕለት እንዲህ ይገንዙሃል ስትል በጨርቅ ጠቀለለችው፡፡

ጣቱን አሰረችው ለምን ቢሉ ፡-

ሞትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ

አንድም፡- በዛራ ልማድ (ዘፍ 38÷1-30)

አንድም፡- ዮሴፍ ኒቆዲሞስ እንዲህ አድርገው ይገንዙሃል ስትል

የክርስቶስ ስመ - ሥጋዊ

ኢየሱስ፡- ሕዝቡን ከኀጢአታቸው የሚያድናቸው (ማቴ 1÷21)

ክርስቶስ፡- የተዋሕዶ ስም (ከተዋህዶ በኋላ የተሰጠው ስም) (ሉቃ 2÷11)

ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ሲሆን ያገኘው ስም ነው ፡፡

አማኑኤል፡- ‹‹እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ›› ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችንም ነፍስ ነሥቶ ከኛ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው፡፡ (ማቴ 1÷23) መናፍቁ ንስጥሮስ ተዋህዶን ተቃውሞ ‹‹ኀድረት›› ብሎ ሲያስተምር (ሲሳሳት) ቅዱስ ቄርሎስ የረታው በዚህ ስም ነው፡፡

መድኃኔዓለም፡- በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣ (ከመጣብን) የነፍስ በሽታ የዳነው(የምንድነው) በእርሱ ነውና (ሉቃ 2÷11)

ማቴ 1÷24 ‹‹ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ እጮኛውንም ወሰደ››

‹‹ይዘሃት ውጣ›› እንዳለው ይዟት ወጣ

‹‹ጠብቃት›. እንዳለው ጠበቃት

‹‹እጮኛውን ወሰደ›› ሲል፡- ወደ በዓሉ (ጉባዔው) ይዟት ሂደ ማለቱ ነው

ማቴ 1÷25 ‹‹የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም››

**የበኩር ትርጉም**

በኩር የግእዝ ቃል ነው ትርጉሙም ‹‹የመጀመሪያ ልጅ›› ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን ‹‹በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማኅጸንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው›› (ዘጸ 13÷1) ብሎ በተናገረው ቃል መሰረት የእናቱን ማኅጸን የሚከፍት ሁሉ በኩር ይባላል፡፡ አንድ ሰው በኩር ለመባል (ለመሆን) የግድ ተከታይ ሊኖረው አያስፈልገውም፡፡

አባ ጀሮም፡- ‹‹ብቸኛ ልጅ ሁሉ የበኩር ልጅ ይባላል፡፡ የበኩር ልጅ ሁሉ ግን ብቸኛ ልጅ አይደለም›› እንዳለ አዲስ የተጋቡ ወላጆች የመጀመሪያ ልጃቸውን በኩር እንዲባል ሁለተኛ ልጅ መውለድ አይጠበቅባቸውም፡፡ አንድ ብቻ ቢሆንም ተከታይ የሌለው በኩር ይባላል፡፡ ይህን ለማስረዳትም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ዕብ 1÷6 ላይ ‹‹ደግሞ በኩርን ወደ ዓለም ሲያስገባ….›› በማለቱ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ሆኖ ወደ ዓለም መምጣቱን ያመለክታል፡፡ በኩር በመባልም ተከታይ እንደሌለው ወንጌላዊው ዮሐንስ ‹‹እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ

ተረከው›› (ዮሐ 1÷18) በማለት የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብኩርናን  አንድ ልጅ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

እንግዲህ ‹‹የበኩር ልጅዋን›› መባሉ መጻሕፍት አስተባብረው በኩር፣ በኩር ብለው የተናገሩለት፣ ቅድመ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን የፈጠረ፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለውን አምላክ፣ ልዑል ባሕርይን ወለደች ለማለት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ በኩር በማለት ረቀቅ ባለ አመለካከት (አመሰጣጠር) ያስተምራሉ፡፡ እንደ ሊቃውንቱ አባባል በኩር የሚለው ቃል ለክርስቶስ በ3 መንገድ ይፈታል፡፡

በልደቱ፡- ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት በመወለዱ በዚህ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንደኛ ተመሳሳይ የሌለው ብቸኛ በመሆኑ በኩር ተብሏል፡፡

በሞቱ፡- ‹‹ነፍሴን እኔ በፍቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም›› (ዮሐ 10÷18) እንዳለ የሞትን ጻእር አርቆ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በመለየት የሙታን በኩር ተብሏል፡፡ በዚህም ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንደኛ ተመሳሳይ የሌለው ብቸኛ ነው፡፡

በትንሣኤው፡- ‹‹ነፍሴን ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ስልጣን አለኝ›› ብሎ እንደተናገረ (ዮሐ 10÷18) መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በገዛ ስልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ በመነሳቱ፤ ሞት ይዞ ሊያስቀረው የማይቻለው መሆኑን በመግለጡ፤ ለሞት ተገዢዎችም ትንሣኤን በመስጠቱ ከሞት ለሚነሡ ሁሉ በኩር ሆነ፡፡ በገዛ ስልጣኑም ከሞት ተነሥቶ ትንሣኤን ለሙታን በመስጠቱ የሚመስለው የሌላ ብቸኛ፤ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንደኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ በኩር የሚለው ቃል ለክርስቶስ ሲተረጎም

ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንደኛ

ተመሳሳይ፣ አቻ፣ እኩያ ተፎካካሪ የሌለው ብቸኛ ማለት ነው፡፡

### የ ‹‹እስከ›› ትርጉም

ለስም አጠራርዋ ክብር ይግባትና ‹‹የበኩር ልጅዋን እስከትውልድ ድረስ አላውቃትም›› የሚለውን ኃይለ ቃል በመያዝ መናፍቃን ዮሴፍም እመቤታችንን ጌታን ከወለደች በኋላ በግብር አውቋታል በማለት በድፍረት ያስተምራሉ፡፡ ይህ ትምህርት ትክክል እንዳልሆነና እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና ያላት መሆንዋን የሚከተለው ሐተታ ቀርቧል፡፡

‹‹እስከ›› - በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት አገባብ(ትርጉም) አለው

ፍጻሜ ያለው እስከ ፍጻሜ ላገኙ ነገሮች መግለጫ

ፍጻሜ የሌለው እስከ ፍጻሜ ላላገኙ (ፍጻሜ ለሌላቸው) ነገሮች መግለጫ

ፍጻሜ ያለው ‹‹እስከ››

ምሳሌ፡-

‹‹እስክነግርህ ድረስ በግብጽ ተቀመጥ›› (ማቴ 12÷13)

‹‹ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ›› (ማቴ 12÷15)

‹‹ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፤ እርሱና የእስራኤል ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ›› (ኢያ 7÷6)

**ፍጻሜ የሌለው ‹‹እስከ››**

ምሳሌ፡-

‹‹ቁራም ውኃው በምድር ላይ እስኪደርቅ ድረስ ወዲያ ወዲህ ይል ነበር›› (ዘፍ 7÷8) የጥፋት ውሃ ከደረቀ በኋላስ ተመልሷልን? ይህ ቃል ቁራው ተመለስ ማለት ሳይሆን ለሁልጊዜ ወይም ጭራሽ አለመመለሱን ስለሚያመለክት ፍጻሜ የሌለው እስከ ይባላል፡፡

‹‹የሳኦል ልጅ ሜልኮልም እስከሞተችበት ድረስ አልወለደችም›› (2ኛ ሳሙ 6÷23) የሚለው ኃይለ ቀል ሜልኮል ከሞተች በኋላ ወልዳለች ማለት ነው? ከሞት በኋላ መውለድ የለም፡፡ (ማቴ 22÷30) ይህ ማለት ሜልኮል ለዘለዓለም ልጅ አልወለደችም ለማለት ነው፡፡ ከተረገመች ጊዜ አንሥቶ መካን ሆና እንደቀረች ለማመልከት ነው፡፡

‹‹እንሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ›› (ማቴ 28÷20) ከዓለም ፍጻሜ በኋላስ ከእነርሱ ጋር አይኖርም ማለት ነውን? ይህ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው

**የ‹‹አወቀ›› ትርጉም**

ተረዳ፣ ተገነዘበ፣ልብአለ፣አስተዋለ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ‹‹ኖህም ከወይን ጠጁ ስካር ነቃ ታናሹ ልጁ /ካም/ ያደረገበትን አወቀ›› (ዘፍ 9÷24) - ምን እንዳደረገበት ተረዳ፣ ተገነዘበ

ተገናኘ፣ በግብር አወቀ (በግብረ ሥጋ)

ምሳሌ፡- ‹‹አዳም ሄዋንን አወቃት›› (ዘፍ 4÷1)

ስለዚህ ‹‹አላወቃትም›› ሲል፡-በግብር እውቀት አላወቃትም ሊል ነው መልኳን አላወቀም/አልተረዳም/፡፡ በአንድ ኅብረ መልክዕ አላውቃትም፡፡ መልኳ ይለዋወጥ ነበርና ጌታን እንደጸነሰች ለማጠየቅ መልኳን ይለዋውጠው ነበር፡፡የብርሃን ጎርፍ ይፈስባት ነበርና፡፡ እንኳን የፀሐየ ጽድቅ ሰሌዳ የሆነች እመቤት ሙሴስ እግዚአብሔርን በማናገሩ ብቻ ስላናገረ ኃላፊ ብርሃን ቢሳልበት እስራኤል ‹‹ተገልበብ ለነ›› ተሸፈንልን ይሉት ነበር፡፡ (ዘጻ 34÷29)

አንድም፡- በነቢያት ወልድ የተባለ እርሱ ድንግል የተባለች እርስዋ እንደሆነች

አላወቁም ነበር፡፡

ምነው መልአኩ ነግሮት አልበረምን? ቢሉ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ‹‹አንድ ዓይን አያስረገጥ አንድ ምስክር አያስደነግጥ›› እንዲሉ ለምስክርነት አላወቃትም አለ፡፡

ምነው ዮሴፍ መልአኩ ባይነግረውስ ቀድሞ የተነገረውን ትንቢት አያውቅምን? ቢሉ ነቢያት (ነቢዩ) ድንግል አለ እንጂ እሷ ናት አላለውም ልጅ አለ እንጂ አምላክ አላለውምና፡፡

አንድም፡- ዮሴፍ በእጮኛ ስም ለእመቤታችን አገልጋይዋ፤ ተላላኪዋ፣ ሆኖ የተመረጠበት ምስጢር ምን እንደሆነ አላወቀም ነበር፡፡

መጻሕፍት በኩር ያሉትን ስሙን ኢየሱስ ያሉትን ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፡፡

ዮሴፍ 5 ነገሮች አይቶ እስኪረዳ ድረስ አላወቀም /አልተረዳም/

ምጽአተ ሰብአ ሰገል ዘምስለ አምኃ

ሑረተ ኮከብ በካልእ ፋና

ሥርቀተ ስብሐተ እግዚእ

ዓቢይ ቅዳሴ መላእክት

ፍርሃተ ኖሎት

# የማቴዎስ ወንጌል

## ምዕራፍ ሁለት

ማቴ 2÷1-2 ‹‹ኢየሱስም በይሁዳ ቤተልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ እንሆ ሰብአ ሰገል ‹የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው? ኮከቡን በምስራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናል› እያሉ ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ››

የይሁዳ ቤተልሔም ማናት? (ለምን ቤተልሔምን አነሣት?) ቢሉ

ከታች (በቁጥር 5፡6 ላይ) ‹‹ወአንቲኒ ቤተልሔም›› ‹‹አንቺ ቤተልሔም…›› ብሎ የሚያመጣት ስለሆነ ከዚህ ላይ አንሥቷታል፡፡

አንድም፡- የጌታችን የትውልድ ቦታ የይሁዳ ቤተልሔም ናት ሌላ ቤተልሔም

አለችና ከዚያ ሲለይ የይሁዳ ቤተልሔም ብሎ ጠቅሷታል፡፡ ሌላዋ

ቤተልሔም የዛብሎን ቤተልሔም ተብላ የምትጠራ ነች፡፡ ይህችም

ለዛብሎንና ለወገኖቹ ርስትነት የተሰጠች ነበረች (ኢያ 9÷15)

የይሁዳ ቤተልሔም ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ የምትገኝ ከተማ ከተማ ናት

አንድም፡- ትንቢቱን ምሳሌውን ይፈጽም ዘንድ

ትንቢቱ ምንድን ነው? ቢሉ (ሚክ5÷2)፣(ማቴ 2÷5)

ምሳሌውስ እንደምነው ቢሉ፡-

ታሪክ፡- ካሌብ ምድረ ርስትን ሰልሎ ሲመለስ (ከዚህ ቀደም ኢያሪኮን እንደሰለሉ) ‹‹ኬብሮንን›› ዓይቶ ለኢያሱ ‹‹ኬብሮንን ስጠኝ ቀድሞ ሙሴ አሰጥሃለሁ ብሎኝ ነበር፡፡ ከ12 ነገድ አንዱ እኔ ነበርኩ፤ ያን ጊዜ 40 ዘመን ሆኖኝ ነበር ዛሬም 80 ዘመን ይሆነኛል ከአንተ ጋር መውጣት መውረድ ይቻለኛል ጉልበት አለኝና ስጠኝ›› አለው፡፡ ኢያሱም በእስራኤል ምስክር ፊት ኬብሮንን ለካሌብ ሰጠው፡፡ ካሌብም ኬብሮንን እጅ አድርጎ ‹‹አዙባ›. የምትባል ሚስት አገባ፡፡ አዙባ ከጠላቶቹ ወገን ነበረችና ኬብሮንን በእርሷ ስም አላስጠራትም፡፡ ቀጥሎም ‹‹ከብታ›› የምትባል ሚስት አግብቶ በሚስቱ ስም ‹‹ከብታ›› ተብላለች፤ ከብታ ማለት ቤተ ስብሐት (ቤት የእመቤታችን፣ስብሐት የጌታ ምሳሌ) ማለት ነው፡፡ ከዚያም ‹‹ኤፍራታ›› የምትባል ሴት ሲያገባ በኤፍራታ ‹‹ኤፍራታ›› ተብላለች፤ኤፍራታ ማለት ደግሞ ፀዋሪተ ፍሬ (ፀዋሪት የእመቤታችን፣ፍሬ የጌታ ምሳሌ) ማለት ነው፡፡ ከብታ ከኤፍራታ ወንድ ልጅ ወለደ፡፡ በዚያን ወራት እጅግ ጥጋብ ሆኖ ስለነበር የልጁን ስም ‹‹ልሔም›› ብሎ ሰየመው ልሔም ማለት ኅብስት ማለት ነው፡፡ በልሔም ቤተ ልሔም ተባለች፡፡ (ቤት የእመቤታችን ልሔም የጌታ ምሳሌ) ኬብሮን 3 ስሞች አሏት ማለት ነው፡፡

ሄሮድስን ለምን አነሣው ቢሉ

ከታች (በቁጥር 17-18) ‹‹**ሕጻናቱን ይገድሉ ዘንድ አዘዘ**›› ብሎ ያመጣዋልና ነው

አንድም፡- ዘመን የሚቆጠር በንጉሥ ነውና

አንድም፡- ሄሮድስ የነገሠው በተንኮል ነበርና በሄሮድስ ላይ ሰማያዊ ንጉሥ መወለዱን ለማጠየቅ

ታሪክ፡- እስክንድር የሚባል ንጉሥ እስክንድርያ የምትባል ሴት አግብቶ አትሮብሎስን ሕርቃሎስን ማርያን ይወልዳል፡፡ ንጉሡ በሚሞትበት ጊዜ ለሚስቱ ‹‹ታናሹን አንግሠሽ ታላቁን ካህን አድርገሽ ኑሪ›› ይላታል አድልቶ አይደለም ታናሽየው ሕርቃሎስ ብልህና ሰው ማስተዳደር የሚያውቅ ስለነበር እንጂ፡፡ እንደነገራት አድርጋ ስትኖር ‹‹ሄሮድስ ወልደ ሐንደፊር›› የሚባል ንጉሥ የእስራኤልን መንግሥት በጣም ይመኘው ነበርና ለታላቅየው ለአትሮብሎስ መልዕክት ይልክበታል፡፡ ‹‹ታላቅ ሳለህ ታናሽ አዋቂ ሳለህ አላዋቂ አድርገውህ በአንተ ላይ ታናሽህን ያነገሡብህ ለምድን ነው?›› ጦር አንሶህ እደሆን ከእኔ ወስደህ ገድለህ ንገሥ ይለዋል አትሮብሎስም እውነት መስሎት ወንድሙን ገድሎ ነገሠ፡፡

ሚች ሕርቃሎስ አርሰጥአሎስ የሚባል ልጅ ነበረውና ለበቀል የአጎቱን የአትሮብሎስን ጆሮ ቆረጠው፡፡ እስራኤል አካሉ የጎደለ አያነግሡም ነበርና አርስጥአሎስን ሳያነግሡት ቀሩ መንግሥትም በመካከል ቀረች፡፡ ይሄኔ ሄሮድስ እህታቸው ማርያን አግብቶ ነገሠ፡፡ እርሱ በተንኮል በጥበብ የነገሥኩ ቢመስለው ‹‹መንግስት ከቤተ ይሁዳ አይወጣም›› የተባለው ይፈጸም ዘንድ በንጉሥ ሄሮድስ ላይ ሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ ተወለደ ለማለት ሄሮድስን አነሣው፡፡

ሰብአሰገል እነማን ናቸው?

ሰብአሰገል፡- ማለት የጥበብ ሰዎች ማለት ነው

‹‹የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው?››

ምነው ኮከቡ ይመራቸው አልነበረምን? መጠየቅ ለምን አስፈለጋቸው ቢሉ፡-

ከሰው ሲደርሱ ይሰውራቸው ነበርና

ስለምን ‹‹ንጉሥ›› አሉ ከፍ ብለው ‹‹አምላክ›› ዝቅ ብለው ‹‹ሕጻን›› ለምን አላሉም ቢሉ፡-

‹‹ንጉሥ›› የሚለው ስም ማዕከላዊ ነውና እሱን ገለጸላቸው

ስም ላዕላዊ - አምላክ ማለት ነው

ስም ማዕከላዊ - ንጉሥ ማለት ነው

ስም ታህታዊ - ህጻን ማለት ነው

‹‹የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ›› ከማለት ‹‹የአይሁድ አምላክ፤ የአይሁድ ፈጣሪ›› ብለው ጠይቀው ቢሆን ‹‹እኒህ ሞኞች፣ተላሎች ሰማይና ምድር የማይችሉትን ማን ችሎ ተወለደ? ባሏቸው ነበርና፡፡

ስሞ ታህታዊ ተገልጸላቸው ‹‹የተወለደው የአይሁድ ሕጻን›› ብለው ጠይቀው ቢሆን ‹‹እኔህ ሞኞች ተላሎች በእስራኤል ከተማ እልፍ ተወልዶ፤ እልፍ ሞቶ ያድራል ስንቱን እናውቅላቸዋለን›› ባሏቸው ነበር፡፡

ሰብአሰገል እጅ መንሻ ይዘው ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፡፡አመጣጣቸውስ እንደምን ነው? ቢሉ፡-

ታሪክ፡- መላእክት ሦስቱን ንዋያት (ወርቅ፣ እጣን፣ከርቤ) ለአዳም ሰጡት፡፡ አዳም ለሔዋን እያለ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ከሰብአ ሰገል አባት ከዤረደሼት ደረሰ፡፡ ዤርደሽት ፈላስፋ ነበር ከውኃ ምንጭ አጠገብ ሆኖ ሲፈላሰፍ ድንግል በሰሌዳ ኮከብ ተሰላ ሕጻን ታቅፋ አየና ፈጥሮ በሰሌዳ ብርት ቀርጾ አስቀመጠው፡፡ ዤረደሽት የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ ልጆች (ሰብአ ሰገልን) ጠርቶ ‹‹ እንዲህ ያለ (የሚመሰል) ኮከብ ባያችሁ ጊዜ ሰማያዊ ንጉሥ ይወለዳልና ወስዳችሁ ስጡት ብሎቸው ነበርና ያን የመሰለ ኮከብ ስላዩ መጥተዋል፡፡

‹‹ኮከቡን››ሲል

በተፈጥሮ ገንዘቡ የሚሆን ሲል ነው

አንድም፡- አምሳያው የሚሆነው ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናል ሲሉ ነው፡፡

ሰብአሰገልን ሲመራቸው የነበረው በቁሙ ኮከብ ነውን ወይስ መልአክ?

ሁለት ትርጓሜ አለው

መልአክ ነበር ይህ በምን ይታወቃል ቢሉ?

ኮከብ በሌሊት እንጂ በቀን (በመዓልት) አይታይም

አንድም፡- ኮከብ መጥቶ ይሄዳል እንጂ ቆሞ (ዘቅዝቆ) በቆመ ብእሲ አይሄድምና፡፡

አንድም፡- ኮከብ ነው፡፡ በሌሊት የሚታየውን በቀን (በመዓልት) እንዲታይ ወደ ቁልቁል የሚሄደውን (የሚወርደውን) ወደ ላይ እንዲወጣ መጥቶ የሚሄደውን በሰው ቁመት እንዲሄድ የሚያደርግ እርሱ ነውና በቁሙ ኮከብ ነው፡፡

**ለምን በኮከብ መራቸው? ቢሉ**

ኮከብ ያመልኩ ነበርና በሚያውቁት ለመሳብ (በለመዱት ለመሳብ)

ለሰብአ ሰገል እንዲገለጽላቸው ያደረገው ለምንድን ነው ቢሉ?

አባታቸው ነግሯቸው ነበርና ይሹት፤ ለፍቅሩም ይሳሱ ነበርና

አንድም፡- ክህደት ጸንቶባቸው ነበርና ጌታ ክህደት ወደ ጸናበት ቦታ መሄድ ልማዱ ነውና፤በመዋዕለ ስደቱ ክህደት ወደ ጸናችባቸው ወደ ግብጽ እንደሄደ

አንድም፡- በእስራኤል ዘለፋ ለአህዛብ ተስፋ ለመሆን

‹‹እኛ እንኳን አውቀን ስንመጣ እስከ አሁን ሳያውቁት›› እንዲሉ

አንድም፡- ነገሥት ፋርስ ለጸብ እንጂ ለፍቅር አይመጡም ነበርና በጌታ ልደት ፍቅር እንደተጀመረ ለማጠየቅ

አንድም፡- የራሱን (የአባቱን) ገንዘብ ለመቀበል

ማቴ 2÷3 ‹‹ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ ኢየሩሳሌምም ከእርሱ ጋር››

ሄሮድስና ሕዝቡ (ኢየሩሳሌም) መደንገጣቸው ስለምን ነው?

ሄሮድስ፡- የተወለደው ንጉሥ ከሆነ እኔን ሳይገድል ይነግሣልን? ብሎ ነው

ሕዝቡ (ኢየሩሳሌም)፡- ሕዝቡ የደነገጡት ደግሞ ጦርነት ጸንቶባቸው ነበርና ነው

አንድም፡-ሰብአ ሰገል 3ቱ ነገሥታት ናቸው ይላቸዋል፡፡ እነዚህ ነገሥታት

(ስማቸውም፡- ማንቲሱሆር፣ በዲዳስፋና ሜልኩ ይባላሉ) እልፍ

ሠራዊት አስከትለው መጥተው ነበርና በዚህ ምክንያት ሄሮድስና

ሕዝቡ ደነገጡ፡፡

ተአምረ ኢየሱስ 3 ናቸው፡ሲል ትርጓሜ ወንጌል 12 ይላል አይጣላምን? ቢሉ አይጣላም፡- ከሀገራቸው 12 ሆነው ተነሥተው ፈለገ ኤፍራጥስ ሲደርሱ 9ኙ ተመልሰዋል፡፡

በምን ምክንያት ተመለሱ? ቢባል

ወደ ኋላ ጦር ተነሣባቸሁ፡ብለዋቸው ‹‹ፍርኻቡር›› በሚባል አዛዥ ተመልሰዋል

አንድም፡- ስንቅ አልቆባቸው

አንድም፡- ኢየሩሳሌም ጠባብ ናት ለሰፈር አትበቃም ብለዋቸው

ምስጢሩ ግን፡- ከበረከቱ ልደቱ እንዳላሳተፋቸው ያጠይቃል፡፡

ማቴ 2÷4፡- ‹‹የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንደሚወለድ ጠየቃቸው››

ሊቀ ካህናቱ አንድ አይደለምን? ለምን የካህናት አለቆች አለ ቢሉ?

አንዱ ሹም ሌሎቹም የሹም ሽር ሆነው ተሹመው ነበርና

ጸሕፍት የሚላቸው እነማንን ነው? ቢሉ

ከ12ቱ ነገደ እስራኤል ተውጣጥተው ‹‹ርስት ከርስት፤ነገድ ከነገድ፤ ትውልድ ከትውልድ እንዳይፋለስ የሚጽፉ፤ በተለይም ‹‹ክህነት ከቤተ ሌዊ፣ መንግሥት ከቤተ ይሁዳ እንዳይወጣ የሚጽፉ ናቸው፡፡

ስለዚህ ሄሮድስ ከሹም ሽር ሊቃነ ካህናት ከጻሐፍት ወግ አይታጣም ብሎ ሰበሰባቸው፡፡

ማቴ 2÷5-6 ‹‹እነርሱም ‹አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገገሮች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እስራኤል የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና› ተብሎ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት፡፡››

ትንቢቱን የተናገረው ሚኪያስ ነው (ሚኪ 5÷2)

ታሪክ፡- ነቢዩ ሚኪያስ ሌላውን ሲያስተምር ውሎ ወደ ማታ በቤተ ልሔም በኩል ሲያልፍ ቤተ ልሔም ተፈታ፤ ምድረ በዳ ሆና፤ ቋያ በቅሎባት አየ፡፡ ‹‹እንዲህ ሆነሽ አትቀሪም ንጉሥ ይነግሥብሻል፤ የነጋሪት ድምጽ ይሰማብሻል፤ድንኳን ይተከልብሻል፤እስራኤል ደጅ ይጠኑብሻል፤አሕዛብ ይገብሩብሻል›› ብሎ ትንቢት ተናግሯል፡፡

ነቢዩ የተናገረው ያልቀረም፡- ዘሩባቤል ነግሦባታል፤ እስራኤል ደጅ ጠንተውበታል፤ የነጋሪት ድምጽ ተሰምቶባታል፤ አሕዛብ ገብረውባታል፤ ድንኳን ተተክሎባታል ፡፡

አንድም፡- ወገኖቼ እስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ክርስቶስ ባንቺ

ይወለዳልና

ዘሩባቤል እንደነገሠ - ጌታ ተወልዶባታልና

ድንኳን እንደተተከለ - የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል

ነጋሪት እንደተሰማባት - ቅዳሴ መላእክት ተሰምቶባታል

እስራኤል ደጅ እንደጠኑባት - 99 ነገደ መላዕክት ደጅ ጠንተውባታል

አሕዛብ እንደገበሩባት - ሰብአ ሰገል ገብረውባታልና

አንድም፡- አንቺ የኤፍራታ ልጅ እመቤታችን በይሁዳ ከነገሡ ነገሥታት

ብትበልጭ እንጂ አታንሺም፤ ወገኖቼ እስራኤል ዘነፍስን

የሚጠብቃቸው ንጉሥ ክርስቶስ ባንቺ ባህርይ ከአንቺ ይወለዳል፡፡

ማቴ 2÷7፡-‹‹ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ ጠይቆ ተረዳ››

ለምን በስውር ጠራቸው ቢሉ

ካህናት ‹‹አሁን ከእኛ ጠይቆ ይነግራቸዋልን? እንዳይሉት

አንድም፡- ውዳሴ ከንቱ ሽቶ ‹‹ሰብአሰገል እኛ እንኳን አውቀን ስንመጣ እሱ ከዚህ ሆኖ እስከ ዛሬ ሳይሰማ ኖሯል?›› ይሉኛል ብሎ

ጠይቆ ተረዳ ያለው ምኑን ነው? ቢሉ

‹‹ይህን ኮከብ ካያችሁ ምን ያህል ዘመን ሆኗል? አላቸው ‹‹ሁለት ዓመት ሆኖታል›› አሉት፡፡ እሱም ‹‹ለካ ያም ብላቴና ሁለት ዓመት ሆኖታል›› ብሎ ተረዳ ፡፡

ማቴ 2÷8፡- ‹‹ወደ ቤተልሔምም እነርሱን ሰደደ ፤ ‹ሂዱ ስለ ሕጻኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁት ጊዜም

እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ› አላቸው››

‹‹**መጥቼ እንድሰግድለት**›› ማለቱ የምጸት አነጋገር ነው

አንድም ፡-እሰግድለት ዘንድ አለ እገድለው ዘንድ ማለቱ ነው

አንድም፡- ‹‹እኛ ብቻ መስሎን ለካ የሀገሩም ሰዎች የሀገሩም ነገሥታት ያምኑበታል›› ብለው ሰብአ ሰገል እምነታቸው እንዲጸናላቸው መንፈስ ቅዱስ አፉን ከፍቶ ፊቱን ጸፍቶ ሲያናግረው ነው፡፡

ሄሮድስ ከሰብአ ሰገል ጋር ሄዶ አይገድለውምን ሰብአ ሰገልን ለምን ላካቸው ቢሉ?፡-

ካህናቱ ዘመዶቼ ናቸውና ቀድመው ልከው ያሸሹብኛል ብሎ ነው፡፡

አንድም፡- ሰብአ ሰገል ይገላግሉኛል ብሎ አይሆንም ያልኳቸው እንደሆነ እልፍ

እእላፍ ሠራዊት አስከትለው መጥተዋልና ይጣሉኛል ብሎ ፈርቶ

ማቴ 2÷9፡- ‹‹**እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ፡፡ እነሆም በምስራቅ ያዩት ኮከብ ሕጻኑ ካለበት ቦታ ላይ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር**››

ኮከቡ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት በሰው ቁመት ተዘቅዝቆ ቆመ፡፡

ማቴ 2÷10፡- ‹‹**ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው**››

ከሰው ሲደርሱ ይሰውራቸው፣ ከሰው ሲለዩ ይመራቸው ነበርና አሁን በከተማው በሰው መካከል ቢገለጽላቸው ፈጽሞ ደስ አላቸው፡፡

አንድም፡- አንኳን 2 ዓመታት የሄዱለት ነገር 2 ሰዓት የሄዱበት ነገር ሲፈጸም

ደስ ያሰኛልና ደስ አላቸው፡፡

አንድም፡- እንዲሁ መርቶ ከምን ያደርሰን ይሆን? ከባህር ይጥለን፣ከገደል

ይጥለን? ብለው ነበርና ካሰቡት ቢያደርሳቸው ፈጽሞ ደስ አላቸው፡፡

ማቴ 2÷11፡- ‹‹ወደ ቤትም ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፡ወድቀውም ሰገዱለት፡፡ ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት››

‹‹**ወደ ቤትም ገብተው**››

ማቴዎስ፡- ቤት፣ በዓት ይላል፡ ሉቃስ ጎል (ግርግም) ይላል አይጣላምን? ቢሉ አይጣላም፡-

ቤት፡- ቢል ዮሴፍ እንደ ዳስ አድርጎ ጥሎ ነበርና

በዓት፡- ቢል ኢዮሲያስ በጨው ግንብ አሰርቶ ነበርና፤ ጨውን ሲልሱ እንስሳት እየጋጡ አጎድጉደውት ነበርና

*ጎል፡- ያለ እንደሆነ የተመቸ ነው የእንስሳት ማደርያ ሆኖ ነበርና፡፡*

**‹‹ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት››**

*ኮከቡን አይተው አምሳያው ሆኖ አገኙት ደስም አላቸው፡፡*

**‹‹ወድቀውም ሰገዱለት››**

*ከፈረስ ከሰረገላ ወርደው ሰገዱለት*

*አንድም፡- መልሰው መላልሰው ሰገዱለት*

*ሐተታ፡-እንደ ጥንት ነገሥታት ወግ፡- ንጉሥ ጋር ሲደርስ ይሰግዳል፡ የታዘዘ ብላቴና መጥቶ ተነሥ ብለውሃል ይለዋል፡፡ ዳግም እልፍ ብሎ ይሰግዳል፡፡ አሁንም ተነሥ ብለውሃል ይለዋል፡፡ እንዲህ እያለ ከንጉሥ ሲደርስ እጅ ነሥቶ በቀኝ አብሮ ይቀመጥ ነበርና በዚያ ልማድ ‹‹ወድቀው ሰገዱለት›› አለ*

**‹‹ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት››**

**‹‹ወርቅ አመጡለት››**

*ይህን የምንገብርላቸው ነገሥታት ቀድሞም ፍጡራን ኋላም ኃላፊያን ናቸው አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርክ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ*

**‹‹ዕጣን አመጡለት››**

*ይህን የምናጥናቸው ጣኦታት ቀድም ፍጡራን ኋላም ኃላፊያን ናቸው አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርክ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ*

**‹‹ከርቤ አመጡለት››**

*ምንም ቀድሞም ያልተፈጠርህ ኋላም የማታልፍ ብትሆንም በመስቀል ጊዜ በሰውነትህ መራራ ሞትን መቀበል አለብህ (ትቀበላለህ) ሲሉ*

*አንድም፡- ወርቅ ጽሩይ ነው፡- ጽሩየ ባሕርይ ነህ ሲሉ፣ ዕጣን ምዑዝ ነው፡- ምዑዘ ባሕርይ ነህ ሲሉ፣ ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል፡ የተለያየውን አንድ ያደርጋል፡- አንተም ከማኅበረ መላእክት የተለያየ አዳምን አንድ ታደርገዋህ፡፡ ጽንዓ ነፍስን ሰጥተህ ታጸናዋለህ ሲሉ*

*አንድም፡- ወርቅ ጽሩይ ነው፡- ባንተ ያመኑ ምእመናን ጽሩያነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው ሲሉ፣ ዕጣን ምዑዝ ነው ፡- ባንተ ያመኑ ምእመናን ምዑዛነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው ሲሉ፣ ከርቤ በዕለተ ዓርብ ያቀምሱታልና*

*አንድም፡- ወርቅ፡- የሰማዕታት ምሳሌ ነው ‹‹ከመ ወርቅ ፈተኖሙ ለሰማዕት›› እንዲል በእሳት ይፈተናሉና ዕጣን፡-የባሕታውያን፡ ‹‹ዕጣን ከሩቅ እንደሚሸት ባሕታውያንም በተስፋ ይኖራሉና›› ከርቤ፡- የምእመናን ‹‹ምእመናን በፍቅር አንድ ይሆናሉና››*

አንድም፡- ወርቅ፡- የሃይማኖት ምሳሌ ነው፡፡ ወርቅ ጽሩይነቱም ግብዝነቱም የሚታወቅ በእሳት ሲፈተን ነው፡ የሃይማኖትም ጥንካሬና ድክመቱ የሚታወቀው መከራ ሲቀበሉበት ነው፡፡ዕጣን፡- የተስፋ ምሳሌ ነው ዕጣን ከሩቅ እንዲሸት ተስፋም ያልያዙትን እንደያዙት ያላዩትን እንዲያዩት ታደርጋለችና፡፡ ከርቤ፡-የፍቅር ምሳሌ ነው፡፡ ከርቤ የተሰበረውን እንደሚጠግን የተለያየውን አንድ እንደሚያደርግ ፍቅርም አንድ ታደርጋለች ሃይማኖት፡ ፍቅር ፡ ተስፋ ያንተ ገንዘብ ናቸው፡ ሲሉ ወርቅ ዕጣን ከርቤ ገብሩለት፡፡

ማቴ 2÷12 ‹‹**ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ ሃገራቸው ተመለሱ**››

**‹‹በሌላ መንገድ ወደ ሃገራቸው መሄዳቸው ስለምንድን ነበር ቢሉ››**

ሄሮድስ ከነገ ከሠለስት ይመጣሉ ሲል እመቤታችን መንገድ እንድትገፋ

አንድም፡- ሃይማኖት እንዲሰፋ ነው፡፡ በመጡበት የተመለሱ እንደሆነ ሃይማኖት ይጸናል እንጂ አይሰፋም ባልመጡበት ቢመለሱ ግን ያልሰማው እየሰማ ሃይማኖት ይሰፋል፡፡

አንድም፡- መንገድ እንዲቀርባቸው ፡፡ በሌላ መንገድ ሁለት ዓመት የመጡትን በ40 ቀናት ገብተዋልና

አንድም፡- በሌላ መንገድ(ጎዳና) ማለቱ በሌላ ኃይለ ቃል ሲል ነው፡፡ ‹‹አይቴ ሃሎ››፡‹‹ወደየት አለ?›› እያሉ መጥተው ነበርና ‹ረከብናሁ አገኘነው›› እያሉ ተመልሰዋና

አንድም፡- በሌላ ሃይማኖት ሲል ነው ‹‹ንጉሥ›› እያሉ መጥተው ‹‹አምላክ›› እያሉ ተመልሰዋልና

ማቴ 2÷13፤- ‹‹እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕጻኑን ሊገድው ይፈልገዋልና ተነሳ፣ ሕጻኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ፣ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው››

መልአኩ ለዮሴፍ ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ የነገረው፤ እያሉ ያልነገራቸው ለምንድን ነው? ቢሉ

ሰብአሰገል ሳሉ ነግሮት ቢሆን ሲሰደድ አይተው አምክነቱን በተጠራጠሩ ነበርና፡፡

አንድም፡- መሰደዱስ ካልቀረ ይዘነው እንሂድ ባሉ ነበርና ይዘውትም እንዳይሄዱ የጌታ ስደት ወደ ግብጽ እንጂ ወደ ሌላ (ባቢሎን) አይደለምና፡፡

**‹‹ሕጻኑንና እናቱን ይዘህ ….››**

**‹‹ሕጻኑን››** ብሎ **‹‹እናቱን››** ቢተው ህጻኑን አለኝ እንጂ እናቱን አለኝን? ባለ ነበር

**‹‹እናቱን››** ብሎ **‹‹ሕጻኑን››** ባይል እናቱን አለኝ እንጂ ብላቴናውን አለኝን? ባለ ነበርና

**‹‹ሕጻኑን እና እናቱን››** አለው

አንድም፡- መልአክ መሆኑን ለማጠየቅ

ሰይጣን ቢሆን አመላክቶ ይተዋል ለመልአክ ግን አካቶ መናገር ልማድ ነውና መልአክ መሆኑን ለማጠየቅ ‹‹**ህጻኑንና እናቱን**›› አለ፡፡

ማቴ 2÷14-15፡- ‹‹**እርሱም ተነሥቶ ሕጻኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት የተባው እንዲፈጸም ወደ ግብጽ ሄደ፤ ሄሮድስም እስኪሞት በዚያ ኖረ፡፡**››

ኮብላይ ለልማዱ መንገዱ ሌሊት ነውና በሌሊት ሄደ ሲል ነው፡፡ መልአኩ እንደነገረው ወዲያውኑ ሳይውል ሳያድር በሌሊት ሄደ ሲል ነው፡፡

‹‹**ከጌታ ዘንድ በነቢይ**›› ማለቱ

እግዚአብሔር በነቢይ አድሮ ሲል ነው

አንድም፡- ነቢይ ከእግዚአብሔር ተገልጾለት

በነቢዩ ቃል ‹‹**እስራኤል ህጻን በነበረ ጊዜ ወደድሁት ልጅንም ከግብጽ ጠራሁት**›› ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ (ሆሴ 11÷1)

ትንቢቱማ ከግብጽ መውጣቱን እንጂ መውረዱን (መሰደዱን) አያመለክትም ቢሉ፡- ካልወረዱ መውጣት የለምና እንዲህ አለ

ስደቱን ወደ ግብጽ ያደረገው ስለምንድን ነው? ቢሉ ትንቢቱን ምሳሌውን ሊፈጽም

ትንቢት፡-‹‹ወይወርድ እግዚእነ ወስተ ምድረ ግብጽ እንዘ ይጼዓን ዲበ ደመና ቀሊል›› ‹‹እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብጽ ይመጣል›› ኢሳ 19÷1 ይህማ የተነገረው ለያዕቆብ አይደለምን ቢሉ? ለጊዜው ለያዕቆብ ቢሆንም ፍጻሜው ግን ለጌታ ነው፡፡

አንድም፡- ዘፍ 15÷13 ‹‹…ዘርህ ለእነርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፡፡ ባርዎችም አድርገው 400 ዓመታት ያስጨንቋቸዋል፡፡›› ብሎ ለአብርሃም ነግሮት ነበርና ጌታም የአብርሃም ዘር ነውና ወደ ግብጽ ተሰደደ፡፡

ፍጻሜው እንደምን ነው ቢሉ? ግብጽ ታቀርበዋችና ፡ ይሸፕታልና ለፍቅሩ ይሳሳሉና

አንድም፡- በግብጽ ክህደት ጸንቶ ነበርና ወደ ጸናበት መሄድ ልማድ ነውና

ከስር በመዋዕለ ስብከቱ ‹‹ደዌ ወደ ጸናባቸው ወደ ጌርጌሴኖን ሄደ›› ብሎ እንደሚያመጣው

አንድም፡- ገዳማተ ግብጽን ለመባረክ

በግብጽ እነ ገዳመ ሲሐት፣ እነ ገዳመ አስቄጥስ፣ አሉና እኒህን ለመባረክ

አንድም፡- ኪዳነ መልከጼዴቅን ለመፈጸም

‹‹ዘመዶቼን ማርልኝ›› ቢለው ‹‹ልጄን በሥጋ ሰድጄ እምርልሃለው›› ብሎት ነበርና

አንድም፡- ሃይማኖት ከሁሉ ሲጠፋ በግብጽ አይጠፋምና እስከምጽአት ድረስ ወልድ ዋሕድ ስትል ትኖራለችና

መሰደዱ ስለምን ነው ቢሉ?

**እንዳይሞት**

**ጊዜው አልደረሰምና**

ከቤተልሔም ሆኖ ድኖ ቢሆን ኖሮ ‹‹**ይህማ ምትሐት ነው ባሉ ነበርና**››

አንድም፡- አዳምን እንደካሰ ለማጠየቅ አዳም ከዚህ ዓለም አፍአ ከምትሆን ከገነት ተሰዶ ነበርና ለዚያ እንደ ካሰ ለማስረዳት

አንድም፡- ለሰማዕታት ስደትን ለመባረክ ሰማዕትነት በእሳት፣ በስለት ብቻ አይደለም እንደነ ገ/ክርስቶስ አገር ጥሎ መሰደድም ሰማዕትነት ነውና

አንድም፡- ኢጋንንትን ከሰው ልቡና አስወጥቶ ለመስደድ

ከዚህ ሲደርሱ የጌታን ስደት መተረክ ይገባል (ራዕ 12÷1-17) ፣ ቅዳሴ ማርያም ገጽ 235፡- ‹‹አዝክሪ ድንግል ንግደቶ ዘምስሌኪ እንዘ ትኀይዱ ምስሌሁ እምሀገር ለሃገር በመዋእለ ሄሮድስ ርጉም›› እንዳለ

ማቴ 2÷16፡- ‹‹ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአሰገል እንደተሳለቁበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣና ልከ ከሰብአ ሰገል እንደተረዳው ዘመን በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕጻናትን ሁሉ አስገደለ››

**‹‹እንደተሳለቁበት ባየ ጊዜ››**

በአንተ በኩል እንመላለሳን ብለው በሌላ ጎዳና እንደሄዱ በሰማ ጊዜ ‹‹**እጅግ ተቆጣና....**››

ያስቆጣልን? ቢሉ ኢያስቆጣም፡- ተቆጪ ለልማዱ ባልጋው በመከዳው በቤተሰቡ ይቆጣልና ‹‹**የጨለማ ገልማጭ**›› እንዲሉ

ማቴ 2÷17-18፡- ‹‹**ያን ጊዜ በነቢዩ ኤርሚያስ ድምጽ ተሰማ፤ ለቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤መጽናናትንም አልወደደችም፡ የሉምና**›› የተባለው ተፈጸመ፡፡››

**‹‹ቃል ተሰምዓ በራማ...››**

ራማ፡- በቁሙ ሰማይ ማለት ነው

ሰማይ ሲል፡-

አንድም፡- ከፍ ካለ ቦታ ማለት ነው

አንድም፡- በመላእክት ዘንድ ማለት ነው

አንድም፡- በእግዚአብሔር ዘንድ ማለት ነው

‹‹**ብካይ (ልቅሶ)**››፡- የልጆቻቸው ከእናቶቻቸው ሲለይዋቸው

‹‹**ወሰቆቃወ (ዋይታ)**››፡- የእናቶቻቸው - ከልጆቻቸው ሲለይዋቸው

‹‹**ወገዓር (ጩኸት)**››፡- ልጆቹን ጠምዘው ሲያርዷቸው

‹‹ወሕማም ብዙኅ (ብዙ ሕመም)፡- 9ወር ከ5 ቀን የጸነሰ ማሕጸን አይችልምና

‹‹ራሔል እንዘ ትበኪ በእንተ ውሉዳ ማለት ራሔል ለልጆቿ ስታለቅስ ተሰማ›› ያለው ተፈጸመ

ራሔልን ለምን አነሣት? ልያን ለምን አላነሣም? ቢሉ

የልያ ዕጻዋ ነው ጌታ ከርሷ ወገን ተወልዷልና የራሔል ግን ያለ ዕጻዋ ነው ጌታ ከርሷ ወገን አይወለድምና፡፡

አንድም፡- የልያ በርህቀተ ሀገር (በቦታ ርቀት ምክንያት) ብዙ ድነውላታል የራሔል ግን በማነስ (በቅርበት) አልቀውባታል፡፡

አንድም፡- በራሔል የልያን መናገር ነው

አንድም፡- ‹‹እናታችን ራሔል ኑራልን መከራችንን አይታ አልቅሳልን›› ብለው ስሟን ጠርተው ስላለቀሱ

አንድም፡- ‹‹የሚድኑ መስሏቸው ከመቃብረ ራሔል ብዙዎቹ ገብተው ተደብቀው ነበር፡፡ ከዚያ እየገቡ ፈጅተዋቸዋልና

አንድም፡- በራሄል ሁሉን መናገር ነው

‹‹ይህማ ከሆነ ሁሉን በሚያገናኝ በያዕቆብ አይናገረውም ነበርን?›› ቢሉ፡-

ወንድ ልጅ ለፈረስ፣ ሴት ልጅ ለበርኖስ ከደረሱ በኋላ የሞቱ እንደሆነ ኃዘን በአባት ይጸናል፡፡ በሕጻንነት የሞቱ እንደሆነ ግን ኀዘን በእናት ይጸናልና በዚህ ልማድ በሚጸናው ለመናገር ነው፡፡

አንድም፡- ግፍ ለግፍ ሲያነጻጽር ነው

ታሪክ፡- እስራኤል በግብጽ አገር በባርነት ሳሉ ራሔል የምትባል ሴት ባሏ ሮቤል (ስምዖንም ይባላል) ሞቶ ‹‹በእርሱ ምትክ ጭቃ እርገጭ›› ብለዋት ስትረግጥ መንታ ጸንሳ ኖሮ ወጥተው ወጥተው ወደቁ፡፡ ደንግጣም ቆመች፡፡ አሰሪዎቿም ‹‹የሰው ደም ያጸናዋል (ያጠነክረዋል) እንጂ ምን ይለዋል? ›› በማለት ልጆቿን እንድትረግጥ አስገደዷት፡፡ ራሔልም ‹‹ኢሃሎኑ በዝ ሰማይ አምላከ እስራኤል አዶናይ›› ብላ እንባዋን በእጇ ተቀብላ ወደ ላይ ረጭታዋለች፡ ኀዘንዋም ቅድመ እግዚአብሔር ደረሰ፡፡ ፈጣሪም ‹‹ሰማዕኩ ገዓሮሙ ለሕዝብየ ወወረድኩ ከመ አድኅኖሙ›› (ዘጸ 3÷7) ‹‹በግብጽ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፤ ጩኸታቸውንም ሰማሁ አድናቸውም ዘንድ ወረድኩ›› ያሰኘው ይኸው ነው፡፡ ‹‹ራሔል ልቅሶ መተውን መጽናናትን እምቢ›› አለች፡፡ በራሔል የደረሰ ግፍ ያሳዝናልና ለማነጻጸር አነሣት

በቤተልሔምም፡- ግፏ ያሳዝናልና፡ የጻር ሞት ነውና፣ ኀዘን በየደጅ ሆኖአልና ለማነጻጸር ራሔልን አነሣት

አንድም፡- ራሔል ልጆቿ ልጆች አልሆኗትም በቤተልሔም ልቻቸው ልጆች ያይደሉ የተውሶ ናቸውና ይህን ሲያነጻጽር ነው

አንድም፡- ራሔል መንግሥተ ሰማያት የሚገባባት አጥታ ታዝናለች ታለቅሳለች፡፡

ሄሮድስ ሕጻናቱን እንዴት ሰበሰባቸው?

ሄሮድስ ‹‹ቄሳር ሕጻናትን ሰብስበህ ልብስ፣ ምግብ እየሰጠህ፣ በማር በወተት አሳድገህ፣ ለእናት ለአባታቸው ርስት ጉልት እየሰጠህ፣ ጭፍራ ሥራልኝ ብሎኛል›› ብሎ አዋጅ አስነገረ፡፡ በዚህም መሰረት ልጅ ያላት ልጇን የሌላት ልብስ ምግብ ልትቀበልበት ብላ እየተዋሰች ይዛ ሄዳለች፡፡ እንዲህ አድርጎ ከሰበሰባቸው በኋላ ፈጅቷቸዋል፡፡

ለሕጻናቱ እልቂት ተጠያቂው ማነው? ሄሮድስ ነው ወይስ ጌታ?

ለሕጻናቱ እልቂት ተጠያቂው ሄሮድስ ነው

1 ሳሙ22÷18፡- በዳዊት ምክንያት 85 ሌዋውያን ቢያልቁ ዕዳው በሳኦል እንደሆነ

ሐዋ 12÷19፡- በቅዱስ ጴጥሮስ ምክንያት 16ቱ የወህኒ ጠባቂዎች ቢያልቁ ዕዳው በሄሮድስ ሆነ እንጂ በዳዊትና በቅዱስ ጴጥሮስ ላይ እንዳልሆነ ዕዳው በሄሮድስ ነው የሆነው በጌታ ዕዳ የለበትም፡፡

ሳኦልና ሄሮድስ ሳያውቁ ነው ጌታ ግን እያወቀ ነው ቢሉ? ጌታ ማወቁን ያውቃል፡፡ሁሉን ያውቃል በሰማዕትታቸው መጠቀማቸውን፣ ክብር እንደሚሆናቸው ያውቃል፡፡ እኒህ ህጻናት ስንክሳር ተጽፎላቸዋል፣ ታቦት ተቀርጾላቸዋል፣ አብያተ ክርስቲያናት ታንጾላቸዋል፡፡

ማቴ 2÷19-20 ‹‹**ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብጽ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ "የሕጻኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሳ፡፡ ሕጻኑንም እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ"**›› አለው››

‹‹**የሕጻኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ**››

የዚህን ብላቴና ሰውነት ለጥፋት የሚሹዋት ሰዎች ሞተዋልና ማለቱ ነው

አንድም፡- ጌታ ነፍስ እንደነሣ ለማጠየቅ ፣‹የዚህን ሕጻን ነፍስ› አለ

ምነው የሞተ አንድ ሄሮድስ አይደለምን ‹‹ሞተዋልና›› ብሎ አበዛ (በብዙ ቁጥር ተናገረ) ቢሉ፡- የምክር ጋናቸው እርሱ ነው እርሱ ከሞተ ያረሡታል ብሎ

አንድም፡- በ3 ዓመት ከመንፈቅ እንኳን በዓላውያን ከተማ በምዕመናን ከተማ

ብዙ ሰዎች ይሞታሉና እሱን የመሰሉ ብዙ ሰዎች ሞተዋልና ሞቱ አለ፡፡

ማቴ 2÷21-22፡- ‹‹**እርሱም ተነሥቶ ሕጻኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ፡፡ በአባቱም በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደነገሠ በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄድን ፈራ ‹‹በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ**››፡፡

ዮሴፍ ወደ ይሁዳ ለመሄድ ለምን ፈራ ?

የክፉ ልጅ ክፉ ነውና እሱስ የአባቱን ክፋት ይተዋልን? ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድን ፈራ

አንድም፡- ልጆቻቸው የሞቱባቸው የይሁዳ ሰዎች ‹‹**ልቻችን ያለቁት በእርሱ**

**ልጅ ምክንያት አይደለምን?**›› ብለው ይጣሉኛል ብሎ ፈራ፡፡

**ማቴ 2÷23፡- ‹‹በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ፡፡››**

ትንቢቱ፡- ‹‹**ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ**›› ‹‹**ልጄ እንደ ሳምሶን ናዝራዊ ይባላል**›› የሚል ነው፡፡ እንዲህ የሚል ትንቢት ከምን ላይ አምጥቶ ጻፈው ቢሉ በ66ቱም በ81 መጻሕፍት አይገኝም፡፡ በምርኮ ጊዜ ጠፍቷል፡፡ ይኸም ከ66ቱ መጻሕፍት በቀር ሌላ አንቀበልም ለሚሉ ወገኖች ማስረጃ እንደሆነ እናስተውል፡፡

አንድም፡- ዕዝራ ተናግሮት ሳይጻፍ ቀረ እና በትውፊት ከሐዋርያት የደረሰ

ትንቢት ነው፡፡

ተናግረውት ሳይጻፍ የቀረውን ማምጣት የሐዋርት ልማድ መሆኑን ሲያጠይቅ ነው፡፡

ትንቢቱ የተነገረ ለሶምሶን አይደለምን ቢሉ፡-

ለጊዜው ለሶምሶን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነው

ሳምሶን በተናቀች መንስከ አድግ (የአህያ መንጋጋ) ጠላቶቹን እንዳጠፋ (መሳ 15÷9-19) ጌታም አይሁድ፣ አጋንንት፣ ማናፍቃን በናቁት ሞቱ ሞትን አጥፍቷልና

አንድም፡- ሶምሶን በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው ጠላቶች በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉ ጌታም በሕይወት ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉና (መሳ 16÷28-31)

# የማቴዎስ ወንጌል

## ምዕራፍ ሦስት

ማቴ 3÷1-2 ‹‹**በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፡- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ፡፡**

‹‹**በዚያም ወራት**››

‹‹**ልጁ ናዝራዊ ይባል ዘንድ**›› ተብሎ ነበርና ‹‹**ናዝራዊ**›› በተባለበት ወራት ሲል ነው፡፡

አንድም፡- ‹‹**ናዝሬት ገብቶ ኖረ ተብሎ ነበርና**›› ናዝሬት በገባበት ወራት

አንድም፡- ‹‹**ተወለደ**›› ብሎ ነበርና ሥጋ በሆነበት (በተወለደበት) ወራት

አንድም፡- ለዮሐንስ 30 ዓመት ሲሞላው ለጌታ መንፈቅ ሲቀረው በዚያ ወራት ሲል ነው፡፡

ይሁዳን ለምን አነሣት ቢሉ

ይሁዳን መጥምቁ ዮሐንስ የተወለደባት ቦታ ናትና አንሥቷታል

ውሃ ከአጠገቡ ያለውን ሳያጠግብ ሳያለመልም ሌላውን እንደማያለመልም ዮሐንስም በቅድሚያ የይሁዳ ሰዎችን ሰብኮ ወደ ሌላ የሚሄድ መሆኑን ለማጠየቅ፡፡

‹‹**ምድረ በዳ (ገዳም)**›› ለምን አለ ቢሉ

ዮሐንስ የሚኖረው በምድረ በዳ ነበርና (በበረሃ ይኖር ነበርና)

አንድም፡- በገዳም (ምድረ በዳ) እንጨት ሰባሪ፣ ውሃ ቀጂ አይታጣምና ለነሱ እየሰበከ መጣ

አንድም፡- በረሃ (ምድረ በዳ) ያለው፡- የአይሁድ ልቦናን ነው በምድረ በዳ እህል ተክል እንዳይገኝ በአይሁድ ልቡናም ምግባር ትሩፋት አይገኝምና

አንድም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት (ኢሳ 40÷3) ‹‹**ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም**›› ብሎ የተናገረልኝ እኔ ነኝ ሲል ነው፡፡

ማቴ 3÷3፡- ‹‹**በነቢዩ ኢሳይያስ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቀኑ" እያለ በምድረ በዳ የሚጮኸው ሰው ድምጽ የተባለለት ይህ ነውና**››

ትንቢቱ (ኢሳ 40÷3-5) በይበልጥ የሚመሳሰለው በሉቃስ 3÷4 ላይ ካለው ኃይለ ቃል ጋር ነው፡፡ ኢሳያስ በትንቢቱ ‹**የእግዚአብሔር መንገድ**› ያለውን ማቴዎስና ሉቃስ ‹**የጌታ መንገድ**› ብለውታል በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡

የጌታን መንገድ አዘጋጁ፡- ንጉሥ በመጣ ጊዜ፡- ተራራው ኮረብታው ተንዶ፣ ጎድጓዳው ሞልቶ፤ ሥሩ ተነቅሎ፣ ድንጊያው ተለቅሞ ለፈረስ ለሰረገላ እንዲመች ተደርጎ ይቆያልና በዚያ ልማድ ተናገረው እንደዚሁ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሰውነታችሁን ከኃጢአት ንጹሕ አድርጉ ሲል ነው

ትንቢቱም አልቀረም ዘሩባቤል ከፋርስ ባቢሎን በወጣ ጊዜ ይህ ሁሉ ተደርጓል፡፡

ፍጻሜው ግን የእግዚአብሔር መንገድ፡- ሕገ ኦሪት ናት

አንድም፡- ሕገ-ወንጌል ናት

አንድም፡- የእኛ ሕይወት ነው፡- ምክንያቱም መልካም ምግባራትን መስራት (ጽድቅ፣ፍቅር፣ሰላም) የእግዚአብሔር መንገድ (ወደ እግዚአብሔር መሄጃ ናቸውና)

ተራራው ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል፡-

ባቢሎናውያን፣ ጣዖታዊ ልቡና ይዋረዱ

አንድም፡- ጽሐፍት ፈሪሳውያን ይዋረዱ

አንድም፡- አጋንንት ይዋረዱ

አንድም፡- በምክረ ርእሱ (በፈቃደ ርእሱ) የሚኖር ሰው ሁሉ በምክረ ካህን ይኑር

ሸለቆው ጎድጓዳው ይሙላ

ትሩፋን ከባሎን ይውጡ (ዐዘቅት ይሙላ)

አንድም፡- ሐዋርያት ልዕልና ነፍስ ያግኙ

አንድም፡- ነፍሳት ከሲኦል ይውጡ

ሥጋ ለባሽ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ

ሥጋ ለባሽ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይወቅ

አንድም፡- ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ ነፍሱን ይወቅ

አንድም፡- ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ አድኅኖተ እግዚአብሔር ወልድ በአምሳለ ኀብስት እንዲሰጥ እንዲሰዋ ይወቅ ሲሰጥ ሲሰዋ ያስተውል ሲል ነው፡፡

ማቴ 3÷4፡- **‹‹እርሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው፤ በወገቡም ጠፈር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር፡፤››**

**‹‹ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው**

ግመል ምን ጠጉር አላትና ቢሉ፡-

ከጋማዋ ከጅራቷ ቢፈልጉ አይታጣምና

አንድም፡- ልብሱን ሲሉ ወንበዶች ይጣሉታል ብላ እናቱ አሥርታ አልብሳው ነበርና

አንድም፡- ግመል በቀለኛ ናት፡፡ አጥብቆ የመታትን እስከ 6 እስከ 7 ዓመት አትዘነጋውም ባጥ ብላ ትረግጠዋለች ስፍራ ሲመቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች፡፡ እርሱም ወይወድዮሙ ውስተ ፍኖተ እሳት የምትል ሕገ በቀል ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ማቴ 7÷19 ‹‹**ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል**››

አንድም፡-ግመል ሁለት ግብር አላት፡፡ የሚበላና የማይበላ እንደ ላም፣ እንደ በሬ ምንዛህ ታወጣለች (ታመነዥጋለች) እንደ ፈረስ፣ እንደ በቅሎ ሸኮናዋ ጽፉቅ (ድፍን) ነው ዮሐንስም ሕገ አሕዛብ ወሕዝብ፤ ለሕዝብ ለአሕዛብም የምትሆን ሕገ-ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል የገመል ጠጉር ለብሷል፡፡ ፍጻሜው ግን ለምዕመናን አብነት ለመሆን ማለት ‹ተርታ ልብስ ለብሳችሁ አልባሌ መስላችሁ ኑሩ› ለማለት፡፡

**‹‹በወገቡ ጠፈር ይታጠቅ ነበር››**

ዮሐንስ ለነገሥታት ንጉሥ፣ለጌቶች ጌታ ለክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ነው የወርቅ ዝናር ቢታጠቅ ይበዛበታልን? ቢሉ አይበዛበትም ያንስበታል እንጂ ይህ ግን ለሥጋውያን ነው እርሱ ግን መንፈሳዊ ነውና ይህን አይሻም፡፡

ጠፍርን አስቀድመው ከደመ ነፍስ ይለዩታል፣ ከውሃ ያገቡታል(ይነክሩታል) ኋላ ጠጉሩን ይመልጡታል፣ ያለፉታል ቀለም ያገቡታል፡፡

ጠፍር ከደመ ነፍስ የተለየ እንደሆነ ዮሐንስም ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ልዩ ነኝ ሲል ነው፡፡

አንድም፡- መክሮ አስተምሮ ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ይለያቸዋል

ከውሃ እንደመንከር - ያጠምቃቸዋል፤ ያስተምራቸዋል

እንደማልፋት -ምግባር ሃይማኖ ያሠራቸዋል

ቀለም እንደ ማግባት - ጸጋ ክብር ያሰጣቸዋል

ዮሐንስ በወገቡ ጠፈር ይታጠቅ ነበር ማለት ፍትወት እንስሳዊ በባሕርዩ እያለች እንዳላወረዳት (እንዳልሠራት) ይጠይቃል፡፡

**‹‹ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር››**

ዮሐንስ ለነገሥታት ንጉሥ ለጌቶች ጌታ ለክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ነው እንደነገሥታቱ ወግ ምግቡ እንጀራ ዶሮ ወጥ፣ መጠጡ የማር ጠጅ የማር ጠላ ቢሆን ይበዛበታልን ቢሉ? አይበዛበትም ያንስበታል እንጂ ይህ ግን ለሥጋውያን ነው እሱ ግን መንፈሳዊ መሆኑን ሲያጠይቅ ‹‹**ምግቡ አንበጣና የበረሀ ማር ነበር**›› አለ

ዩሐንስ አንቦጣ የሚባል ቅጠል አለ እሱን ደቁሶ ጨው ነስንሶ ይበላ ነበር፡፡

አንድም፡- አንበጣ በልሳነ አቴና ‹‹ቀሞሲስ›› ይለዋል በእኛ የጋጃ ማር (ጣዝማ ማር) ሲል ነው፡፡

አንድም፡- አንበጣ ይላል በቁሙ አንበጣውን ይበላው ነበር፡፡

ሶምሶን ፡- ከአፈ አንበሳ መዓር አግኝቶ እንደተመገበ ከመንሰከ አድግ ውሃ አግኝቶ እንደጠጣ

ኤልያስም ፡- በአፈ ቋዕ ሥጋ እየመጣለት ይበላ እንደነበር ዮሐንስም አንበጣን ይበላ ነበር

ይህንንም ሊቁ በምስጢር ሲፈታው

አንበጣ ማለቱ፡- ልዕልና ስብከቱ (የትምህርቱ ልዕልና)

መዓር ማለቱ፡- ጣዕመ ስብከቱ (የትምህርቱ ጣዕም) ነው ብሎታል፡፡

ማቴ 3÷5-6፡- **‹‹ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙርያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፡፡ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር፡፡››**

**‹‹ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር››**

ኃጢአታቸውን እየነገሩት በዮርዳስ ያጠምቃቸው ነበር ‹‹**እገሌ ተጠመቅ በማየ ንስሓ ከመ ትኩን ረድኡ ለክርስቶስ**›› እያለ

ጥምቀት ከ3 ወገን ነው፡-

መዝገበ ውሉደ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት

ጥምቀተ ዮሐንስ

ጥምቀተ አይሁድ

አንድም፡- ጥምቀቱ 8 ወገን ነው ፡፡አራቱ ምሳሌያዊ፣ አራቱ አማናዊ

አራቱ ምሳያዊ

አጥመቃ ለምድር በማየ አይህ - ምድርን በንፍር ውሃ ማጥመቁ

የጥፋት ውሃ - የጥምቀት ፣ ሕዝቡ - የኃጢአት

እስራኤል ዘሥጋ በሙሴ አማካኝነት ባሕረ ኤርትራን ሲሻገሩ በባሕር መጠመቃቸው

ወተጠምቃ እገሪሆሙ ለካህናት - በኢያሱ ጊዜ በዮርዳኖስ ሲሻገሩ

ጥምቀተ አይሁድ - በዓመት አንድ ጊዜ የሚጠመቁት የመንጻት በዓል የሚሉት (ዮሐ 5÷1)

አራቱ አማናዊ

1. የጌታ ጥምቀት፡-

2. አንብዓ ንስሐ የንስሐ ዕንባ/ የካህናት ቢያጡ ሳይጠመቁ እያለቁ ቢሞቱ እንባቸው እንደ ጥምቀት ይሆንላቸዋል፡፡

ደመ ሰማዕታት - የሰማዕታት ደም ፡- በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች ስለሃማኖቸው ጽናት ሲሞቱ አሕዛብ ሲመለከቱ ሳይጠመቁ እነርሱም እንደ ክርስቲኖቹ ይሰው ስለነበር ደም ሲፈሳቸው የደም ጥምቀት ሆኖላቸዋል፡፡

ባሕረ አሳት

ማቴ 3÷7፡- ‹‹**ዳሩ ግን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ብዙዎች ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፤ እንዲህ አላቸው፡- እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ?**

በአባታቸው በፋሬስ-ፈሪሳውያን፣በአባታቸው በሳዶቅ-ሰዱቃውያን፣ በዔቦር-ዕብራውያን፣በይሁዳ-አይሁድ፣ በአሞን - አሞናውያን ተብለዋልና በአባት ስም መጠራት ልማድ ነውና (ዘፍ 19÷37-38)

‹‹**እናንተ የእፉኝት ልጆች**››

አባቶቻቸው ወደው ለራሳቸው ባወጡት ስም ‹‹**ትውልደ አራዊተ ምድር**›› የምድር አራዊት (የአውሬ ልጆች) አላቸው፡፡

እንደምን (እንዴት) ቢሉ፡- ወንድሞቹ ዮሴፍን ሸጠው በልተው ‹‹**እኩይ አርዌ በልዖ** ‹‹**ክፉ አውሬ በላው**›› ብው ነበርና (ዘፍ 37÷1)

አንድም፡- እፉኝት - አርዌ ገሞራዊት ናት፡፡ አፊ ማኅጸንዋ ጠባብ ነው የወንዱን ዘር በአፏ ትቀበለዋለች፣

አባለ ዘሩን ቆርጣ ትጥለዋለች፡፡ በጽንስ ጊዜ አባት ይሞታል፡፡ በሚወለዱበትም ጊዜ አፊ ማኅጸንዋ ጠባብ ነውና ሥጋዋን በልተው ሆዷን ቀደው ይወጣሉ፡፡ በወሊድ ጊዜ እናት ትሞታለች፡፡አይሁድም

እንደ አባት የሆኗቸውን ነቢያትን እንደ እናት የሆኗቸውን ሐዋርያትን ገድለዋልና፡፡

‹‹**ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ**››

በጥጦስ፣ በሐላዊ መሲህ፣ በምጽአት ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ሲል ነው

ማቴ 3÷8፡- ‹‹**እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ**››

ለማመን የሚያበቃችሁን ሥራ ሥሩ

ማቴ 3÷9 ‹‹**በልባችሁም፡- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና ከነዚህ ድንጊያዎች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር ይችላል**››

‹‹**በልባችሁ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ**››

አብርሃም አብርሃም በማለት ወይም አብርሃም አባታችን ነው በማለት አትድኑም፤ የአብርሃምን ሥራ በመስራት በማመን ነው እንጂ ‹‹**ከእነዚህ ድንጊያዎች**›› አለ በድንጋይ ከተመሰሉ ከአሕዛብ እግዚአብሔር ሰዎችን ሊያስነሳ ይችላል ማለቱ ነው

አንድም፡- ደንጊያ ይቡስ (ደረቅ) ነው፡- ይቡሳነ አእምሮ ናቸውና

አንድም፡- ደንጊያ ቆሪር (ቀዝቃዛ) ነው፡- ቆሪራነ አእምሮ ናቸውና

አንድም፡- ደንጊያ ክቡድ (ከባድ) ነው፡- ክቡዳነ አእምሮ ናቸውና

ማቴ 3÷10 ‹‹**አሁንስ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል**››

‹‹**አሁንስ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል**››

ምሳር ያለው ሥልጣን - እግዚአብሔርን ነው

የእናንተን ልጅነት ከአብርሃም አባትነት ሊለይ ሥልጣነ እግዚአብሔር ተቃጥቷልና ሲል ነው፡፡ ለምን ቢሉ ከላይ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉት አይደለም

አንድም፡- ምሳር አለ ሥልጣነ-ክህነት ነው፡፡ መለኮት ከሥጋ ጋር ተዋህዷልና ክፉውን ህሊና ከበጎ ህሊና ሊለይ

ሥልጣነ - ክህነት ተቀጥቷልና ሲል ነው

‹‹**እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል**››

በእኔ ትምህርት አምኖ በጎ ሥራ የማይሠራውን ሰው ሁሉ ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል ከገሃነም ስቃይ ያመጡበታል

ማቴ 3÷11፡- ‹‹**እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል**››

‹‹**እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ**››

ዮሐንስ ለምን ስለራሱ ጥምቀት ሊገልጽ ፈለገ? ቢሉ

ምክንያቱ በዚህ መጽሐፍ (በማቴዎስ ወንጌል) ያልተያያዘ (ያልተጻፈ) በሉቃስ የተያያዘ ታሪክ አለ፡፡

ታሪክ፡ (ሉቃ 3÷10-15)-ዮሐንስ ሲያስተምር ብዙ ህዝብ ወደ እርሱ እየመጡ እንግዲህ ምን እናድርግ ብለው ይጠይቁት ነበር፡፡ባለጸጎች መጥተው ምንተ ንግበር ‹‹**እንግዲህ ምን እናድርግ**›› ይሉታል፡፡ ዮሐንስም ሁለት ልብስ ያለው ለሌላው አንድ ይስጥ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ››ይላቸው ነበር፡፡ ኃጥአን መጸብሐን መጥተው ‹‹**ምንተ ንግበር**›› ይሉታል ዮሐንስም ‹‹**ከታዘዛችሁት አብልጣችሁ አትውሰዱ**›› ይላቸው ነበር፡፡ ጭፍሮችም መጥተው ‹‹**ምንተ ንግበር**›› ይሉታል ዮሐንስም፡- ‹‹**በማንም ግፍ አትስሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ደሞዛችሁ ይብቃችሁ**›› ይላቸው ነበር፡፡ ዮሐንስ ይህን ትምህርት በማስተማሩ ክርስቶስ ቢሆን ነው (ክርስቶስ ይሆንን?) ብለው አስበው ነበርና፡-እኔስ ለጠጅ ብርሌን፤ ለልብስ ገላን እንዲያጥቡለት ለእርሱ ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት አጠምቃችኋለሁ እንጂ ክርስቶስ አይደለሁም በማለት ስለራሱ ጥምቀት ገለጸ፡፡

‹‹**ጫማውን ልይዝ የማይገባኝ**››

‹‹**ጫማውን ለመያዝ የማልሆን የማልበቃ ነኝ**›› ሲል ነው የንጉሥን የንግሥትን ጫማ ትበቃለህ ያላሉት ብላቴና ሰው አይዝምና ለእርሱ አልበቃም ሲል ነው፡፡

አንድም፡- ባሕርዩን ለመረምር የማይቻለኝ

አንድም፡- እርሱ ከሚያደርገው ከተአምራቱ ከትሩፋቱ ላደርግ የማይቻለኝ

አንድም፡- ጫማ አለ መርገምን ሲል ነው መርገምን ከምዕመናን ለአንዱ አርቅለት ዘንድ ከማይቻለኝ

**‹‹ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል››**

**‹‹ከእኔ በኋላ የሚመጣው ሲል››**

ዮሐንስ በልደተ ሥጋ ክርስቶስን በስድስት ወር እንደሚበልጠው ሲያስረዳ እዲህ አለ፡፡ ሉቃ 1፥26

**‹‹ከእኔ ይልቅ ይበረታል››** ማለቱ ደግሞ የክርስቶስን ቀዳማዊነቱን፣ የባሕርይ አምላክነቱን ከዮሐንስ አስቀድሞ እንደነበር ያስረዳል ዮሐ 1፥1 **‹‹ውእቱ ያጠሞቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወእሳት-እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል››**

**‹‹በጄ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ፤ በጄ ባትሉ በገሃነም እሳት ያጠምቃችኋል››** ሲል ነው

አንድም፡- **‹‹ከመንፈስ ቅዱ እሳትነት ያጠምቃችኋል››** ሲል ነው

እሳት ምሉዕ ነው፡- መንፈስ ቅዱስም ምሉዕ ነውና

አንድም፡-እሳት በምልዓት ሳለ ቡላድ ካልመቱ አይገለጽም፤ መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያናግር፣ ምስጢር ሲያስተረጉም እንጂ በሰው አድሮ ሳለ  አይታወቅም

አንድም፡- እሳት ከቡላዱ ሲወጣ በመጠን ነው ኋላ በእንጨት እቀጣጠሉ ያሰፋታል፣ መንፈስ ቅዱስም በጥምቀት ሲሰጥ በመጠን ነው ኋላ  በሥራ ያሰፉታል

አንድም፡- እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጣል - መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን፣  መዓዛ ጸጋን ያመጣልና

አንድም፡- እሳት በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል፤ ከመጠን ወጥቶ የሞቁት  እንደሆነ ግን ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በተጻፈው  የመረመሩት እንደሆነ ሕይወት ይሆናል፤ በማይገባው ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና

አንድም፡- እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ ያቃጥላል መንፈስ ቅዱም ሕዝብ አሕዛብ የጸለዩትን ጸሎት፣ ያቀረቡትን መሥዋዕት ይቀበላልና

አንድም፡- እሳት ውሃ፣ ገደል ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል፤ መንፈስ ቅዱስም  ቸርነቱ ካለ አለ ካለው ሁሉን ላጥፋ  ቢል ይቻለዋልና

አንድም፡- እሳት ውሃ፣ ገደል ካከለከለው ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል፤ መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋልና

አንድም፡- እሳት ዱር(ጨለማ) ይገልጻል መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጻልና

አንድም፡- እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተክል ይመቻል መንፈስ ቅዱስም  ያደረበት ሰውነት ለገድል፣ ለትሩፋት ይመቻልና

አንድም፡- እሳት ከአንዱ ፋና ሃምሳ፣ ስድሳ ፋና ቢያበሩለት ተከፍሎ የለበትም መንፈስ ቅዱም ተከፍ ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ይኖራልና

አንድም፡- በእሳት ቀድሞ ሰብአ ሳዶምን፣ ሰብአ ገሞራን አጥፍቶበታል፣ ለመዓት እንጂ ለምህረት አልተፈጠረም እንዳይሉ ለምሕረትም እንደተፈጠረ ለማጠየቅ

አንድም፡- ሽክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ ነቅ (ሰንጥቅ) ያገኘችበት እንደሆነ እንደገና መልሳ ከስክሳ በውሃ ለውሳ በእሳት ታድሰዋለች፡፡ የሰው ልጅ ተሐድሶም በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ሲያጠቅ ነው፡፡

ማቴ 3÷12 ‹‹**መንሹም በእጁ ነው፤ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፤ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል**››

‹‹**መንሹ በእጁ ነው**››

መንሽ የተባለው ስልጣኑን ነው ኃጥአንን ከጻድቃን የሚለይበትን ስልጣን ሲያጠይቅ ነው ንዑ ወ ሑሩ የሚልበትን ሥልጣን ሲያጠይቅ ነው

መንሹ ጣቱ ሦስት መያዣው አንድ ነው ቢሉ የአንድነትና የሦስትነት ምሳሌ

መንሹ ጣቱ ሁለት መያዣው አንድ ነው ቢሉ ጣቱ የሥጋና የአምላክ መያዣው በተዋህዶ አንድ የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡

አንድም፡- ክፉውን ሕሊና ከበጎው ሕሊና የሚለይበት ሥልጣነ ክህነት ሲያጠይቅ ነው፡፡

‹‹**አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል**››፡- አውድማ › የተባለ የሰው ልጅ ልቡና ነው

‹‹**ፈጽሞ ያጠራል**››፡- ሲል ጻድቃንን ከኃጥአን፣ በጎ ህሊናን ከክፉ ህሊና ይለያቸዋል ሲል ነው

አንድም፡- ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ በመንግሥተ ሰማያት ያስገባል

አንድም፡- በጎውን ህሊና ከክፉ ህሊና በመንፈስ ቅዱስ ያስጠብቃል

‹‹**ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥላቸዋል**››

ኃጥአንን ከጻድቃን ለይቶ በገሃነም ሥቃይ ያመጣባቸዋል

አንድም፡- ክፉውን ህሊና ከበጎ ህሊና ለይቶ በቀኖና ያጠፋዋል ሲል ነው፡፡

ማቴ 3÷13 ‹‹**ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡**››

ለጌታ ሠላሳ ሲመላው ለዮሐንስ መንፈቅ ሲተርፈው ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡

አንድም፡- ዮሐንስ ሰው ሰብስቦ በሚያጠምቅበት በዚያ ጊዜ መጣ

ምነው ባርያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጂ ጌታ ወደ ባርያው ይሄዳልን፤ ባርያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በባርያው እጅ ይጠመቃልን ቢሉ፡-

ጌታ መምጣቱ ለትህትና ነው እንጂ ለልዕልና አይደለምና

አንድም፡- ለአብነት፡- ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ብሎት ቢሆን ዛሬ ነገሥታት መኳንንት መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበርና ‹‹**ሂዳችሁ ተጠመቁ**›› ለማለት አብነት ለመሆን ነው

ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ያደረገው ስለምንድን ነው ቢሉ

ትንቢቱን ምሳውን ለመፈጸም

ትንቢት፡- ‹‹**ባሕርኒ ርእየት ወጎየት፤ ወዮርዳኖስኒ ገብዓ ድኅሬሁ ምንተ ኮንኪ ባሕር ዘጎየይኪ፤ ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባእከ ድኅሬከ**›› ባሕር አየች ሸሸችም፤ ዮርዳኖስም ወደኋላ ሸሸ መዝ113÷3

ምሳሌ፡- ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ (ምንጩ፣ መነሻው) አንድ ነው፤ ዝቅ ብ በደሴት ይለያያል ከታች ወርዶ ይገናኛል፡፡ እንዲሁም የሰው ሁሉ ነቁ አንድ አዳም ነው፡፡ ከዚያም እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቁልፈት ተለያይተዋ፡፡ በኋላም ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ በጥምቀት አንድ ሆነዋልና፡፡

አንድም፡- አብርሃም ለአምስቱ ነገሥተ ሠዩም ረድቶ አራቱን ነገሥተ ኮሎደጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ደስ ቢለው እግዚአብሔርን ‹‹**በዘመኔ ልጅህን ልከህ ተሳየኛለህን ወይስ በዚያ ቀን ታደርሰኛለህ (ታበቃኛለህ) ቢለው ‹‹እርሱን አታየውም ምሳሌውን ግን ታያለህና ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ**›› አለው፡፡ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ቢሄድ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ አኮቴት ጽውዓ በረከት ይዞ ተቀብሎታል፡፡ ይህም ምሳሌነት አለው አብርሃም የጥምቀት፣ መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት፣ ኅብስት አኮቴት ጽውዓ በረከት የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ናቸው፡፡

አንድም፡- እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል (ወርሰዋል) ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ምሳሌ ናቸው፡፡

አንድም፡- ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ገነት አርጓል ምዕመናንም አምነው ጠምቀው ወደ ገነት ለመግባታቸው ምሳሌ

አንድም፡- የኤልሳዕ ደቀ መዝሙራት ‹‹**ማደሪችን ጠበበን እንሂድና ዕፅ ቆርጠን ሁለተኛ ቤት እንሥራ**›› ብለው ይሄዳሉ፡፡ ኤልሳዕም መምህረ ትህትና ነውና አብሯቸው ሄደ፡፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቆርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባህር ገባበት ወደ መምህር መጥቶ ‹‹**ጌታዬ ጥንቱኑ የተውሶ ነበር፡፡ ጭራሹኑ ጠፋብኝ**›› አለው፡፡ ኤልሳዕም የገባበትን አሳየኝ አለው፡፡ አሳየው፡፡ ቅርፊት ከዛፍ ቀርፎ (ልጦ) አመሳቅሎ ባሕሩ ላይ ቢጥለው መዝቀጥ የማይቻለው ቅርፊት ዘቅጦ መዝቀጥ የሚገባውን ብረት ይዞ ወጥቷል፡፡

እንደዚህም ሞት የማይገባው መለኮት ሙቶ፣ ሞተ የሚገባው አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ነው፡፡

አንድም፡- ኢዮብ ከዮርዳኖስ ተጠምቆ ከደዌው ድኗል

ኢዮብ፡- የአዳምና የልጆቹ ፤ደዌ፡- የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ፤ዮርዳኖስ፡- የጥምቀት

አንድም፡- ጥዕማን ከዮርዳኖስ ተጠምቆ ከደዌው ተፈውሷል

ንዕማን፡- የአዳም፤ደዌ፡- የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፤ ዮርዳኖስ፡- የጥምቀት

ኢዮብ፣ ንዕማን፣ ጌታ. የተጠመኙት ወደቡ አንድ ነው

ትንቢቱን አውቆ አናግሯል፣ ምሳሌውንም አውቆ አስመስሏል ምስጢሩ እንደምን ነው ቢሉ፡

ታሪክ፡- ዲያቢሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ በአዳምና በሔዋን ሥቃይ አጸናባቸው ‹‹ስመ **ግብርናችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ መከራውን አቀልላችኋላሁ›› አላቸው ‹‹አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፤ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ›› ‹‹አዳም የዲያብሎስ ባርያ፤ ሔዋን የድያብሎስ ገረድ››** ብለው ጽፈው ሰጡት፡፡ መጻፍስ የለም (አይደለም) ይሁንብን ማለታቸውን ለመናገር ነው እንጂ፡፡

እርሱ (ዲያብሎስ) ያን በሁለት እብነ በረድ ጽፎ አንዱን በዮዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎት ነበር፡፡ በዮርዳኖስ የጣለውን ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ ረግጦ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል፡፡ በሲኦል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲወጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል፡፡ (ቆላ 2÷14)

ማቴ 3÷14 ‹‹**ዮሐንስ ግን፡- በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛ፡፡ አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?** ብሎ ይከለክለው ነበር፡፡

የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ እናት ቅድስት ኤልሳቤጥ የጌታችን እናት እመቤታችን ወደእርሷ በመጣች ጊዜ ‹‹**የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ (እንዴት ይሆንልኛል)**? (ሉቃ 1÷43) እንዳለች እርሱም ‹‹**ባርያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በባርያው እጅ ይጠመቃልን?**›› አለ፡፡

ማቴ 3÷15፡- ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል አለው፡፡ ያን ጊዜ ፈቀደለት››

‹‹**አሁንስ ፍቀድልኝ**›› ማለቱ በቁጥር 14 ላይ ከልክሎት ስለነበረ ነው፡፡

አንድም፡- ትህትናውን ያመለክታል

‹‹**እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል**›› ማለቱ

መጠመቁ ለሁላችንም ተድላ (ደስታ) ነው እንደምን ቢሉ ራሱን ከዮሐንስ አግብቶ አንተም መጥምቀ መለኮት ተብለህ ክብርህ ሲነገር ይኖራልና እኔም በባርያው እጅ ተጠምቀ ተብዬ ትህትናዬ ይነገራል አለው፡፡

አንድም፡ ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናልና ዮሐንስ እንዲያጠምቅ ጌታ እንዲጠመቅ ትንቢት ተነግሮዋልና፡፡

አንድም፡- ራሱን ከምዕመናን አስገብቶ “ይህ ለኛ ተድላችን ነው” አለ፡፡እናንተም ብትጠመቁ ይወርድላቹኋል ለማለት፡፡

**”ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል**” ማለቱ

ጽድቀ ተሰብኦን መፈጸም ይገባናል ሲል ነው፡፡

አንድም፡- ራሱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ አድርጎ ‹‹**ይህ ተድላችን** **ነው**›› አለ፡፡ ለምን ቢሉ፡-አብ ‹‹**ዝንቱ ውእቱ ወልድየ**›› ይህ የምወደው ልጅ ነው ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በአምሳ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስትነት ይገለጻልና ‹‹**እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል**›› ማለቱ በማኅጸን የጀመርነውን ቸርነት መፈጸም ይገባናል ሲል ነው፡፡

**“ያን ጊዜ ፈቀደለት (ተወው)”** ሲል

እንዲያው ዝም ብሎ ተወው ማለቱ አይደለም፡፡የአብ ስም በአንተ አለ የወልድ ስም የአንተው ነው የመንፈስ ቅዱስም ስም በአንተ ውስጥ ህልው ነው ሌላ ሰውን በአንተ ስም (በስምህ) አጠምቃለሁ አንተን በማን ስም ላጥምቅህ (በምን ስም ላጥምቅህ) ብሎታል፡፡ **ጌታም፡-** ‹‹**የቡሩክ እግዚአብሔር ልጅ ብርሃንን ገላጭ (የምትገልጽ) እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ›› ይቅር በለን**›› እያልክ አጥምቀኝ ብሎታል፡፡ከዚህ ንግግር በኋላ ተያይዘው ወደ ባሕር ወርደዋል፡፡

ጌታችን የተጠመቀበት ምስጢራዊ ምክንያቶች

ትንቢተ ነቢያትን ለመፈጸም መዝ 113÷3-7

አንድም፡- ምስጢረ ሥላሴን ለመግለጽ

አንድም፡- እናንተም ብትጠመቁ መንፈስ ቅዱስ ያድርባችኋል ለማለት - ለአብነት

አንድም፡ ሥርዓተ ጥምቀትን ለመመሥረት

አንድም፡- ዓለም ሁሉ የጌታን ጸጋና ክብር እንዲለብስና የእርሱ ደቀ መዝሙር እንዲሆን (ማቴ 28÷19)

አንድም፡- ሰዎች ሥርየተ ኃጢአትን እንዲያገኙ ‹‹**ያመነ የተጠመቀ ይድናል**›› ባለው ትምህርት መሠረት (ማር 16÷16)

አንድም፡- በጥምቀቱ ጥምቀትን ለመባረክ፣ ውሃውን ለመቀደስ፣ ለጥምቀትም ኃይልን ለመሥጠት

**ጌታ በ30 ዘመኑ ለምን ተጠመቀ?**

አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በኋላ በምክረ አጋንንት ተታሎ ያጣውን ልጅነት ለመመለስ አዳምን መስሎ ዳግማዊ አዳም ሆኖ በ30 ዘመኑ ተጠመቀ፡፡ ምክረ አጋንንትን በ30 ዘመኑ ተጠምቆ አፈራረሰው

አንድም፡- ሌዋውያን 30 ዘመን ሳይሞላቸው ለመንፈሳዊ ሥራ አይሰማሩም ነበር (ዘኍ 4÷1-3) ጌታም ሕግንና ነቢያትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽር አልመጣምና 30 ዘመን ሲሞላው የድኅነት ሥራውን በጥምቀትጀመረ፡፡ (ማቴ 5÷17)

*ማቴ* 3÷16፡- ‹‹***ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፡፡ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱም ላይ ሲቀመጥ አየ***››

*ጥምቀቱን በውሃ ያደረገው በሌላ (በማር በወተት) የላደረገው ስለምን ነው ቢሉ፡-*

*ትንቢቱንና ምሳውን ይፈጽም ዘንድ ነው*

*ትንቢቱ፡-* ‹‹***ጥሩውን ውሃ እረጭኃቹኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፤ከርኩሰታችሁ ሁሉ ከጣኦቻችሁ ሁሉ አጠራችኋለሁ***›› (*ሕዝ* 36÷25)

*ምሳሌው፡-* ‹‹***ባሕር (ውሃ) ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ***›› (*ዘፍ* 1÷20) *ባለ ጊዜ በልብ የሚስቡ፣ በእግር የሚሽከረከሩ፣ በክንፍ የሚበሩ በደመ ነፍስ ህያው ሁነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተገኝተዋል፡፡*

*በረው፣ በረው የሄዱ ፍጥረታት ነበሩ፣ ከዚያም የቀሩ ነበሩ*

*በረው የሄዱ - የኢጥሙቃን (ያልተጠመቁ)*

*ከዚያው የቀሩ -ጥሙቃን (የተጠመቁ) ሰዎች ምሳሌ*

*አንድም፡- በልብ የሚሳቡ - የሰብአ ዓለም (የሰዎች)፣በእግር የሚሽከረከሩ - ከትሩፋት ወደ ትሩፋት የሚያድጉ የባሕታውያን፣ በክንፍ የሚበሩ - ተመስጦ ፀጋ ያላቸው የሰማዕታት ምሳሌ ናቸው ትንቢቱን አውቆ አናግሯል፡፡ ምሳሌውንም ባወቀ አስመስሏል ምስጢሩ እንደምን ነው ቢሉ፡-*

*ውሃ በዙፋን ካለ ንጉሥ በአደባባይ እስካለ ጽኑስ (ውሃ) ለሁሉ ርኩብ (የሚገኝ) ነው፡፡ጥምቀትም መሠራቱ ለሁሉም ነውና*

*አንድም፡- ውሃ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይፈሳል ጥምቀትም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደረጋል*

*አንድም፡- ውሃ ከእድፍ (ከቆሻሻ) ያነጻል ጥምቀትም ከኃጢአት ያነጻልና*

*አንድም፡- ውሃ መልክ ያሳያል፤ መልክ ያጠራል ጥምቀትም መልክአ ነፍስን ያሳያል፤ መልክአ ነፍስን ያለመልማል*

*አንድም፡-ውሃ ለወሰደው ፍለጋ የለውም በጥምቀትም የተሠረየ ኃጢያት በፍዳ አይመረመርምና*

*አንድም፡- ሽክላ ሰሪ ሰርታ ስትጨርስ የነቃባት እንደሆነ እንደገና ከስክሳ በውሃ ለውሳ ታድሰዋለች ተሐድሶም በጥምቀት ነውና*

*አንድም፡- በውሃ ቀድሞ ሰብአ ትካትን ኋላም ግብጻውያንን ካጠፋ በኋላ ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም ብለው ያስቡ ነበርና ለመዓት ብቻ ሳይሆን ለምሕረትም እንደተፈጠረ ለማጠየቅ*

‹‹***እነሆም ሰማያት ተከፈቱ***›› *ሲል*

*ለሰማይ መከፈት መዘጋት ያለበት ሆኖ ሳይሆን ደጅ (በር) በተከፈተ ጊዜ ያልታየ ዕቃ ከውስጡ እንዲታይ ያልተገለጸ ምስጢር ተገልጸ (ታየ) ሲል ነው*

‹‹***የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይ ሲመጣ አየ***››

መንፈስ ቅዱስን ርግብ አለው ለምን አለው ቢሉ፡-

ርግብ ኀዳጊተ በቀል ናት (በቀልን የምትተው) ናት መንፈስ ቅዱስም ኃዳጌ በቀል ነውና

አንድም፡- ርግብ በኖኅ ጊዜ የጥፋት ውሃ ጎደለ ስትል በአፏ ወይራ ዘይት ይዛ ተገኝታለች፡፡ መንፈስ ቅዱስም ተስፋ መስቀልን ያበስራልና

አንድም፡- ርግብ ክንፏን ቢመቷት፣ ዕንቁላሏን ቢሰብሩባት ቤቷን ካላፈረሱባት አትሄድም መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሰሩ ፈጽመው ካልካዱት አይለይምና

እንደ አንድ ባህታዊ

ታሪክ፡- አንድ ባህታዊ በአንዲት ቆንጆ ልጃገረድ ዓይቶ በሐፀ ዝሙት ተነድፎ ‹‹ላግባሽ›› አላት ‹‹ለአባቴ ንገረው እምቢ አይልህም አለችው፡፡ ሂዶ ነገረው፡፡ አምላኬን ልጠይቅ›› ብሎት ጣዖቱን ገብቶ ልስጠው አልስጠው ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ጣዖቱም ‹‹ቆቡን ይቅደድ፤ ፈጣሪውን ይካድ ይህን ካላደረገ አስትስጠው ይለዋል፡፡ባሕታዊው ቆቡን ቀድዶ ፈጣሪውን ካደ በዚህ ጊዜ አድሮበት የነበረው መንፈስ ቅዱ በርግብ አምሳል ተለይቶት ሲሄድ ያያል፡፡‹‹ያልከኝን አደረኩ ስጠኝ›› ቢለው ‹‹ሁለተኛ ልጠይቅ›› ብሎ ገብቶ ጣዖቱን ቢጠይቅ ‹፣ቆይ ፈጣሪው ፈጽሞ አልራቀውም በአጠገብ፣ በአጠገቡ ይጠብቀዋልና አትስጠው›› ይለዋል፡፡ ‹‹እምቢ አይሆንም›› ቢለው ‹‹ለዚህ ብዬ ፈጣሪዬን ካድኩ፤ ቆቤን ቀደድኩ›› ብሎ ንስሐ ቢገባ መንፈስ ቅዱስ ተመልሶ በርግብ አምሳል ሲያድርበት አይቷል፡፡ ያም ባሕታዊ እስካሁን ወዴት ነበርህ አለው፡፡ አሁንም የተገለጽኩልህ ንስሐ ብትገባ ነው ብሎታል፡፡ (ሰሙነ ሕማማት)

ጥምቀቱን በመዓልት ያላደረገው በሌሊት ያደረገው ስለምን ነው ቢሉ፡-

በመዓልት (በቀን) አድርጎት ቢሆን መንፈስ ቅዱስን በቁሙ ርግብ ነው ብለው በተጠራጠሩ ነበር

አሁንስ በቁሙ ርግብ አለመሆኑ፤ መንፈስ ቅዱ መሆኑ በምን ይታወቃል? ቢሉ፡- ጌታ የተጠመቀው ከሌሊቱ በአሥራኛው ሰዓት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ተዋሕስያን ከየቦታቸው አይወጡምና ርግብ አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል

መንፈስ ቅዱስ የወረደው ጌታችን ከውሃው ከወጣ ከዮሐንስም ከተለየ በኋላ ነው ለምን?

ከውሃ ሳለ ወርዶ ቢሆን ለቀድሶተ ማያት የወረደ እንጂ ለጌታ አይደለም ባሉ ነበርና

አንድም፡-ከዮሐንስ ሳይለይ ወርዶ ቢሆን ስለ ክብረ ዮሐንስ ወረደ እንጂ ለጌታ አይደለም ባሉ ነበርና

ረቦ ወርዷል ያሉ እንደሆነ

አብ ምሉዕ ነው አንተም ምሉዕ ነህ እኔም ምሉዕ ነኝ ሲል ነው

አሰይፎ ወርዷል ያሉ እንደሆነ

የብሉየ መዋዕል የአብ ሕይወት ነኝ፣የብሉየ መዋዕል የአንተም ሕይወት ነኝ እኔም ብሉየ መዋዕል ሕይወት ነኝ ሲል ነው

ወርዶ ራሱን ቆንጠዋ አድርጎ ይዞታል፡፡ለምን ቢሉ

አብ አኃዜ ዓለም ነው፤ አንተም አኃዜ ዓለም ነህ፤ እኔም አኃዜ ዓለም ነኝ ሲል ነው፡፡

ማቴ 3÷17፡- ‹‹**እንሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚሰኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ**››

‹‹**ለተዋሕዶ የመረጥሁት በእርሱ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድኩት ልጄ ይህ ነው**›› የሚል ቃል ከወደ ሰማይ ተሰማ

ሐተታ፡- በዚህ አድሮ ያለው ልጄ ነው አላላም፡፡ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አድርጎ ‹‹**ይህ ልጄ ነው**›› አለ እንጂ፡፡ልጄም ማቱ እንደ አምላነቱ ነው እንጂ እንደ ሰውነቱ አይደለም

የምወደው ልጄ ሲል ፍቅርን ከማመልከቱም በላይ የክርስቶስን ሕማም ዓይተው ‹ቢጠላው ነው እንጂ ለእንዲህ ያለ ስቃይ አሳልፎ የሰጠው› የሚሉ ነበሩና በእርሱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ወርዶ ተወለዶ ሕማሙን ተቀብሎ ሞቱን መቅመሱን ያመለክታል፡፡

# የማቴዎስ ወንጌል

## ምዕራፍ አራት

ማቴ 4÷1 ፡- ‹‹**ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው**››

‹‹**ከዚህ በኋላ ….. መንፈስ ወደ ምድ በዳ ወሰደው**›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ከተጠመቀ በኋላ ፈቃዱ አነሣስቶ ወደ ገዳም ወሰደው ማለቱ ነው

አንድም፡- መንፈስ ሲል፡- መንፈስ ቅዱስ የሚል አብነት ይገኛል፡፡ ይህም ማለት ሰማዕታትን አነሳስቶ ወደ ደም ጻድቃን አነሣስቶ ወደ ገዳም እንደሚወስድ ወስደው ማለት አይደለም ነገር ግን ፈቃዳቸው አንድ መሆኑን መናገር ነው፡፡

ክርስቶስ በዲያቢሎስ መፈተን ለምን አስፈለገው?

ጌታችን በዲያብሎስ መፈተን ያስፈልገው እንደ ፍጡር (ሰው) መከራን እማርበታለው ዋጋን ክብርን አገኝበታለው ብሎ አይደለም፡፡ ነገር ግን ቀድሞ ዲያብሎስ ራሱን በሥጋ ከይሲ ሰውሮ አዳምን ድል ነሥቶት ነበርና ክርስቶም ዳግማዊ አዳም ሆኖ እራሱን በሥጋ አዳም ሰውሮ አይጥ በወጥመድ እንደሚያዝ ዲያብሎስን ድል ነሥቶታል፡፡፡

ፈተናውን ስለምን በገዳም አደረገ?

በገዳም የተፈተነበት ምክንያት አዳም ከዚህች ዓለም አፍአ (ወጪ) በምትሆን በገነት ድል ተነሥቶ ነበርና እርሱም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገዳም ዲያብሎስን ድል ለመንሣት ወደ ገዳም ሂዶ ፈተናውን ተቀበለ፡፡

ጌታችን ተጠምቆ አልዋለም አላደረም ዕለቱን ገዳም ሄዷል፡፡ እናንተም ተጠምቃችሁ ዕለቱን ገዳም ሂዱ(ሰይጣንን በጾም በጸሎት ድል አድርጉ) ለማለት

አንድም፡- በገዳም ጾር ይቀላል ለውጣንያን አብነት ለመሆን

አንድም፡- በገዳም ጾር ይጸናል( ይከብዳል) ለፍጹማን አብነት ለመሆን ፈተናውን በገዳም አደረገ፡፡

ማቴ 4÷2 ‹‹**አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ**››

ጌታችን መጾ ለምን አስፈለገው?

ጌታችን ሠራዔ ሕግ ነውና ጾምን የመጀመሪያ ሕግ አደረገው፡፡ አንድም ሥራውን በጾም ጀመረ፡፡

አንድም፡- መብል ለኃጢአት መሠረት እንደሆነ (አዳም በጾም ወድቋልና) ጾም ለምግባር ለትሩፋት መሠረት ናትና

አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ለምን ጾመ?

ቀድሞ አባቶቼ አርባ አርባ ጾመዋልና ከዚያ ቢያተርፍ ‹‹**አተረፈ**›› ቢያጎድል ‹‹**አጎደለ**›› ብለው አይሁድ ደገኛይቱን ወንጌል አንቀበልም ባሉ ነበርና

አንድም፡- ሙሴ አርባ ጹሞ ሕገ ኦሪትን ሠርቷል እርሱም አርባ ጹሞ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ (የሠራ) ነውና

አንድም፡- አንድም ኤልያስ አርባ ጹሞ ገነት ገብቷል እናንተም አርባ ብትጾሙ ገነት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት

አንድም፡- ዕዝራ አርባ ቀን ከምግብ ተከልክሎ ምሥጢር ተገልፆለት  መጻሕፍትን ጽፏል፡፡

እነዚያ ቀን ሲጽፉ እየዋሉ ማታ ይመገባሉ፡፡ እርሱ ግን ሲጽፍ የሚውለውን ሌሊት ሲያስላስለው (ሲያስበው) ያድር ነበር፡፡ እናንተም አርባ ብትጾሙ ምሥጢር ይገለጽላችኋል ለማለት፡፡

ምስጢሩ እንደምን ነው ቢሉ?

አዳም በአርባ ቀን ያገኘውን ልጅነት አስወስዶ ነበርና ለአዳም እንደካሰለት ለማጠየቅ ጌታችን አርባ ቀን ጾመ

‹‹**ተራበ**››

ጌታ ተራበ ሲባል ረሃቡ የፈቃዱ (ሥጋ በመልሱ) ነው እንጂ እንደኛ ያለ ረሃብ አይደለም

መራቡም ለአጽድቆተ ትስብዕተ፣ ለካሳ ነው

ማቴ 4÷3፡- ‹‹**ፈታኙም ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እንዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንደሆኑ በል አለው**››

ክርስቶስ ‹‹**ተራብኩ**›› የሚል ድምጽ አሰምቶት ቀረበ እንጂ ፈታኝ ዲያቢሎስ እንዲሁ አይቀርብም

አንድም፡- የተራበ የሚበላ እንደሚፈልግ ፍሬ ሲሻ አይቶታል

አንድም፡- እንደተራበ ፊቱን አጠውልጎ ታይቶታል

ዲያቢሎስ እንዲያው ዝም ብሎ አይቀርብም በአምሳለ ሐራሲ ሆኖ በቀዳዳ ስልቻ ዳቦ የያዘ መስሎ ሁለት ድንጊያ ይዞ ይቀርባል:: ‹‹ደንጊያውን ዳቦ አድርግና አንዱን ለአንተ አንዱን ለእኔ ዳቦ አድርገህ እንብላ›› እለዋለሁ፡፡ ‹‹ድንጊያውን ዳቦ" ከማድረግ የያዝከውን አንበላም›› ያለኝ እንደሆነ ‹‹**አዳም አባቱን በመብል ምክንያት ድል እንደነሳሁት እርሱንም በመብል ምክንያት ድል እነሳዋለሁ**›› ብሎ በዮርዳኖስ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ተብሎ ሲመሰከርለት ሰምቶ ነበርና ‹‹**የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ ይሁኑ ብለህ እዘዝ**›› አለው፡፡ቢያደርገው የሰይጣን ታዛዡ አሰኘዋለሁ ባያደርገው ደካማ እሰኘዋለሁ ድካሙንም አይቼ እቀርበዋለሁ ብሎ ነበር፡፡

ድንጋዩን ኅብስት አድርግ ማለቱ ምን ልማድ ይዞ ነው ቢሉ በዮሴፍ ልማድ ነው፡፡

ማቴ 4÷4፡- ‹‹**እርሱም መልሶ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፏልና አለው**››

ሰው የሚድነው በኅብስት ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ዳን ያለው ይድናል ሙት ያለው ይሞታል ሲል ነው

አንድም፡- የሰው ልጅ የሚድን ገበሬ በጣረበት በእንጀራ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር እንደሆነ ተጽፏል (ዘዳ 8÷3) ይህም ሊታወቅ እግዚአብሔር በምድረ በዳ መና እያወረደ (እያዘነመ) አርባ ዓመት ተመግበዋል፡፡

አንድም፡- ሰው የሚድን ገበሬ በጣራበት በእንጀራ ብቻ እንዳልሆነ ተጽፏል፡፡ ሕግን በመጠበቅ፣ በትምህርትም ነው እንጂ፡፡ ይህም ማለት የሰው ባሕርዩ ባሕርይ እንስሳዊ ባሕርይ መልአካዊ አለው፡፡ ባሕርይ እንስሳዊ ምግብ ሲያጣ ይጎዳል ባሕርይ መልአካዊም ትምህርት ሲያጣ ይጎዳልና፡፡

አንድም፡- ወልደ እግዚአብሔርስ ከሆንክ ይህን ድንጊያ ኅብስተ ሕይወት ኅብስተ መድኃኒት ይሁን ብለህ እዘዝ

ሲለው ነው፡፡ ጌታም ሰው የሚድን በዕሩቅ ብእሲ ሥጋ (መለኮት ባልተዋሐደው) እንዳይደል ተጽፏል፣ አካላዊ ቃል በተዋሐደው ሥጋ ነው እንጂ አለ፡፡

ማቴ 4÷5-6 ‹‹**ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን መቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ፣ መላዕክቱን ስለ አንተ ያዝዙልሃል እግርህንም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፏል፡፡ (መዝ 90÷11) የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው፡፡**››

ወደ ቅድስት ወሰደው ሲል እሱስ አይወስደውም ፈቃዱን አውቆ ሄደለት ለማለት ነው፡፡

አንድም፡- ዲያብሎስ ካህናትን ድል በማልነሣበት በገዳም ስለሆነ ነው እንጂ ካህናትን ድል በምነሣበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር ብሎዋል፡ ይህን ፈቃዱን አውቆ ወደ ቅድስት ሀገር ስለሄደለት ውሰደው አለ፡፡

በመቅደሱ ጫፍ ላይ አቁሞ በአምሳለ ሊቀ ካናት ሆኖ ይታየዋል፡፡ ከዚያ በኋላ በመዝሙር የተጻፈውን በመጥቀስ (መዝ 90÷11) ‹‹**የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ዘለህ ወደታች ውረድ**›› አለው ይህንን ያለበት ምክንያትም፡-

ቢዘል ይሰበራልና አርፈዋለሁ ባይሰበር ምትሐት አሰኘዋለሁ፣ ቢያደርገው ሌላ ያር እሻለታለው ባያደርገው ደካማ አሰኘዋለሁ ፣ቢያደርገው የሰይጣን ታዛዥ ብዬ ዕዳ እልበታለሁ ባያደርግው ድካሙን አይቼ እቀርበዋለው ብሎ ነበር፡፡

ማቴ 4÷7፡- ‹‹**ኢየሱስም፡- ጌታ አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፏልና አለው፡፡**››

ዳግመኛ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አትፈታተነው የሚል ጽሑፍ አለ አለው፡፡ እንዲህ የሚል ከምን አለ ቢሉ እንደ ጊዜ ግብሩ ጠቀሰው፡፡ እሥራኤል በገዳም ሳሉ ሙሴ ከአሥራ ሁለቱ

ነገድ አውጣጥቶ ኢ.ያሱና ካሌብን ምድረ ርስትን ሰልላችሁ ኑ ብሎ ሰደዳቸው፡፡ እነርሱም ሰልለው ሲመለሱ ከወይኑ ዘለላ ከስንዴው ዛላ ይዘው መጡ፡፡ « እንደምን ሁናችሁ መጣችሁ? ሀገሪቱስ እንደምን ያለች ናት? » ብለው ጠየቋቸው፡፡ ‹‹ሀገሪቱስ መልካም ናት የስንዴው ዛላ እጅ ይመላ የወይኑ ዘለላ ጋን ይመላ እንዲሉ እንዲህ ያለ ታፈራለች አሉ፡፡ ነገር ግን እኛ በእነርሱ ፊት እንደ ፌንጣ ሆነን ታየን፡፡›› ብለው አሥሩ አስገርመው አስፈራርተው ተናገሩ፡፡ ካሌብና ኢ.ያሱ ግን ‹‹በፈቃደ እግዚአብሔር እንገባባታለን›› ሲሉ፤ ዓስሩ ካገባነስ አሁን ያግባን ሙሴ ተነሣ ታቦተ ጽዮንንም አንሣ እንሂድ አሉት ሙሴም ‹‹ታቦተ ጽዮንም አሁን አትነሣ እግዚአብሔርን አትፈታተኑ›› አላቸው፡፡ ‹‹አይሆንም›› ብለው ሄዱ፡፡ በወሰን ያሉ አሕዛብ ገጥመው ድል አደረጓቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ከባሕር ጠልቀው ከገደል ገብተው አልቀዋል፡፡ ከዚህም ጌታ አንደ ጊዜ ግብሩ ጠቀሰው፡፡/ዘኑ 13፥14/

ማቴ 4÷8-10፡- ‹‹**ደግሞ ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውን አሳይቶ፣ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሀለሁ አለው ያን ጊዜ ኢየሱስ፣ ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው››**

ዲያብሎስ ነገሥታትን ድል በማልነሣበት በቤተ መቅደስ ቢሆን ድል ነሣኝ እንጂ ነገሥታትን ድል በምነሣበት በተራራ ቢሆን መች ድል ይነሳኝ ነበር ብሏልና ፈቃዱን አውቆለት በመሄዱ ወደ ተራራ ወሰደው አለ፡፡ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሀለሁ አለው ደፋር ነውና ብትሰግድልኝ እጅ ብትነሣኝ ይህን ሁሉ አሰጥሃለሁ አለው ያን ጊዜ ኢየሱስ፣ ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው››

ከዚህ በኋላ ከኋላዬ ወግድ አለው ራስ ዓይቶ ከኋላ የሚመጣ ጠላት ክፉ ነውና ጽኑ ባላጋራዬ ሲል ነው

አንድም፡- ከእኔ በኋላ ከሚነሱ ምእመናን ወግድላቸው አለው

ከኋላዬ ሂድ ባለው ጊዜ እንደ ጉም ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፍቶዋል፡፡

እስካሁን ሂድ ሳይለው አሁን ደርሶ ወግድ ከኋላዬ ማለቱ ስለምንድን ነው? ቢሉ፡- ንጉሥ በመንግሥቱ ጎልማሳ በሚስቱ እንዲቀና ጌታም ለአምልኮቱ ቀናዒ ነው፡፡ (ዘፀ 20÷6)

ለጌታህ ለአምላህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ እግዚአብሔር ሲል አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እርሱንም ብቻ ማምለክ እንዳለብን ያመለክታል፡፡

ከኋላዬ ሂድ ባለው ጊዜ እንደ ጉም ተኖ እንደ በኖ ጠፍቶዋል ታድያ ከዚያ በኋላ ጥቅሱን ለምን ይጠቅሰዋል ቢሉ ፡-

ሰይጣንና ውሻ ምልልስ ወዳጅ ነውና ተመልሶ ይሰማዋል

አንድም፡-እንደ አምላክነቱ አጽንቶት ሰምቶ ይሄዳል

አንድም፡-ካለበት ሁኖ እንዲሰማው አድርጎታል

አንድም፡-ከሐተታ ለመዳን ጥቅሱ ይቀድማል፡፡

ማቴ 4÷11 ፡- ‹‹**ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው፤ እንሆም መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር፡፡››**

ከሦስት ዓመት በኋላ በዕለተ ዓርብ በአይሁድ አድሮ እስኪያሰቅለው ድረስ ተወው፡፡

በሉቃስ 4÷13 - እስከ ጊዜው ድረስ ተወው ብሎ ያቀናዋል፡፡ ማለትም በዕለተ ዓርብ በአይሁድ ሥግው ሁኖ እስኪያሰቅለው ድረስ ተወው ሲል ነው፡፡

ጌታ የተፈተነባቸው ፈተናዎች ሦስቱ አርዕስተ ኃጣውእ(ሦስቱ ታላላቅ የሰይጣን ፈታናዎች) በመባል ይታወቃሉ፡፡እነርሱም፡- ስስት፣ትዕቢትና ፍቅረ ንዋይ ናቸው፡፡

ስስት፡- ያልሰጡትን መሻት ነው

ትዕቢት፡- አምላክ እሆናለሁ ማለት ነው

ፍቅረ ነዋይ፡- በቃኝ አለማለት ነው

በነዚህ ሁሉ ለአደምና ለሔዋን ድል ነሥቶላቸዋል፡፡ አንድም ለአዳምና ለሔዋን ብቻም አይደለ ለሁሉም ነው፡፡

የመነኮሳት ፆራቸው ስስት ነው፡- በፈለጉት ጊዜ አያገኙምና በትርምት ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በቦታቸው በገዳም በስስት ቢመጣበት በትዕግስት ድል ነሥቶላቸዋል፡፡

የካህናት ፆራቸው ትዕቢት ነው፡- አእምሮአችን ረቂቅ ማዕረጋችን ምጡቅ ነው እሉ ይታበያሉና፡፡ በቦታቸው በቤተ መቅደስ በትዕቢት ቢመጣበት በትህትና ድል ነሥቶላቸዋል፡፡

የነገሥታት ፆራቸው ፍቅረ ነዋይ ነው፡- ቤታቸውን ከፍ ካለ ቦታ ላይ አሰርተው ያለፈ ያገደመውን የወጣ የወረደውን እያዩ የዚህ ሁሉ እንጂ ኑሮው በእኛ ነው እሉ ገንዘብ ይሰበስባሉ፡፡ ቦታቸው በተራራ ነው፡፡ በተራራ በፍቅረ ነዋይ ቢመጣት በጸሊዓ ንዋይ ድል ነሥቶላቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ኃጢአት ከሥሩ እንደተነቀለ ዛፍ ሆናለች፡፡ ከሥሩ የተነቀለ ዛፍ እንዳይለመልም፤ እንዳያብብ፤ እንዳያፈራ ኃጠአትም በፍዳ የማታስይዝ ሆናለች፡፡

**‹‹እነሆም መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር››**

መላዕክት ጌታችን እየተፈተነ ሳለ ያልመጡት ሰይጣንን ድል ከነሣው በኋላ መምጣታቸው ስለምን ነው? ቢሉ፡- በፈተናው ጊዜ መጥተው ቢሆን ‹‹**ከመላዕክቱ ጋር ሆኖ ድል ነሣኝ እንጂ ብቻውን ቢሆን መች ይነሣኝ ነበር**›› ባለ ነበርና፡፡

አንድም፡- እናንተ ድል ብትነሡ መላእክት ተገልጸው ያገለግሏችኋል ለማለት

ማቴ 4÷12 ‹‹**ኢየሱስም ዮሐንስ አልፎ እንደተሰጠ በሰማ ጊዜ ወደ ገሊላ ፈቀቅ ብሎ ሄደ**››

ጌታችን ሄሮስ ዮሐንስን እንዳሰረው ሲሰማ ‹‹**መከራ በመጣባችሁ ጊዜ ሽሹ**›› **ለማለት፤ ለአብነት ወደ ገሊላ ፈቀቅ አለ፡፡ (ማቴ 14÷11)**

ማቴ 4÷13-16፡- ‹‹**ናዝሬትንም ትቶ በባቢሎንና በንፍታሌም አገር በባህር አጠገብ ወደ አለችው ወደ ቅፍርናሆም መጥቶ ኖረ፡፡ በነቢዩ ኢሳያስ፡- የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር የባህር መንገድ፣ በዮርዳስ ማዶ የአህዛብ ገሊላ በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ፡፡**››

ነቢዩ ኢሳያስ በትንቢቱ የተናገረው (ኢሳ 9÷1-) ይፈጸም ዘንድ በዚያ ገብቶ ኖረ

‹‹**በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ**›› ማለቱ

በድንቁርና፣ በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀት ተሰጣቸው ሲል ነው

አንድም፡- አንድ ገጽ በማለት ሞትን በመምሰል ሞት ባመጣው ምስል ለሚኖሩ ሰዎች ክርስቶስ ተወለደላቸው፣ ወንጌል ተጻፈላቸው

አንድም፡- በሞተ ሥጋ በሞተ ነፍስ ለነበሩ ልጅነት ተሰጣቸው በኃጢአት በክህደት ለነበሩ ሃይማኖት ተገለጸላቸው ሲል ነው፡፡

ማቴ 4፡17-19 "**ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ ፡-መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር፡፡ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማቾች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፡፡ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና፡፡**"

ነጠላ ትርጉም

ማቴ 4፡19 "**እርሱም ፡-በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው፡፡**"

ለጊዜው በእግር ተከተሉኝ ለፍጻሜው ግን በግብር ምሰሉኝ አላቸው፡፡ ሰውን እንደ ዓሣ ወንጌልን እንደ መረብ ዓለምን እንደ ባሕር አድርጋችሁ እንድታስተምሩ አደርጋቹኋለሁ ሲላቸው ነው፡፡

ማቴ 4÷20፡- ‹‹**ወዲውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት**››

ለጊዜው ‹‹ኑ›› ያላቸው የጌታችንን ጥሪ ሰምተው በእግር ተከተሉት ፍጻሜው ግን በግብር መሰሉት ማለት ነው፡፡

ማቴ 4÷21፡- "**ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎች ሁለት ወንድማማቾች የዘብድዮስ ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብድዮስ ጋር በታንኳ መረባቸውን ሲያበጁ አየ ጠራቸውም**"

ነጠላ ትርጉም

ማቴ 4÷22፡- ‹‹**እነርሱም ወድያው ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት**››

ምነው መጽሐፍ ‹‹**አባትና እናትህን አክብር**›› (ዘጻ 20÷12) አይልምን? አባትን ጥሎ መሔድ ይገባልን? ቢሉ

ከአክብሮተ እናት እና አባት አክበሮተ እግዚአብሔር እንዲበልጥ ለማሳየት

አንድም፡- አባት እራሱን የሚያስተዳድርበት ገንዘብ ካለው ትቶ መሔድ ጥፋት አይደለም አባት ግን እራሱን የሚረዳበት ገንዘብ ከሌለው ትቶ መሔድ አይገባም፡፡(ማቴ 10÷37-38) ነገር

ግን አባታቸው ዘብድዮስ ባለሞያተኞችን ቀጥሮ ማሰራቱ ገንዘብ እንዳለው ያመለክታልና፡፡ (ማር 1÷20)

ማቴ 4፡23 **“ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕመም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር፡፡ ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ ፈወሳቸውም፡፡”**

ነጠላ ትርጉም

ማቴ 4፡25 **“ከገሊላም ከአሥሩ ከተማም ከኢየሩሳሌምም ከይሁዳም ከዮርዳኖስም ማዶ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት”**

ከእስሩ አህጉር ከብዙ መንደር ተውጣጥተው አምስት ገቢያ ያህል ሰዎች ተከተሉት፡፡ ለአንድ ሽማግሌ ዓሥር ልጆች ነበሩት እኒህ እየራሳቸው አንድ አንድ አገር አቅንተው ይኖሩ ነበርና

አንድም፡-ፊላጦስ ለቀረጥ ይመቸው ዘንድ እንዱን ከተማ ለአሥር ከፍሎታል፡፡

ከዚያ ተውጣጥተው ተከትለውታል፡፡

ስለምን ይከተሉታል ቢሉ፡-

ስለአምስት ነገር ይከተሉታል፡፡አንዱ ገቢያ መልኩን እናያለን ብለው፣አንዱ ገቢያ ኅብስት አበርክቶ ያበላናል ብለው፣አንዱ ገቢያ ትምህርቱን እንሰማለን ብለው፣ አንዱ ገቢያ ከደዌያችን ይፈውሰናል ብለው፣ አንዱ ገቢያ የኦሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ብለው ይከተሉት ነበር፡፡

# የማቴዎስ ወንጌል

## ምዕራፍ አምስት

**ማቴዎስ 5 1÷1 ‹ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፤ በተቀመጠም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፣ አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው እንዲህም አለ›**

**ማቴ 5÷3 ‹‹በመንፈስ ድች የሆኑ ብፁዓን ናቸው መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና››**

በመንፈስ ድች የሆኑ ማለት የዋሐን ትሑት የሆኑ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች ራሳቸውን ችሎታ እንዳላቸው አድርገው አይቆጥሩትም፡፡ በራሳቸው ዘር፣ ጠባይ፣ ተፈጥሮ፣ ሀብት፣ አቅምና ችሎታ ተስፋ አያደርጉም፡፡

ነዳያን በመንፈስ ማለት ደንቆሮ የሆኑ ያልተማሩ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ማንነታቸውን አውቀው በፊታቸው ሁሉን የተዉ ማለት ነው፡፡ ነዲያን በመንፈስ በእግዚአብሔር ፊት የተሰበረና የተዋረደ ልብ ይኖራቸዋል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ከእነሱ እጅግ የሚበልጥ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ መኖሩን በማሰብ ነው፡፡

አንድ ሰው ራሱን ዝቅ ካላደረገ የትህትናም ሥራ ካልሰራ አምላካዊ ጸጋን አያገኝም እርሱም አይፈልገውም፤ ሁሉ ያለው ይመስለዋልና፡፡ ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ ግን ይህን የትሩፋት ሥራ መንገድ መከተል ራስን ከመውደድ መራቅ እያለውም እንደሌለው ሆኖ መታየት ተገቢው ነው፡፡

**ማቴ 5፡4 ‹‹የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና››**

ኀዘን /ልቅሶ/ የሚገባና የማይገባ በመባል ለሁለት ይከፈላል፡፡

የማይገባ ኀዘን፡-

እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድም፣ ዘመድ የለኝ፣ ርስት ጉልት ሄደብኝ ብሎ ማዘን የማይገባ ነው፡፡ እንደ አባት እንደ እናት ሥላሴ፣ እንደ ወንድም እንደ እህት መላዕክት አሉና እንደ ርስት እንደ ጉልት የማታልፍ መንግሥት ሰማያት አለችና፡፡ (2ቆሮ 7÷10-11)

የሚገባ ኀዘን

የራስን ኃጢአት አስቦ ማልቀስ /እንደ አዳም፣ እንደ ዳዊት (2ኛ ሳሙ 11÷12) ፣ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ (ሉቃ 22÷54-62/

የባልንጀራን ኃጢአት አስቦ ማልቀስ /እንደ ሳሙኤል/ 1ኛ ሳሙ 15÷35

ግፍዓ ሰማዕታትን አስቦ ማልቀስ /የሐዋ 8÷27/

ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን / እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ የጌታችንን የዕለተ ዓርብ መከራውን እያሰበ ሰባ ዘመን ቁጹረ ገጽ ሆኖ ኖሯልና፡፡

እንዲህ ያሉ ሰዎች ይጽናናሉ/ ይደሰታሉ/፡፡ ይህም እውነተኛ ደስታ የሚገኘው በመንግሥት ሰማያት ነውና፡፡

ይጽናናሉ /ይደሰታሉ/ ማለቱ ፡- መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ ሲል ነው፡፡

ማቴ 5÷6 ‹‹**ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፣ ይጠግባሉና**››

ጽድቅን የሚራቡ የሚጠሙ ማለት፡- ጽድቅን እንደ እህል የሚራቡ እንደ ውኃ የሚጠሙ፣ በየጊዜው የሚፈልጉ እርሱን ብቻ የሚራቡና የሚጠሙ ማለት ነው፡፡ ጽድቅን ለማግኘት ለጽድቅ ለመብቃት ሕግጋትን ለመፈጸም ሲሉ አሁንም ነገም እርሱን ብቻ የሚራቡ እርሱን ብቻ የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ሲል ነው፡፡

ማቴ 5÷6 ‹‹**የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፣ ይማራሉና**››

ምሕረት ሦስት ዓይነት ነው፡፡ ምሕረት ሥጋዊ፣ ምሕረት መንፈሳዊና ምሕረት ነፍሳዊ፡፡

ምሕረት ሥጋዊ፡- ቀዶ ማልበስ ቆርሶ ማጉረስ፣ ቢበድሉ ማሩኝ፣ ቢበደሉ ይቅርታ ማድረግ ነው፡፡

ምሕረት መንፈሳዊ ፡-ክፉውን ሃይማኖት ክፉውን ምግባር በጎ ሃይማኖት በጎ ምግባር መስሎ ይዞት ሲኖር መክሮ አስተምሮ ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ማስያዝ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጎውን ማሠራት ማለት ነው፡፡

ምሕረት ነፍሳዊ፡- መጥዎተ ርእሰ /ራስን መስጠት/ ነው፡፡ /ዮሐ 15፣13/

ይማራሉና ማለቱም፤- ለእርሱም ሥላሴ ያዝኑላቸዋል ይራሩላቸዋል ማለቱ ነው፡፡

ማቴ 5÷8 ‹‹**ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና**››

ልባቸው የነጻ እግዚአብሔርን ያዩታል ማለት፡- እግዚአብሔር በዓይነ ሥጋ ይታያል ማለት አይደለም፡፡ በዓይነ ልብ ግን ይታያል፣ ያውም በጣም ንጹሕ የሆነ እንደሆነ፡፡ የልብ ንጽሕና ማለት ከልብ የሚመነጩ መጥፎ ሐሳቦችን መተው ማለት ነው፡፡

በሥጋዊ አስያየታችን በሥጋዊ ዓይናችን ዛሬ እግዚአብሔርን ልናየው ከቶ አንችልም፡፡ ግን ነፍሳችን ጠርታ፣ ሥጋ ነፍስን መስሎ ወደ እግዚአብሔር በቀረብን ጊዜ ፊት ለፊት እግዚአብሔርን እናየዋለን /1ኛ ቆሮ 13÷12/ እነዚህን ልቦናቸው የነጻ ወገኖች ግን አሁንም ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ የደረሱ ስለሆነ እንደ ጌታ ቃል እግዚአብሔርን ያዩታል፡፡

ማቴ 5÷9 ‹‹**የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና**››

በመጀመሪያ ሥጋና ነፍሳቸውን ካስማሙ በኋላ ሌሎችን በመምከርና በማስተማር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፡፡ እውነተኛ አስታራቂ ክርስቶስ ነው /ኤፌ 2÷14/፡፡ ሐዋርያት አስታራቂዎች ናቸው /2ኛ ቆሮ 5÷17-30/፡፡ ዛሬም ካህናትና ሽማግሌዎች ሁሉ የማስታረቅ መብት አላቸው 1ኛ ቆሮ 6÷5

ሰላምና እርቅን የሚመሠርቱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ፡፡ /ዮሐ 1÷12/ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው /ሮሜ 8÷14/፡፡ እነዚህ ሁሉ ሰላማውያን

ናቸው ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ስለሆነ ልጆቹ ሰላማውያን ይሆናሉ፡፡ /1ኛ ቆሮ 14÷33/

ማቴ 5÷10 ‹‹**ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፡፡ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና**››

ስለ ጽድቅ ማለት /ስለ እውነት/ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፡፡ እውነት መራራ ናትና እውነትን ተናግሮ በእውነትም ሰርቶ የሚያስቀምጠው የለም፡፡ ነብያት ስለ ጽድቅ ተሰደው ነበር፡፡ ክርስቶስም መሰደድ ብቻ ሳይሆን የተሰቀለውም ስለ ጽድቅ ነው፡፡ እነርሱም ለደቀ መዛሙርቱ እውነትን ስለምትናገሩ፣ እውነትን ስለምትሠሩ ሐሰተኞች ያሳድዱችኋል ብሎ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡ /ዮሐ 15÷18-19/

ኃጢአተኛው ዓለም በጨለማ ውስጥ ስለሆነ ተስፋ ቆርጦ ይኖራል፡- ስለዚህ መንፈሳዊ ነገር እውነትም የሆነ ነገር ሁሉ አያስደስተውም፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሊሰማ ፈጽሞ አይወድም፡፡ እንደዚህ ያለ ነገር የሚናገረውንና የሚሠራውንም ሁሉ ያሳድደዋል፡፡

እውነተኛ ክርስቲያን እውነት ከመመስከር ወደ ኋላ አይመለስምና መከራና ስደት ይደርሱበታል፡፡ /የሐዋ 4÷18-19/ በግፍ የሚሰደዱ ታላቅ ክብር አላቸው ሲል ነው፡፡/ሮሜ 8÷18 ፣ 2ቆሮ 4÷17/

ማቴ 5÷11-12 ‹‹**ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፣ ሀሴትም አድርጉ፡፡ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳደዋቸዋልና፡፡**››

ስለ ክርስቶስ ስም የተረገሙ የተወቀሱና የተከሰሱ፣ ከሀገርም እንዲወጡና እንዲሰደዱ የተፈረደባው፣ በበለጠም የመኖር ዕድል ተነፍጓቸው የተገደሉ ብዙ ናቸው፡፡ እዚህ ሰዎች ወንጀል አልሠሩም፣ ክፉ ነገር አልተናገሩም፣ በክርስቶስ በማመናቸው ወንጌልንም በማስተማራቸው ብቻ ይህ ሁሉ መከራ የደረሰባቸው ናቸው፡፡

አስቀድሞ ነቢያት በእግዚአብሔር አምልኮ ከዚያም የመሲሕን መምጣት ተስፋ ያደርጉና ይጠባበቁ ስለነበሩ፣ ስለዚህ ሁሉ ገልጠው ትንቢት ስለተናገሩ እየተንገላቱ እየተሰደዱ የሞቱ ብዙዎች ናቸው፡፡ የኤልያስን፣ የኢሳያስን፣ የኤርሚያስንና የሌሎች ሰማዕታትን ታሪኮች ለአብነት ያህል መመልከቱ ይጠቅማል፡፡ /1ኛ ነገ. 18፣ ዕብ 11÷32-40/

ሥጋን እንጂ ነፍስን ለመግደል የሚችል የለምና /ማቴ 10÷25-28/ ክርስቲያን ሁሉ ስለ እውነት /ጽድቅ/ የመጣው ቢመጣ መፍራት ማፈር የለበትም፡፡ ቢሰደድም ክብሩ ነው፣ ቢሞትም ዕረፍቱ ነው፣ ተቀባዩ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ይላል ‹‹ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት አደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ፡፡ ስለ ክርስቶስም ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ፡፡›› /1ጴጥ 4÷13-14)

ማቴ 5÷13 ‹‹**እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፡፡ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጪ ተጥሎ በእግር ከመረገጥ በቀር ወደፊት ለምንም አይጠቅምም**››

በዚህ ክፍል ውስጥ በጨው የተመሰሉ ክርስቲያኖችና ወንጌላውያን ናቸው፡፡ ክርስቶስ ተከታዮቹን ለምን በጨው መሰላቸው? ጨው ምግብን ያጣፍጣል / ኢዮብ 6÷6/ ክርስቲያኖችም በኃጢአት አልጫ የሆነውን ኅብረተሰብ ያጣፍጣሉ፡፡

አንድም፡- ጨው ቁስልን ያደርቃል፤ ክርስቲያኖችም በኃጢአት የቆሰለውን ዓለም ይፈውሳሉና /ኢሳ 1÷5/

አንድም፡- ጨው በጥንት ዘመን ገንዘብ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ገንዘቦች ናቸውና /2ኛ ቆሮ 12÷14/

አንድም፡-ጨው በብሉይ ኪዳን ዘመን ለመሥዋዕት ይጨመር ነበር /ዘሌ 2÷13/ ክርስቲያኖችም መሥዋዕት እስከመሆን ድረስ ስለ ክርስቶስ ይመሰክራሉ /ፊሊጵ 1÷29/

አንድም፡- ጨው በጠቅላላው ፍቅርን ያመለክታል /ማር 9÷50/፡፡ ጨው አልጫ ቢሆን የሚሰጠው ጥቅም የለም፡፡ ክርስቲያኖችም በክርስቶስ ሕግ ካልተመሩ ከንቱ ይሆናሉ፡፡

አንድም፡- ጨው በሌላ መንገድ የቅጣት፣ የፍርድና የመርገም ምልክት ይሆናል፡፡ /ዘፍ 19÷26፣ መሳ 9÷45/፡፡እውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት የሌላቸው ክርስቲያኖች የመርገምና የቅጣት ምልክቶች ናቸው/ዕብ 6÷4-6/

ማቴ 5÷14-16 ‹‹**እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፡፡ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም፡፡ መብራትንም አብርተው ከእንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል፡፡ መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፡፡››**

እውነተኛ የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ነው፡፡ /ዮሐ 8÷12/ እውነተኛ ተከታዮቹም የዓለም ብርሃን ተብለዋል፡፡ ብርሃንነታቸው ግን ከራሳቸው ባሕርይ ሳይሆን ከክርስቶስ ብርሃን የተቀጣጠለ ነው፡፡ /ኤፌ 5÷8)

የክርስቲያኖች ብርሃንነት፡-

ክርስቶስን ሲከተሉ ነው፡፡ /ዮሐ 12÷35-36/

አንድም፡- ቃሉን ሲያስተምሩ ነው፡፡ /ፊሊጵ 2÷15/

አንድም ፡-ላላመኑት መድኃኒት ለመሆን ነው፡፡ /ኢሳ 49÷6፤ የሐዋ 13÷47/

በተራራ ላይ የተሰራች ከተማ እንዲሁም በከፍተኛ መቅረዝ ላይ የተሰቀለ መብራት ከሩቅ ይታያና ሊሰወሩት አይችሉም፡፡ ክርስቲያኖችም በመልካም ስራቸው በሁሉ ዘንድ መታየትና መታወቅ ለአምላካቸውም መመስገን ምክንያት ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

ማቴ 5÷17-48 ‹‹**እኔ ሕግና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ፡፡ ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም ... ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም››**

ክርስቶስ ከሊቃውንት መካከል አልተነሣም፡፡ በሊቃውንትም አልተመረጠም፡፡ ደግሞም እንደ ሃይማኖት መሪዎች አልሄደም፡፡ ለምሳሌ ከኃጢአተኞች ጋር ይበላ ነበር፡፡ ሰዎች በእርሱ ሕይወትና ትምህርት ሲደነግጡ ባየ ጊዜ ሕግን ሊፈጽም እንደመጣ ገለጸ፡፡

ክርስቶስ ሕግን እንዴት ፈጸመ?

በራሱ ሕይወት የሕግን ትእዛዝ ሁሉ በመፈጸም፡፡ ከሕግ በታች ሆኖ በመኖር፡፡ /ገላ 4÷4/

በራሱ ሞት መሥዋዕትን ሁሉን በመፈጸም፡፡ /ዕብ 9÷25-26/

የፈሪሳውያንን አተረጓጎም በማፈራረስና ትክክለኛውን ትርጓሜ በማስተማር፡፡ /ማቴ 5÷21-48/

የእግዚብሔርን ቃል ኪዳን በመግለጥ፡፡ ለምሳሌ ምሥጢረ ጥምቀትንና ቅዱስ ቁርባንን በመመሥረት፡፡ ሕግን በፊደል ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ መንገድ በመግለጥ ሕግን እንድንፈጽም መንፈስ ቅዱስን በመስጠት፡፡ /ሮሜ 8÷2-4/

ፈሪሳውያን ከሕዝብ የተለዩ የሃይማኖት መሪዎች ናቸው፡፡ የአባቶችን ወግ በጥብቅ ይጠብቁ ነበር፡፡ በሃይማኖታቸውም ይኩሩ ነበር /ሉቃስ 19÷9-14/ ሆኖም በእግዚአብሔር ፊት በቂዎች አልነበሩም፡፡

**የፈሪሳውያን ዓይነት**

የትከሻ ፈሪሳዊ፡- መልካም ሥራውን እንደ ባጅ ሠርቶ በትከሻው ይይዛል፡፡

የቆይታ ፈሪዊ፡- መልካም ሥራውን ሰዎች እንዲያዩለት ሰዎችን የሚያስቆም፡፡

ዕውር ፈሪሳዊ፡- ሴቶችን እንዳያይ ዓይኑን ሸፍኖ የሚሄድ፡፡

ምግባር ቆጣሪ ፈሪሳዊ፡- ሁልጊዜ መልም ሥራውን እየደመረ ከኃጢአቱ ጋር የሚያወዳድር፡፡

መፍቀሬ እግዚአብሔር ፈሪሳዊ፡- እንደ አብርሃም ያለ ነው፡፡

**ፈሪሳውያን ስህተታቸው ምን ነበር?**

ሃይማኖታቸው ልብ ወደ መለወጥ አያደርስም ነበር፡፡ ማር 7÷14-23

ሥነ ሥርዓት እየሰበኩ ሌላ ሕግንና ትዕዛዝን ይረሱ ነበር፡፡ ማቴ 23÷23

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ የራሳቸውን ትዕዛዝ ይጨምሩ ነበር፡፡ ማቴ 5÷43

እግዚአብሔርን ሳይሆን እራሳቸውን ያመሰግኑ ነበር፡፡ ሉቃስ 18÷9-14

ማቴ 5÷21-23 ‹‹**ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፡፡ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፡፡**››

እኔ ግን እንዲህ እላለሁ ሲል ክርስቶስ መናገሩ እውነተኛ ሠራዔ ሕግነቱን፤ አምክነቱን በቀጥታ ያስረዳል፡፡ ማለት የቀደመውን ሕግ የሠራው የደነገገውም እርሱ እንደመሆኑ አሁንም ከቶ አልሻረውም፣ አልናቀውም፣ አላቃለለውም ግን ያንኑ አጠበቀው፣ ባለስልጣንነቱን የሕግ ባለቤትነቱን በይበልጥ ገለጠበት እንጂ፡፡

የብሉይ ሕግ የሚለው አትግደል ነበር፡፡ አዲሱ ሕግ ግን ወንድምህን በከንቱ አታስቆጣ፣ አታሳዝን፣ አትሳደብ ሲል ለሞት ምክንያት የሚሆኑ በሮችን ዘጋ፣ የግዳይ ምክንያት የሚሆኑትን ሥራቸውን ቆረጠ፡፡ በብሉይ ሕግ ወንድም የሚባለው እስራኤላውያን ለእስራኤላዊው ነው፡፡ ክርስቶስ ግን ወንድሙን የተቆጣ ሲል በመላ የሰው ነገድ የሆነውን ሁሉ ነው፡፡ በክርስትና ሃይማኖት መሠረት ሰው ሁሉ የአንድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ስለሚያምን ሁሉም ወንድሙ ሁሉም እኅቱ ነው፡፡ /ሉቃስ 10÷25-37/

ወንድሙን በከንቱ የተቆጣ ማለት፡- ምክንያት ካለ ይቆጣ ይጣላም ማለት አይደለም፣ ሕገ እግዚአብሔር ሲፈርስ፣ የሰው ሕይወት ከመንፈሳዊ መስመር ውጭ ሆኖ ሲገኝ፣ በፍቅር መምከር እምቢ ሲል መቆጣት መገሰጽ ተገቢ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡

በከንቱ የሚቆጣ፤- እንዲሁ በፍርድ እንዲፈረድበት ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ በማለት የሚሳደብ ግን በሸንጎ ይፈረድበታል ማለት ለሞት ወይም ለመግደል ምክንያት የሚሆን የሚያነሣሳ ስድብ ስለሆነ ቅጣቱን ከፍ አድርጎ ተናገረው፡፡

ደንቆሮ በማለት የሚሳደበው ግን ሰውን ብቻ የበደለ የሰደበም ሳይሆን ፈጣሪውንም የሰደበ በመሆኑ በገሃነም እንደሚፈረድበት ቅጣቱም የበለጠ ከፍተኛ መሆኑን ገልጦ ተናገረ፡፡

እንግዲህ ነፍስ የገደለማ ምን ያህል ከፍተኛ ቅጣት ያገኘው ይሆን? ይህን በማመዛዘን ከመበደል በወንጀልም ሥራ ላለመድረስ በከንቱ በወንድሙ ላይ አለመቆጣት ወንድሙን በከንቱ አለመጣላት በሆነውም ባልሆነውም አለማሳዘን አለማስቆጣት ነው፡፡ ክርስቶስ ስድብን በነፍስ ገዳይ አንጻር የተመለከተው ለነፍስ መጥፊያ መነሻ መሆኑን በመመልከት ነው፡፡ ስለዚህ ማንም ክርስቲያን በወንድሙ ላይ መቆጣት ማስቆጣትም ተገቢ አለመሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡ ከክርስቲያን አንደበት ሊወጣም ሊሰማም የሚገባው ቡራኬ፣ ምክር፣ ተግሳጽ እንጂ ቁጣ፣ እርግማን፣ ስድብ ሊሆን አይገባም፡፡

ማቴ 5÷23-25 ‹‹**እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፡፡ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ**››

ሰጥቶ ቢሄድ መባው እንኳን የገባልኝ እንጂ ብሎ ዕርቁ በቀረ ነበርና፡፡ ይዞ ወደ ቤቱ ተመልሶ ቢሆን ዕርቁም መባውም በቀረ ነበርና ልብ እንዲቀረው በአዳሪ አኑሬያለሁ ብሎ ፈጥኖ ታርቆ እንዲመለስ እዲህ አለ፡፡

አንድም፡-ጸሎት በምትጸልዩበት ጊዜ የነቀፍከው ወንድምህ እንዳለ ብታስብ ጸሎቱን ትተህ ሂድ አስቀድመህ

ከወንድምህ ተዋቅሰህ ታርቀህ ከዚያ በኋላ መጥተህ ጸሎትህን ጸልይ፡፡ በቂም በበቀል ሆነው የጸለዩት አይጠቅምምና፡፡

ማቴ 25÷25 ‹‹**አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባለጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፡፡ ባለጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው ወደ ወህኒም ትጣላለህ፡፡ እውነት እልሃለሁ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም**››

የእርቅን አስፈላጊነት ያስተምራል፡፡

አንድም ፡-በዚህ ዓለም ሳለህ በባላጋራህ በዲያቢሎስ እወቅበት፡፡ ይህን ዓለም ፍኖት አለው፡፡ በመንገድ አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ እንደሆነ በዚህ ዓለም አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ

ነውና፡፡ ባለጋራ ዲያቢሎስ ለጌታ አሳልፎ እንዳይሰጥህ ጌታም አሳልፎ ለዲያቢሎስ ይሰጥሃል፡፡ ዲያቢሎስ ያግዝሃል፡፡ ሥራ ሰርተህ ያገኘኸው ጸጋ ክብር ይቅርና በአርባ ቀን ያገኘኸውን ልጅነት እስከማጣት ደርሰህ ከገሃም አትወጣም ብዬ እንዳትወጣ በእውነት እነግርሃለሁ፡፡

አንድም ፡-በዚህ ዓለም ሳለህ በባለጋራህ በፈቃደ ሥጋህ ፈጥነህ እወቅበት፡፡ ባለጋራህ ፈቃደ ስጋ አስፈርዶ ለጌታ እንዳይሰጥህ፡፡ ጌታም አሳልፎ ለዲብሎስ ይሰጥሃል፡፡ ዲብሎስም ያግዝሃል፡፡ በነቢብ በገቢር በሰራኸው ኃጢአት ቀርቶ በሐልዮ በሰራኸው ኃጢአት ተፈርዶብህ ከገሃነመ እሳት አትወጣም ብዬ እንዳትወጣ በእውነት እግርሃለሁ፡፡

ማቴ 5÷27-29 ‹‹**አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ግዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አምንዝሯል፡፡**››

አንድ ሰው ዘማዊ በመሆኑ ከሴት በመድረሱ ብቻ ይፈርድታል አላለም፡፡ በውስጣዊ አካል በሐሳብ እንኳን የተመኘው እንደሚፈረድት ጌታ ተናገረ፡፡ አትግደል ከሚለው ቀጥሎ አትሰስን የሚለውን ትእዛዝ አመጣ፣ ብዙ ሕይወት የሚጠፋው አገርም የሚጎዳው ዝሙት ከመሠራቱ የተነሣ ነውና፡፡ ወደ ሴት የተመለከተ ብቻ አላለም፣ ግን አይቶ የተመኘ አለ እንጂ፡፡ ይህም የሚያመለክተው በዓይኑ ማየት ብቻ ሳይሆን ለሴቷ ትኩረት ሰጥቶ የተመለከታት፣ በፈቷም / በመጎምዠት/ ስሜት የተመኛት፣ ስሜቱን ያሳረፈባት ማለቱ ነው፡፡ ይህ ሰው ለዚች ሴት አንድ ግምት ሰጥቷል፤ ማለት ሰው አላየውም አላወቀውም እንጂ እርሱ አድርጎል ሰስኖባታል፡፡ ጌታ የልብ አምላክ እንደመሆኑ በልብ የሚታሰበውን እንደሆነ እንደተደረገም ስለሚቆጥረው ሴትን ያየ ሁሉ የተመኛትም ፈጽሞ በልቡ አመነዘረባት አለ፡፡ በዓይን አይቶ በልብ በተመኘ ወንጀሉንስ መፈጸም የሚከለክለው ቦታ፣ ጊዜ ሌላም ልዩ ልዩ ሁኔታዎች እንጂ በእርሱ በኩል ፈጽሞታል፡፡ ስለዚህ በድኗል፣ሰስኗል ማለት ነው፡፡

ማቴ 5÷29-30 ‹‹**ቀኝ ዓይንህም ብታሰናከልህ አውጥተህ ካንተ ጣላት ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፉ ይሻላልና፡፡**››

ቀኝ ዓይን ቀኝ እጅ እንዳለ በቁሙ ይተረጉማል፣ በዝሙት እንዳይወድቁ ዓይናቸውን በወስፌ ያወጡ እጃቸውን የቆረጡ አሉና፡፡ /አንድምታ ወንጌልን ተመለከት/

አንድም ፡- ዓይን የተባለች ሚስት ናት፤ከዓይን የሚሰወር እደሌለ ከሚስትም የሚሰወር የለምና ሚስትህ መልካም ያልሆነ ሥራ ላሠራህ ብትልህ ፈቃዷን አፍርስባት ዛሬ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ አፍርሰህ ኖረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና፡፡ እጅ የተባሉ ልጆች ናቸው፡፡ ‹‹**ወድቆ ይነሡ በእጅ፤ ዘግይቶ ይከበሩ በልጅ**›› እንዲሉ ልጆችህ መልካም ያልሆነ ሥራ እናሠራህ ቢሉህ ፈቃዳቸውን አፍርስባቸው፡፡ ዛሬ በዚህ ዓለም የልጆችህን ፈቃድ አፍርሰህ ኖረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሀልና ሲል ነው፡፡

ማቴ 5÷31-32 ‹‹**ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተብሏል፡፡ እኔ ግን ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል**››

በጠቅላላ ይህ አንቀጽ የሚያስተምረን ባልና ሚስት ወደው ፈቅደው በግል ስምምነት፣ ወላጅና ወዳጅ ተማክሮበት ተስማምቶበት ከተጋቡ በኋላ መፋታት ተገቢ አለመሆኑን ነው፡፡

ሴቷን ለመፍታት የፈቀደ እንደሆነ የነውሯን መግለጫ፣ የፍችዋን ማስረጃ ሰጥቶ እንዲሰዳት ተጽፎ ነበር፡፡ ጌታ ግን ዝሙት ካልሠራችበት በቀር ሊፈታት የማይገባ መሆኑን ሲያስረዳ ወዲያውም በነውር የተፈታችውን ደግሞ ማግባት ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን ተናግሯል፡፡

ባሏ እያለ ወደ ሌላ የሄደችው ሴት ባሏን እንደገደለችው፣ በሕይወትም እንደለሌለ እንዳደረገችው የሚቆጠር ስለሆነ እርሷ እንድትፈታ ፈቅዷል፡፡

አንድ ሰው ሚስቱን ከፈታ በኋላ ሳያገባ እንዲኖር ቅዱስ ሉቃስ ያስገነዝባል፣ እንዲሁም ሌላው የፈታትን ያገባ እነርሱም እንደበደሉ ይናገራል፡፡ /ሉቃስ 16÷16/

ማቴ 5÷33-37 **‹‹ደግሞ ለቀደሙት በውሸት አትማል፣ ነገር ግን መሐላህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ከቶ አትማሉ በሰማይ አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፡፡ በኢየሩሳምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፡፡ በራስህም አትማል አንዲቱን ጸጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና፡፡ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም ይሁን ከነዚህም የወጣ ከክፉ ነው፡፡››**

ለቀደሙት ሰዎች በእውነት እንጂ በሐሰት፣ በስመ እግዚአብሔር እንጂ በስመ ጣዖት፣ ዳኛ ፈርዶባችሁ እንጂ ዳኛ ሳይፈርድባችሁ አትማሉ ያልኳቸውን ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን ከቶ አትማሉ እላችኋለሁ፡፡ ከሰማይ የወረደ መቅሰፍት አይሳተን፣ ሰማይ ተኀርዶ ይጫነን እያሉ ይምላሉና የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና አለ፡፡ ምድር ተከፍታ ትዋጠን በማለት ይምላሉና በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ /መመላለሻ/ ናትና አለ፡፡ ከበረከተ ምድር አያሳትፈን ከምድረ ከነዓን ያስወጣን፣ እያሉ ይምላሉና በኢየሩሳምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ማለት የልዑል እግዚአብሔር መመለኪያው ናትና አለ፡፡ እንዲሁ እንደ ጸጉሩ ያጥቁረኝ ብለው ይምላሉና በራስህም አትማል አንዲቱን ጸጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና፡፡ ነገር ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም ይሁን ከነዚህም የወጣ ከክፉ /ከዲያብሎስ/ ነው፡፡ /ዘሌ 19÷12፤ ዘፀ 20÷7፤ ዘዳ 5÷11፣ ዕ 5÷12/

በአጠቃላይ አነጋገር ክርስቶስ ፈጽሞ መማል እንደማይገባ አስተምሯል፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤት፣ ስለከባድ ነገር መሐላ እንደሚፈቀድ ተጽፏል፡፡ /ማቴ 26÷63፣ ዘጸ 22÷11፣ ዕብ 6÷16/

ማቴ 5÷38-42/ **‹‹ዓይን ስለዓይን፣ ጥርስም ስለ ጥርስ እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን አትቃወሙ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብ እንዲወስድ ለማወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፡፡ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሔድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ፡፡ ለሚለምንህ ስጥ ካንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል፡፡››**

**‹‹ዓይን ስለዓይን››** በጊዜው በነበረው ኅብረተሰብ መካከል ትክክለኛ ፍትሕ እንዲገኝ ለባለሥልጣናት ለዳኛ የተሰጠ ሕግ ነበር፡፡

**‹‹ክፉውን አትቃወሙ››** ክፉ የተባለ ዲያብሎስ ነውና የዲያብሎስ መሳሪያ የክፋቱ መግለጫ ሆኖ መጥቶ አንድ ሰው ክፉ ቢያደርግብህ ነገሩን በትዕግስት ተመልከተው ክፉ አድራጎቱን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስጠው ማለቱ ነው፡፡

**‹‹ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፡፡ እጀ ጠባብህን ቢቀማህ መጎናጸፊያህን ደግሞ ጨምርለት……››** ሲል ምሳሌ የሰጠው እስከዚህ ድረስ ከባድ ነገር ቢደርስብህ እንኳ አንተ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆንክ በትዕግስት ትምህርት ስጠው፤

ትሩፋትም አስተምረው፡፡ ይህን ሁሉ የሚያደርገው አቅም አንሶት ሳይሆን የበለጠ ዋጋ የሚገኝበት ስለሆነ ነው ብሎ ወደ በሃይማኖትህ ወደ በጎ አድራጎትህ እንዲገባ አድርገው ማለቱ ነው፡፡

**‹‹አንድ ምዕራፍ ትሔድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ››** መምህረ ንስሐህ አንድ ሱባዔ ቀኖና ቢሰጥህ ይህ ተስማምቶኛል ጨምርልኝ ብለህ ከእሱ አስፈቅደህ ሁለት ሱባዔ ጹም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ አንቀጽ ውስጥ አምስት ምሳሌዎች ተነግረዋል፡፡ ሁለቱ ከባዶች ናቸው፡፡ ግን ለክርስቲያን ፍጹምነቱ የሚገለጥባቸው መሳሪያዎቹ ናቸው፡፡ ኃይል አለኝ ብሎ በኃይሉ ተመክቶ መግደል ወደሞት የሚያደርስ ስለሆነ አትግደል የተባው ሕግ እንዳይሻር በትዕግሥት ሆኖ ሁሉን በቀላሉ ማሳለፍ እንዳለበት ይህ አንቀጽ በሰፊው ያስረዳል፡፡

ማቴ 5÷43-48፣ **‹‹ባንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ፡፡ እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑት ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና፡፡ የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ ብትነሱ ምን ብልጫ ታርጋላችሁ አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፡፡››**

ወዳጅን መውደድ የሁሉ ዘዬ ነው፡፡ ማለት ወዳጁን የማይወድ የለምና እውነተኛው ፍቅር ግን ጠላትን መውደድ ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ጠላታችንን እንድንወድ አጥብቆ ይነግረናል፡፡

አባታችን እግዚአብሔር ጎዳጌ በቀል፤ ሁሉን ይቅር የሚል አምላክ ነው፡፡ ቂም በቀል የለበትም እንግዲያውስ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርን አባትነት የሚያምን ከሆነ አንደ አባቱ እንደ እግዚአብሔር ሁሉንም ይቅር ባይ መሆን አለበት፣ የተለየ ጠላት ሊኖረው ከቶ አይገባም ማለቱ ነው፡፡ እግዲያውስ ክፉ አድራጊዎች እነርሱ ቢረግሟችሁ እናንተ መርቁ፣ ቢጠሏችሁ ውደዱ ፣ ቢያሳድዷችሁ ጸልዩላቸው ሲል እናንተ የእግዚአብሔር ልጅነታችሁን በሥራ አሳዩ እናንተ ከእርሱ ከፍ ያላችሁ የመቻል ኃይል ያላችሁ እንደመሆናችሁ በሥራ ግለጡላቸው ለማለት እንዲህ አለ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት

ትምህርት ክፍልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የተዘጋጀ

መስከረም 2006 ዓ.ም